## የካናዳ የቅድመ ጉዞ ገለጻ

# የተሳታፊዎች መልመጃ/መማሪያ

ወደ ካናዳ ለሚገቡ
አዲስ መጪዎች
የሚያገለግል መመሪያ




COA OCE
Canadian Orientation Abroad
Orientation canadienne à l'étranger

IOM
UN MIGRATION

Funded by:
Immigration, Refugees and Citizenship Canada

Financé par :
Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada

በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹ አመለካከቶች የደራሲው ናቸው እንጂ የዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) አስተያየት ናቸው ማለት አይደለም። በህትመቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ሥያሜዎች እንዲሁም የቀረቡ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች ድርጅቱ (IOM) በሀገራት፣ በግዛት፣ በከተማ ወይም በአካባቢ ወይም በባለስልጣናቶቹ፣ በድንበር ወይም በወሰን የሕግ ሁኔታ ላይ ያለውን አመለካከት የሚገልጹ አይደሉም።

ደርጅቱ (IOM) ሰብአዊ እና ሰላማዊ ፍልሰት ለፍልሰተኞች እና ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ ነው ለሚለው መርህ ተገዢ ነው። የመንግሥታት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፣ ከዓለማቀፉ ማኅበረሰብ አጋር ከሆኑት ጋር የሚከተሉትን አብሮ ይሠራል፡ በስደት ዙሪያ ያለውን ፈተና መጋፈጥ፣ የስደት ጉዳዮችን በሚመለከት ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፣ በፍልሰት ውስጥ ያለውን የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማበረታታት እንዲሁም የሰዎችን ክብር እና የስደተኞችን ደኅንነት መጠበቅ።

---

ይህ ህትመት ሊሰራ የቻለው ከዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) ጋር በተደረሰ ስምምነት መሠረት በካናዳ መንግስት ድጋፍ ነው። በዚህ ውስጥ የተካተቱ ሐሳቦችና ዕይታዎች የካናዳ መንግስትን አመለካከት አይወክሉም።

መኖሪያቸውን በካናዳ ያደረጉ የመንግስት ሠራተኞች፣ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ባለሞያዎችና አዲስ መጪዎች እንዲሁም ዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) እና በካናዳ እና ከካናዳ ውጪ የሚገኙ በውጪ አገራት የካናዳ የቅድመ ጉዞ ገለጻ ሠራተኞች (COA/OCE) ስላደረጋችሁት አስተዋጽኦ እናመሠግናለን። በካናዳ የሚቋቋሙ ስደተኞችን ዝግጁ በማድረግ የነበራቸው ትጋት እና ሃሳብ የዚህ ህትመት መሠረት ሆኗል።

አሳታሚ: ዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM)
17 route des Morillons
የፖስታ ሳጥን ቁጥር Box 17
1211 ጄኔቫ 19
ስዊዘርላንድ
ስልክ: +41 22 717 9111
ፋክስ: +41 22 798 6150
ኢሜይል: hq@iom.int
ድረገጽ: www.iom.int

በአን ዩሱፍ፤ ለዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) የተዘጋጀ
ይህ እትም ያለ መደበኛ አርትዖት በIOM ወጥቷል።
ይህ እትም የወጣው ያለ IOM የህትመት ክፍል (PUB) ይሁንታ ነው።
ይህ ህትመት ያለኦፊሴላዊ ትርጉም በTRS ክፍል ወጥቷል።
በእንግሊዝኛ የመጀመርያው እትም ኦፊሴላዊ ያልሆነ ትርጉም፣ የተሰጠው ርዕስ *Canadian Orientation Abroad Participant Workbook: A pre-departure guide for newcomers to Canada.*

ተጨማሪ ጥቆማዎች: IOM ፣ የካናዳ ቅድመ ጉዞ ግለጻ የተሳታፊዎቸ መማሪያ መጻሐፍ፣ ለካናዳ የቅድመ ጉዞ መመሪያ ለአዲስ መጭዎች (2020) ጄኔቫ፡፡

---

ISBN 978-92-9268-173-9 (Print)
ISBN 978-92-9268-517-1 (PDF)

© IOM 2022

CC BY NC ND

አንዳንድ መብቶች የተጠበቁ ናቸው። ይህ ስራ
**የጋራ የፈጠራ ባለቤትነት-ንግድ ነክ ያልሆነ-የማይሻሻል 3.0 IGO ፍቃድ** (CC BY-NC-ND 3.0 IGO) ስር ይገኛል።*

ለተጨማሪ ዝርዝሮች እባክዎን **የቅጂ መብት እና የአጠቃቀም ውልን** ይመልከቱ።

ይህ ኅትመት በዋናነት ለንግድ ጥቅም ወይም ለገንዘብ ማካካሻ ለታለመ ዓላማ ጥቅም ላይ መዋል፣ መታተም ወይም እንደገና መሰራጨት የለበትም፣ ከትምህርት ዓላማዎች በስተቀር፣ ለምሳሌ. በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ እንዲካተት።

ፍቃዶች፡ ለንግድ አገልግሎት ወይም ለተጨማሪ መብቶች እና የፍቃድ ጥያቄዎች በ publications@iom.int መቅረብ ይኖርበታል።

* https://creativecommons.org/licenses/by-nc-nd/3.0/igo/legalcode

PUB2023/006/U

# ማውጫ


የፈጣን ምላሽ ኮዶች አጠቃቀም መመሪያ ገጽ i

ምልክቶች ገጽ ii

ተግባራት ገጽ iv

1. ስለ ካናዳ አጭር መግለጫ ገጽ 1

2. ጉዞ ገጽ 35

3. ድጋፍ እና አገልግሎቶች ገጽ 63

4. መኖሪያ ቤት ገጽ 81

5. ጤና ገጽ 93

6. ትምህርት ገጽ 107

7. ሥራ ገጽ 123


8. ገንዘብ አያያዝ ገጽ 141

9. መጓጓዣ/ትራንስፖርት ገጽ 159

የሂደት ካርታ የጀርባ ገጽ ውስጠኛ ክፍል

# የፈጣን ምላሽ ኮድ አጠቃቀም መመሪያዎች

በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ፣ እንደዚህ ያሉ ምልክቶችን ያገኛሉ፣ እነዚህም በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ወደሚገኙበት ማስፈንጠሪያ የሚጠቁሙ ናቸው። እነዚህም የፈጣን ምላሽ ኮዶች ይባላሉ። በእነዚህ ኮዶች በስማርት ስልኮች ወይም በታብሌቶች ላይ ያሉ ካሜራዎችን በመጠቀም በበይነ መረብ ላይ በፈጣን ምላሽ ኮዶች መረጃዎችን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ያንብቡ። ይህንንም ለማድረግ የበይነ መረብ ግንኙነት ያስፈልግዎታል።



1. በመጀመሪያ የያዙት መሳሪያ ላይ የሚገኘው ካሜራ የፈጣን ምላሽ ኮዶችን ማንበብ እንደሚችል አልያም የኮዶቹን ማንበቢያ መተግበሪያ ከበይነ መረብ ማውረድ ይጠበቅብዎ እንደሆነ ያጣሩ።



2. የበይነ መረብ ግንኙነት እንዳለዎ እርግጠኛ ይሁኑ።



3. የስልክዎን ካሜራ ወይም ኮዱን የሚያነበውን መተግበሪያ ይክፈቱ።



4. የካሜራው እስክሪን ወደ መሀል መሆኑን በማረጋገጥ ሊነበብ የተፈለገው የፈጣን ምላሽ ኮድ ላይ እንዲያነጣጥር ያድርጉ።




5. ኮዱ እስኪነቃኝ ድረስ ይጠብቁ።




6. የኮዱን ይዘት በመክፈት ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።

**በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ ላይ የፈጣን ምላሽ ኮድ በእንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ እንዲሁም በሌሎች ቋንቋዎች ጭምር ወደሚገኙ የተለያዩ ጠቃሚ እና ታማኝ ድረገጾች ማስፈንጠሪያዎችን ያቀርብልዎታል። እነዚህን ቋንቋዎች የማይናገሩ ከሆነ፣ ድረገጹ የያዘውን መረጃ ለመረዳት በድህረ ገፅ የቀጥታ መተርጎሚያዎችን መጠቀም ይችላሉ።**




# ምልክቶች

በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ የተለያየ ትርጉም ያላቸውን ምልክቶች ያገኛሉ። ስለ ምልክቶቹ አጭር ማብራሪያ ተቀምጧል። ስለእነዚህ ምልክቶች እና ስለትርጉማቸው የመልመጃ መጽሐፍን በማንበብ የበለጠውን የሚያውቁ ይሆናል።



1. የካናዳ መንግስት



2. በኩቤክ ዙሪያ ያሉ መረጃዎች



3. በካናዳ ቀደምት ሕዝቦች



4. ካናዳ ወይም ካናዳዊ




5. ከካናዳ ውጪ ያሉ አገራት



6. መልክዓ ምድራዊ መገኛ



7. የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች



8. በስርዓተ ጾታ ማንነት፣ በስርዓተ ጾታ ገለጻና አረዳድ፣ በድምሩ የጾታ ስርዓት ብዝኀነት



9. የሃይማኖት ብዝኀነት



10. እርዳታ እና ድጋፍ



11. የገንዘብ ድጋፍ



12. አስቸኳይ የሰፈራ ድጋፍ



13. በመንግስት ድጎማ የሚደረግላቸው ድርጅቶች




14. የስደተኞች ግላዊ ሊጋሾች



**15.** መብቶች በካናዳ



**16.** ህጎች በካናዳ



**17.** ግላዊነት፣ ጥበቃ ወይም ደኅንነት




**18.** የተፈቀደ ወይም ሕጋዊ



**19.** የማይፈቀድ ወይም ሕገወጥ



**20.** የማይፈለግ ወይም ተቀባይነት የሌለው



**21.** ጊዜ ማሳለፊያ





**22.** በጊዜ የተገደቡ



**23.** መረጃ



**24.** ፍለጋ




**25.** የትምህርት ዲግሪዎች ወይም የምስክር ወረቀቶች






**26.** የሥራ ልምድ



**27.** ጋብቻ/ትዳር



**28.** ግለሰብ (ጾታ ያልተገለጸ)

# የመልመጃ ተግባራት

በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ፣ በካናዳ ያለውን ሕይወት በሚመለከት ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት የሚረዱ፣ ሊደረጉ የሚገባቸው ተግባራት አሉ። መመሪያዎቹ በየተግባራቱ መግቢያ ላይ ተጽፈዋል። እነዚህን በጥንቃቄ ያንብቡ። በዚህ መሠረት ቀሪዎቹን እንዲመልሱ ለእያንዳንዱ የመልመጃ ተግባር የመጀመሪያው ጥያቄ ላይ በቀይ ቀለም ምላሹ ተቀምጧል። ተግባራቱ ትክክለኛ መልስ ካላቸው፣ በግልባጭ የተጻፉትን መልሶችን ከየገጹ መጨረሻ ላይ ይመልከቱ።
በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ የተካተቱ የተግባር ዓይነቶች፤

**ሀ) የካርታ መልመጃ ተግባራት**
አንድን ስፍራ በካርታ ላይ መፈለግና በዚያ ላይ የ ‹ ✗ › ምልክት ማድረግ።

**ለ) የማዛመድ መልመጃ ተግባራት**
በቁጥሮች እና በቃላት መካከል ማስመር።

**ሐ) ምልክት በማድረግ ምላሽ የሚሰጥባቸው የመልመጃ ተግባራት፤**
ጥያቄውን ካነበቡ በኋላ “ ✓ ” ምልክትን በሳጥን ውስጥ ማቀመጥ።

**መ) የመመደብ የመልመጃ ተግባራት**
ምስሎቹን በመመልከት በሳጥኑ ውስጥ ምልክቶችን በማስቀመጥ መመደብ።

**ሠ) የ‹ባዶ ቦታውን ሙላ› የመልመጃ ተግባራት**
በቀረበው ክፍት ቦታ ላይ የጎደለውን መረጃ ማሟላት።

**ረ) በቅደም ተከተል የማስቀመጥ የመልመጃ ተግባራት**
የተጻፉትን በማንበብና ከፊታቸው በሚገኘው ሳጥን ውስጥ ቁጥሮችን በማስቀመጥ ከመጀመሪያ ወደ መጨረሻ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ።

**ሰ) የታሪክ ሰሌዳ**
ታሪክ የሚናገሩ በቅደም ተከተል የተቀመጡ ምስሎችን መመልከት።

**እንዲያስቡበት ወይም ምላሽ እንዲሰጡበት የሚፈለገውን ጥያቄ እንዲህ ባለ መልኩ በሳጥን ውስጥ ያገኙታል።**

**እንዲያስታውሷቸው የሚፈለጉ መረጃዎች እንዲህ ባሉ ሳጥኖች ውስጥ ይቀመጣሉ።**

# ማስታወሻዎች

# ምዕራፍ 1
# ስለ ካናዳ አጭር መግለጫ




# ምዕራፍ 1
# ስለ ካናዳ አጭር መግለጫ




## 1.1 ስለካናዳ ይህን ያውቃሉ?


ካናዳ የተለያዩ የመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ዓይነት ያላት በዓለማችን ሁለተኛዋ ትልቅ ሀገር ናት። እንደየስፍራው ሁኔታ ከፍታ ያላቸው ተራሮች፣ ሰፋፊ እና ለጥ ያሉ ሜዳዎች፣ ጫካዎች እና በርካታ ሐይቆች እንዲሁም ወንዞች ይገኛሉ።



አሁን ካናዳ በሚባለው በዚህ ስፍራ የመጀመሪያዎቹ አውሮፓውያን ሳይሰፍሩ በፊት ጥንታዊ ሕዝቦች ተደላድለው ይኖሩ ነበር። እነዚህ ጥንታዊ ሕዝቦች ከቃልም ሆነ ከጽሑፍ ታሪክ በፊት የነበሩ ናቸው።

አሁን፣ የካናዳ ማኅበረሰብ በእድሜ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታ ማንነት፣ በችሎታና በኢኮኖሚ ደረጃ ብዝኀነት ያለው ነው።





ካናዳ ከስፋቷ አንጻር የነዋሪዋ ብዛት ጥቂት የሚባል ነው። የካናዳ ሕዝብ ብዛት በአሁኑ ጊዜ________________________ ነው ተብሎ ይገመታል።.




«ካናዳ» የሚለው ሥያሜ የመጣው ከሁሮን-ኢሮኩዮስ (የመጀመሪያ ዜጎች) ‹ካናታ› ከሚለው ቃል ነው፤ ትርጓሜውም ደኅንነት ያለበት አካባቢ፣ መንደር ወይም ሰፈር ማለት ነው።



ካናዳ በጠቅላይ ሚኒስቴር እንጂ በፕሬዝዳንት አትመራም። ለካናዳ በምሳሌያዊነት እንደ ርዕሰብሔር/ፕሬዝዳንት ሆነው የሚያገለግሉት የካናዳ ንጉሥ ወይም ንግሥቲቱ ናቸው። ይህም በእንግሊዝ አገር ካለው የንጉሣዊ ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው። ንጉሡ ወይም ንግሥቱቲ በመንግስት ውስጥ ምንም ዓይነት ሥልጣን/ኃይል የላቸውም።



ካናዳ ዴሞክራሲያዊት አገር ስትሆን፣ የተመረጡ የተወካዮች እና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶች ያገለግላሉ፤

በካናዳ ከ200 በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ። እነዚህም የጥንታዊ ሰዎች ቋንቋዎችን የሚያካትቱ ሲሆን በካናዳ ኑሮአቸውን ያደረጉ የበርካታ ፍልሰተኞች ቋንቋም ይነገርባታል።





## 1.2 ካናዳን የቆረቆሩ ሰዎች

ካናዳን የቆረቆሩ ሦስት ዓይነት ሰዎች ይገኛሉ፤ እነዚህም ጥንታዊ ሕዝቦች፣ ፈረንሳዮች እና ኢንግሊዞች ናቸው። በተያያዘ የካናዳ የምሥረታ ታሪክን ስንመለከት፣ ሰደተኞች የካናዳን ማኅበረሰብ በመመሥረት በኩል ጠቃሚ ሚና ተጫውተዋል።.






1. «ጥንታዊ ሕዝቦች» የተባሉት አሁን ካናዳ በሚባለው መሬት ላይ ይኖሩ የነበሩ የመጀመሪያዎቹ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ የአውሮፓ ሰፋሪዎች በስፍራው ከመድረሳቸው በጣም ቀድመው በዚያ ይኖሩ ነበር። የራሳቸው ኢኮኖሚ፣ ቋንቋ እና ባህል የነበራቸው ናቸው።




በአሁኑ ጊዜ፣ በካናዳ ያሉ አምስት በመቶ ሰዎች ጥንታዊ ሕዝቦች ናቸው። በካናዳ እውቅና የተሰጣቸውም ሦስት የተለዩ ኅብረቶች/ ቡድኖች አሉ።



ሀ) **የመጀመሪያዎቹ ዜጎች**

‹የመጀመሪያዎቹ ዜጎች› የሚባሉት የተለያዩ እና በመቶዎች የሚቆጠሩ ናቸው። አሁን ላይ ቋንቋቸው ከ60 በላይ ሲሆን፣ እነዚህንም ቋንቋዎች እንዲያገለግሉ ለማስቻል ሰዎች ጥረት ያደርጋሉ። የመጀመሪያዎቹ ዜጎች በመላው ካናዳ በሚገኙ ከተማዎችም ይኖራሉ። ግማሽ የሚሆኑት ለእነሱ ጥቅም እንዲውል በተለየው ‹ሪዘርቭስ› ተብሎ በሚጠራው መሬቶች/ አካባቢዎች ላይ ይኖራሉ። የተቀሩት ብዙዎች ደግሞ በራሳቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በመስጠት እየተሳተፉ ራሱን በሚያስተዳድር መንግሥት ስር ይኖራሉ።




**ለ) ኢንዩት**

በሰፊው የካናዳ ሰሜናዊ ክፍል በትንሽ ኅብረተሰብ ውስጥ ይኖራሉ። ኢኑክቲቱት የሚባለው ቋንቋው ሲሆን ‹ኢንዩት› ማለት ‹ሰዎች› ማለት ነው። የኢንዩት የመሬት፣ የባህር እና የዱር ሕይወት ላይ ያላቸው እውቀት እና ግንዛቤ ከባድ በሆነው የአርክቲክ ከባቢ ውስጥ ችግሩን ተቋቁመው እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። አሁን ላይ ማኅበረሰቡን ለመመገብ አደን እና አሳ ማጥመድን የቀጠሉበት ሲሆን፣ በዚህም የባህር አንበሳ የሚባለው ሲል ፣ ኣሳ ነባሪ፣ ካሪቡ የተባሉትን እንስሳት ጨምሮ አስግረው እና አድነው ለምግብነት ይጠቀማሉ።




**ሐ) ሜቲስ**

የእነዚህ ሕዝቦች ከመጀመሪያ የአውሮፓውያን የቆዳ (እንደ ጥንቸል ያሉ ትንንሽ እንስሳት ቆዳ) ነጋዴዎች እና ከመጀመሪያዎቹ ዜጎች ሴቶች የተወለዱ ናቸው። ሜቲስ በኋላ ላይ ይህ ንግድ ባለበት መስመር የሚገኝ የራሱ ባህል እና ወግ ያለው የተለየ ማኅበረሰብ ሆነ። አሁን ላይ በመላው ካናዳ የሚኖሩ ሲሆን፣ ይልቁንም በኦንታሪዮ እና ምዕራብ ግዛቶች አካባቢ ይገኛሉ።




በ1600 የአውሮፓውያን ሰፋሪዎች አሁን ካናዳ በሚባለው ስፍራ መኖር እና አካባቢዎችን በቅኝ ግዛት መያዝ ጀመሩ። ቅኝ ግዛት ማለት በሌሎች ተይዞ የቆየን መሬት  ባለቤትነትን ቀይሮ ቦታው ላይ መስፈር ነው። በዚህ መሠረት በዚያን ዘመንም አውሮፓውያን ሰፋሪዎች ጥንታዊ ሕዝቦችን ቅኝ ገዝተው ነበር።





**2.** ‹‹ፈረንሳዊ ካናዳውያን›› አኬዳዊያን፣ ኵቤካዊያን እና ሌሎች በመላው ካናዳ የሚገኙ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ማኅበረሰቦችን ያካትታል።

‹አኬዳዊያን› የሚባሉት አሁን የአትላንቲክ አካባቢ በሚባለው አካባቢ የሚገኙ እና የፈረንሳይ ሰፋሪዎች ተወላጅ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የአኬድያንስ ባህል እያደገ እና እየተስፋፋ እና ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች ባሉበት የካናዳ ክፍልም ሕይወት ዘርቶ ይገኛል።

‹ኵቤካዊያን› የኵቤክ ሕዝቦች ናቸው። አብዛኞቹም ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪና ከ1600 እስከ 1700 የጋራ ዘመን መካከል ባለው ጊዜ ወደ ስፍራው የመጡ የፈረንሳይ ሰፋሪዎች ተወላጅ ናቸው። ኵቤካዊያን የተለየ ማንነት፣ ባህል እና ቋንቋን አላቸው። በአሁኑ ጊዜ ከኵቤክ ውጪ ባሉ ሌሎች ግዛቶች አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች ይኖራሉ።




**3.** ‹‹ኢንግሊዛዊ ካናዳውያን›› የእንግሊዝ፣ የዌልስ፣ ስኮትላንድ እና አይሪሽ ዝርያ/ተወላጅ ናቸው። እነዚህም ከ1600 እና 1900 የጋራ ዘመን መካከል ወደ ካናዳ የመጡ ናቸው።



በርካቶቹ ጥንታዊ ሕዝቦች አውሮፓውያኑን በደስታ የተቀበሏቸው ሲሆን፣ ሰላማዊ የንግድ ልውውጥም ከእነርሱው ጋር ያደርጉ ነበር። ለአውሮፓውያኑ ከባዱን የካናዳን የክረምት ወቅት እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ ዘዴውንም ያስተምሯቸው ነበር።



ውሎች በጥንታዊ ሕዝቦች እና በካናዳ መንግስት መካከል የተደረጉ ስምምነቶች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ዜጎች የሚባሉት ትምህርት ቤት ሊገነባላቸው፣ ዓመታዊ ክፍያ ሊሰጣቸው እና የተወሰነ የአደን እና አሳ ማስገር መብት ሊሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸው በተለዋጭ ሰፊ መሬቶችን አሳልፈው ሰጥተዋል። ጥንታዊ ሕዝቦች እና መንግሥት እነዚያን ስምምነቶች ሁልጊዜ በተመሳሳይ መንገድ አይረዷቸውም። አሁንም ቢሆን ካናዳ ለጥንታዊ ሕዝቦች የተገባውን ቃል ማክበሯ አነጋጋሪ ነው። የጥንታዊ ሕዝቦችን ታሪክ በሚገባ መማር በካናዳ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት ያግዝዎታል።




ካናዳ ከጥንታዊ ሕዝቦች ጋር ያላትን ግንኙነት እውቅና በመስጠት፣ በመከባበር፣ በመተጋገዝ እና በመተባበር ላይ መሠረት በማድረግ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ዝግጁ ናት።

የካናዳ ሕግ ለጥንታዊ ሕዝቦች መብት እውቅና ይሰጣል። እነዚህም፣



**1.** የውል መከበር መብት




**2.** የማደን እና አሳ የማስገር/የማጥመድ መብት



**3.** የመሬት ባለቤትነት መብት



**4.** ራስን በራስ የማስተዳደር መብት



እንደአለመታደል ሆኖ የካናዳ መንግስት የጥንታዊ ሕዝቦችን መብት በተገቢው መንገድ አያከብርም።



በ2008፣ የካናዳ መንግስት የእውነት እና ስምምነት ኮሚሽን አቋቁሞ ነበር። ይህ ቡድን በጥንታዊ ሕዝቦች፣ በመንግሥት እና በሁሉም ካናዳውያን መካከል የመከባበር ግንኙነት እንዲፈጠር እና ግንኙነቱ የሚድንበትን ምክረ ሐሳብ ወይም መንገድ የያዘ ዘገባ አወጣ። አሁንም ጉዳዩ በሂደት ላይ ያለ ሲሆን፣ ‹ስምምነት/እርቅ› ተብሎ ይጠራል።

በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በዚህ ከጥንታዊ ሕዝቦች ጋር በሚኖረው ስምምነት የሚጫወቱት ድርሻ አላቸው።

**መመሪያዎች፡** ለስምምነት የሚመከሩ ተግባራትን ያንብቡ። ይህን በሚመለከት በካናዳ ሲኖሩ ሊያደርጉት የሚችሏቸው ላይ በሳጥኑ ውስጥ "✓" ምልክት ያድርጉ።



☐ **1.** ስለ ጥንታዊ ሕዝቦች በይበልጥ ማወቅ



☐ **2.** ጥንታዊ ሕዝቦችን እና ባህላቸውን ማክበር






☐ **3.** የጥንታዊ ህዝቦች አርቲስቶችን እና ንግድ ስራዎቻቸውን መደገፍ



☐ **4.** በጥንታዊ ሕዝቦች ክዋኔዎች ላይ መሳተፍ

## 1.3 የካናዳ ካርታ

**መመሪያ:** የካናዳን ካርታ ይመልከቱ። የሚኖሩበትን ስፍራ ካወቁ በላዩ ላይ ✕ ምልክት ያድርጉ።




★ ‹ኦታዋ› የካናዳ ዋና ከተማ ናት። መገኛውም ከኦንታሪዮ እና ኩቤክ ግዛት መካከል ነው።

እንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ የካናዳ ብሔራዊ ቋንቋዎች ናቸው። በሕግ፣ የሀገሪቱ የፌዴራል መንግሥት በመላው ካናዳ በሁለቱ ቋንቋዎች፣ ማለትም እንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ አገልግሎቶችን መስጠት ይጠበቅበታል። ኩቤክ የፈረንሳይኛ ተናጋሪ ግዛት ነው። የኒው ብረንስዊክ ይፋዊ ቋንቋዎች ፈረንሳይኛ እና እንግሊዘኛ ናቸው። በሌላው ግዛት ያሉ አብዛኞቹ ሕዝቦች እንግሊዘኛ ተናጋሪ ናቸው። ነገር ግን በመላው ካናዳ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ማኅበረሰቦች አሉ።




በካናዳ ስለ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ማኅበረሰብ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ይህንን ያንብቡ፤



# 1.4 የካናዳ ምልክቶች

***መመሪያ፡*** የካናዳን ምልክቶች ይመልከቱ። በምልክቶቹ እና በማብራሪያዎቹ መካከል መስመር በማስመር ያዛምዱ።



**የንስር ላባ**

1.



***Inuksuk***

2.



**የኢንፊኒቲ ምልክት**

3.



**የማፕል ቅጠል**

4.



**አይጠ መጎጥ**

5.



**የዱር ቀይ አበባ**

6.

ሀ) ይህ በሜቲስ ባንዲራ ላይ የሚገኝ ነው። ትርጉሙም የጥንታዊ ሕዝቦች  እና የአውሮፓውያን ባህል ተቀላቅሏል፣ እንዲሁም የሜቲስ ሰዎች ለዘለዓለም ይኖራሉ ነው።

ለ) በካናዳ በብዛት ከሚገኝ ዛፍ ላይ ያለ፣ ዛፉ ጣፋጭ መጠጥ የሚያመርት ሲሆን ቅጠሎቹም ቀለማቸውን ይቀያይራሉ። በካናዳ ባንዲራ ላይ ይታያሉ።

ሐ) የተቀደሰ የሚባል እና ከፈጣሪ ጋር ያለን ግንኙነት ማሳያ፣ የመጀመሪያ ዜጎች ምልክት ነው። በተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ ይጠቀሙታል።

መ) ለካናዳ ነጻነት ሕይወታቸውን የሰጡ ወታደሮችን ለማስታወስ የሚውል ምልክት።


ሠ) ቆዳው በአንድ ወቅት ለካናዳ ኢኮኖሚ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው።

ረ) የኢንዩት የድንጋይ ሥራ ሲሆን ለመረጃ ልውውጥ ያገለግላል። በአርክቲክ አካባቢ ኑሮን ለመግፋት የሚያገለግል እንዲሁም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል ነው።


መልሶች፤ 1 (ሐ)፤ 2 (ረ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ለ)፤ 5 (ሠ)፤ 6 (መ)

## 1.5 ወቅቶች

**መመሪያዎች፡** በካናዳ ስላሉ አራት ወቅቶች እና በየወቅቶቹ የአየር ጠባይ እንዴት እንደሚለወጥ ያንብቡ።



- በጣም ሞቃታማ (ከ33ዲግሪ-ሴንቲግሬድ በላይ)
- ሞቃታማ (ከ25ዲግሪ-ሴንቲግሬድ እስከ 32ዲግሪ-ሴንቲግሬድ)
- መካከለኛ (ከ19ዲግሪ-ሴንቲግሬድ እስከ 24ዲግሪ-ሴንቲግሬድ)
- ነፋሻማ (ከ6ዲግሪ-ሴንቲግሬድ እስከ 18ዲግሪ-ሴንቲግሬድ)
- ቀዝቃዛ (ከ-9ዲግሪ-ሴንቲግሬድ እስከ 5ዲግሪ-ሴንቲግሬድ)
- በጣም ቀዝቃዛ (ከ-19ዲግሪ-ሴንቲግሬድ እስከ -10ዲግሪ-ሴንቲግሬድ)
- እጅግ ከፍተኛ ቅዝቃዜ (ከ-20ዲግሪ-ሴንቲግሬድ በታች)



# 1.6 ለእያንዳንዱ ወቅት ተግባራት

በየአንዳንዱ ወቅት በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ወይም ተግባራት አሉ።

***መመሪያ፡*** የየወቅቱን እንቅስቃሴዎች ወይም ድርጊቶች ይመልከቱ። በወቅቶች እና በተግባራቱ መካከል በማስመር ያዛምዱ።




መልሶች፡ 1 (ሰ፣ሐ)፤ 2 (ሠ፣ለ)፤ 3 (ረ፣ሸ)፤ 4 (ሀ፣መ)




በርካታ ሃገር በቀል/ጥንታዊ ፈጠራዎች በቀደመው የካናድያን ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። አሁን ድረስ በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች በሁሉም ወቅቶች ከቤት ውጪ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ይከውናሉ።

## 1.7 ለክረምቱ ወቅት ዝግጁ ነዎት?

ካለው እጅግ ቀዝቃዛ ለሆነ የአየር ሁኔታ እንግዳ ስለሆኑ የካናዳ የክረምት ወቅት ለአዲስ መጪዎች እጅግ ያልተለመደ ሊሆን ይችላል። ለሰስ ያለ ነፋስ የአየር ሁኔታ እጅግ ቀዝቃዛ እንደሆነ እንዲሰማ ሊያደርግ ይችላል። በዚህ ወቅት ሙቀት ለማግኘት ልብስ በሚገባ መደራረብ ያስፈልጋል።

***መመሪያ፡*** በቅዝቃዜ ምክንያት አደጋ ላይ ሊወድቁ የሚችሉ የሰውነት ክፍሎችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ የሰውነት ክፍል እና እነዚህን ክፍሎች ከቅዝቃዜ ለመጠበቅ መጠቀም የሚያስፈልጉ ልብሶች መካከል መስመር በማስመር ያዛምዱ።




**በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች ዓመቱን ሙሉ ንቁ ከመሆናቸው በላይ ከቤት ውጪ በሆኑ በርካታ እንቅስቃሴዎች ይዝናናሉ። ስለዚህም በአግባቡ እና በስርዓቱ መልበስ አስፈላጊ ነው።**

መልሶች፦ 1 (ሠ)፤ 2 (ሀ)፤ 3 (ረ)፤ 4 (ለ)፤ 5 (መ)፤ 6 (ሐ)

# 1.8 የካናዳ ገጽታዎች

**መመሪያ፡** ሰዎቹን ይመልከቷቸው። ካናዳውያን ናቸው ብለው የሚገምቷቸው ሰዎች ምስል ፊት ባለው ሳጥን ውስጥ የ “✓” ምልክት ያስቀምጡ።


✓ 1.


2.


3.



4.


5.



6.


7.


8.


9.


10.


11.


12.

መልሶች፡ 1 (✓)፤ 2 (✓)፤ 3 (✓)፤ 4 (✓)፤ 5 (✓)፤ 6 (✓)፤ 7 (✓)፤ 8 (✓)፤ 9 (✓)፤ 10 (✓)፤ 11 (✓)፤ 12 (✓)


ምዕራፍ 1 - ስለ ካናዳ አጭር መግለጫ



አዲስ መጪዎች ችሎታቸውንም ወደ ካናዳ ይዘው ይመጣሉ። በማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ለካናዳ ስኬት አስተዋጾ አለው። ይሠራሉ፣ ግብር ይከፍላሉ፣ ጓደኝነት ይፈጥራሉ እንዲሁም በሚኖሩበት ኅብረሰተብ ውስጥ ተሳትፎ አላቸው።



በአገሪቱ ከአምስት ሰዎች መካከል አንዱ ከካናዳ ውጪ የተወለዱ ናቸው።




በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች ከሁሉም ሰው ጋር ያለ እድሜ፣ ጾታ፣ ዘር፣ የኑሮ ደረጃ፣ ትዳር ወይም የቤተሰብ ሁኔታ፣ የፍልሰት ሁኔታ፣ የአካል ብቃት ወይም ጉዳት አልያም በስርዓተ ጾታ አረዳድ ልዩነታቸው በመቻቻል እና በመከባበር እንዲኖሩ ይጠበቅባቸዋል።
ይህንንም በሚከተሉት መንገዶች ማድረግ ይቻላል፤



**1.** በንግግርዎ እና በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሌሎችን ማክበር



**2.** እርስዎ ከለመዱት የአኗኗር ዘዴ የተለየ ቢሆንም፣ ሰዎች እንደፈለጉ ኑሮአቸውን እንዲመሩ መብታቸውን ማክበር



**3.** ያለልዩነት እና ማግለል ሰዎች ሁሉ በፍትህ የሚስተናገዱበትን መንገድ ማጠናከር


**ትዕግስተኛ እና ከሁሉም ጋር ተግባቢ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ልዩነት ለመቀበል የሚያስችል አእምሮ ባለቤት መሆን በካናዳ ለመኖር የሚያደርጉትን የመላመድ ጥረት ያግዛል።**

## 1.9 ብዝኀነት

ካናዳ ብዝኀነትን የምታከብር እና ዋጋ የምትሰጥ ሀገር ናት። የካናዳ ሕግ ለሁሉም በእኩል ያገለግላል/ይተገበራል። በዚህ የመልመጃ መጽሐፍ ቀጣይ ገጾች ላይ በካናዳ ስላለው ብዝኀነት ያነብባሉ።



***መመሪያ:*** በካናዳ የጾታ ባህርያት፣ የስርዓተ ጾታ ምንነት፣ የስርዓተ ጾታ መገለጫ እንዲሁም የፆታዊ ፍላጎት ምርጫን እና መብትን በሚመለከት ያንብቡ።



### 1. የጾታ ባህርያት

ስንወለድ፣ በባዮሎጂያዊ አመላካቾቻችን መሠረት ጾታችን ይሰጠናል። በሕክምና ባለሞያዎች እንዲሁም በቤተሰቦቻችን ወንድ ♂ ወይም ሴት ♀ መሆናችንን ከአካላዊ መለያዎች በመነሳት ይነግሩናል። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ የሴትም የወንድም ጾታ ቅልቅል ○ ይዘው ይወለዳሉ። ሁላችንም የጾታ ባህርያት አሉን። እርስዎም ስለራስዎ ያስቡ።




### 2. የስርዓተ ጾታ ማንነት

ይህ ራሳችን የምንረዳው ሴት ♀ ፣ ወንድ ♂ ፣ ሁለቱንም ⚧ ወይም ከሁለቱም ያልሆነ ⊖ የሚለው ስሜት ነው። የስርዓተ ጾታ ማንነታችን ስንወለድ ከተሰጠን ጾታ ጋር ተመሳሳይ ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል። ሁላችንም የስርዓተ ጾታ ማንነት አለን። ማንም ሰው የእርስዎ ጾታ ይህ ነው ብሎ ሊነግረን አይችልም፣ እኛ ብቻ ነን የምናውቀው። የጾታ አረዳዳችን ሊለወጥ ይችላል። እርስዎም ስለራስዎ ያስቡ።



### 3. የስርዓተ ጾታ አገላለጽ


ይህ ጾታችንን እንዴት ነው የምንገልጸው የሚለው ነው። የጾታ አገላለጻችን ወንድ ♂ ፣ ሴት ♀ ፣ የሁለቱም ቅልቅል ⚥ ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል። የስርዓተ ጾታ ገለጻችን በልብስ ምርጫችን፣ በጸጉር አሠራራችን፣ በምንጠቀመው መዋቢያ ቁሳቁስ፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ ድምጽ ወይም ጸባይ እና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል። የምንጠቀመው ስም እና የስም ገላጮችም ጾታችንን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ናቸው። ጾታችንን የምንገልጽበት መንገድ ሊቀየር ይችላል። ሁላችንም ጾታችንን በተለያየ መንገድ እንገልጻለን። እርስዎም ጾታዎን እንዴት እንደሚገልጹ ያስቡ።



## 4. የጾታዊ ዝንባሌ/ፍላጎት አገላለጽ

ይህ ከሌሎች ጋር የሚኖረን አካላዊ፣ የፍቅር እንዲሁም የስሜት መሳሳብ ነው። ከእኛ የተለየ ጾታ ላለው፣ ለተመሳሳይ ጾታ፣ ከአንድ ጾታ በላይ ላለው ወይም ምንም ጾታ በሌለው ሰው ልንሳብ እንችላለን። ሁላችንም የጾታዊ ግንኙነት ገለጻ አለን። በዚህ ግንኙነት ላይ ያለን መረዳት ሊቀየር ይችላል። እርስዎም በማን እንደሚሳቡ ያስቡ።

በካናዳ ያለው ሕግ ሰዎች በጾታ ባህሪይ፣ በስርዓተ ጾታ ማንነት፣ በስርዓተ ጾታ አገላለጽ ወይም በፆታዊ ፍላጎት አረዳዳቸው ምክንያት ፍትሓዊ ባልሆነ መንገድ እንዳይስተናገዱ የሚጠብቃቸው ነው።



**ሀ)** ጋብቻ የሁሉም ሰው መብት ነው፣ ተመሳሳይም ሆነ ተቃራኒ ጾታ ለሆኑ።






**ለ)** ሰዎች ሲወለዱ ከተሰጣቸው ጾታ የተለየ ጾታ እንዳላቸው የሚሰማቸው ከሆነ፣ በሕጋዊ መንገድ ጾታቸውን መቀየር ይችላሉ። የካናዳ ፓስፖርት እና የማንነት ሰነዶች ሰዎች ጾታቸውን ‹ወንድ› ‹ሴት› ወይም ሌላ ጾታ (X) ብለው እንዲመርጡ ይፈቅዳል።



**ሐ)** በካናዳ ሰዎች የጾታ ፍላጎት ምርጫን፣ የስርዓተ ጾታ ማንነት እና የስርአተ ፆታን መገለጫን በፈለጉት መንገድ ሊገልጹ መብት አላቸው።

**አውሮፓውያን ሰፋሪዎች ወደ ካናዳ ከመምጣታቸው አስቀድሞ የተለያየ የስርዓተ ጾታ ማንነት ያላቸው ሕዝቦች በካናዳ ኖረዋል። በጥንታዊ ሕዝቦች ዘንድም አሁን ላይ ከሴትም ከወንድም ውጪ የሆነ ጾታ ያላቸው ሰዎች ‹ሁለት-መንፈስ› በሚል ይታወቃሉ። እነዚህም ለአንዳንድ ጥንታዊ ሕዝቦች መንፈሳዊ ትርጓሜ አላቸው።**




# 1.10 የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በካናዳ





አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እክል፣ የእንቅስቃሴ ገደብ እና እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ወሰን አለባቸው። አንዳንድ ጉዳቶች ሊታዩ የሚችሉ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ አይታዩም። አንድ ሰው ከአካል ጉዳት ጋር ሊወለድ ይችላል ወይም በተለያየ አደጋ፣ ሕመምና በእድሜ መግፋት ምክንያት አካል ጉዳት ሊደርስበት ይችላል።



በካናዳ ከአምስት ሰዎች መካከል አንድ ሰው ቢያንስ አንድ የአካል ጉዳት አለበት።



አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በካናዳ እንደማንኛውም ሰው ተመሳሳይ ጥራት ያለው አገልግሎትን በሁሉም ዘርፍ የማግኘት መብት አላቸው። እርስዎ ወይም ከቤተሰብ አባላት መካከል አካል ጉዳት ያለበት ሰው ካለ፣ የሚያስፈልግዎትን ነገር ሁሉ እርዳታ ለሚሰጥዎ በማሳወቅ መብቶችዎን ይጠቀሙ።



በካናዳ ያሉ የንግድ ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ድርጅቶች እና ማኅበረሰቦች የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ፍላጎቶች ለማሟላት እየሠሩ ይገኛሉ።


ይህም ተከታዮቹን ያካትታል፤





1. ተደራሽ የሆነ የሕዝብ ስፍራ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መፍጠር
2. አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ትምህርት እንዲያገኙ ለማስቻል ነጻ የትምህርት እድል ወይም የገንዘብ እርዳታ ማቅረብ





3. አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እንዲሠሩበት ለማስቻል የሥራ ቦታ/ስፍራ ሁኔታን መቀየር እና ምቹ ማድረግ
4. በሥራ፣ በትምህርት፣ በቤት እንዲሁም በየእለት ባለ የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ያለውን እኩል ያልሆነ መስተንግዶ መቃወም




**ለእርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ መካከል የአካል ጉዳት ላለበት ለእንክብካቤ የሚወጣው ወጪን በተመለከተ ሊያግዝዎት የሚችሉ አገልግሎት ሰጪዎች አሉ። ለበለጠ መረጃ ሊጋሾችዎን ወይም በመንግሥት የሚደጎሙ ድርጅቶችን ይጠይቁ።**




# 1.11 በካናዳ የአካል ጉዳት ካለባቸው ሰዎች ጋር መግባባት ወይም ትስስር መፍጠር

**መመሪያ፡** የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችን ትዕይንት ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ትዕይንት እና ዝርዝር ማብራሪያው መካከል መስመር በማስመር ያዛምዱ።



1.



2.



3.



4.



5.



6.

ሀ) አካል ጉዳት ካለበት ሰው ጋር መነጋገር ሲፈልጉ በሚያግዟቸው ሰዎች በኩል ሳይሆን በቀጥታ ከራሳቸው ጋር ይነጋገሩ።

ለ) አካል ጉዳት ያለበት ሰው የሆነን ሥራ መሥራት አይችልም ብለው አይገምቱ።

ሐ) አንድን አካል ጉዳት ያለበት ሰው ሲመለከቱ ግለሰቡን እንጂ ጉዳቱን አይመልከቱ።


መ) ፈቃዳቸውን ሳያገኙ አካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎችንም ሆነ መርጃ መሣሪያቸውን አይንኩ።

ሠ) አካል ጉዳት ያለበትን ሰው ሳይጠይቁ ከማገዝ ይልቅ እርዳታዎን ይፈልግ እንደሆነ ይጠይቁ።


ረ) አካል ጉዳት ያለበትን ሰው ‹ጤናማ ያልሆነ› ብለው አይጥሩ።

መልሶች፡ 1 (ሐ)፡፡ 2 (ረ)፡፡ 3 (ሀ)፡፡ 4 (ለ)፡፡ 5 (ሠ)፡፡ 6 (መ)

# 1.12 አድሎ በካናዳ





አድሎ ሰዎችን ሌሎች በነጻነት የሚያደርጉት ነገር እንዳያደርጉ ይገድባቸዋል። አንድን ሰው ላይ አድሎ መፈጸም ማለት፣ ሰዎችን ከሌሎች ነጥለው ያለ እኩልነት በአሉታዊ መንገድ ማስተናገድ/ማየት ነው።



ነዋሪነታቸው በካናዳ የሆነ ሰዎች በካናዳ አድሎ እንዳለ ሊያውቁ ይችላሉ። ካናዳ ብዝኀ ባህል ያለባት እና ሁሉንም ተቀባይ ሀገር ብትሆንም፣ ከአምስት ሰዎች አንድ ሰው ይህ መገለል ወይም አድሎ ይደርስበታል።

አድሎ በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። አንዳንዴ ለመለየት ቀላል ነው። በሌላ ጊዜ ደግሞ ድብቅ ይሆናል።

አድሎ በየእለቱ የሚያጋጥም ክስተት ሊሆን ይችላል፣ ይህም ቀላል የሚመስል ትንኮሳ ወይም ዘለፋ/ስድብ የሚያካትት ይሆናል። አንዳንዶቹ ስድቦች ከታች የተዘረዘሩትን ይመስላሉ፤




**1.** ንቁ እና ጎበዝ እንደሆነ ሰው አለመታሰብ




**2.** በጥርጣሬ መታየት



**3.** የአገልግሎት ሰጪ ሠራተኛ እንደሆኑ መታሰብ





**4.** አገልግሎት ለማግኘት በጠየቁ ጊዜ በአግባቡ አለመስተናገድ



**በካናዳ ሕግ ሌሎች ሰዎችን በማንነታቸው ምክንያት በመጥፎ ሁኔታ ወይም ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ማስተናገድ ሕገወጥነት ነው።**




**መመሪያ፡** በካናዳ ያሉ የአድሎ ምሳሌዎችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ምሳሌ እና የአድሎ ዓይነቶች መካከል በማስመር ያዛምዱ።



1. «ከየት አገር ነው የመጣኸው/ሽው? ወደ መጣህበት/ሽበት ተመለስ/ሺ!»



2. «የእኛ ቡድን ተጫዋቾች ራሳቸውን እንዲሸፍኑ አይፈቀድም። ስለዚህ መጫወት አትችልም/ይም»



3. «አሳንሰሩ ተሰብሯል»



ሀ) አካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ አድሎ




ለ) ብሔርን መሠረት ያደረገ አድሎ



ሐ) ሐይማኖትን መሠረት ያደረገ አድሎ

መልሶች፡ 1 (ለ)፤ 2 (ሐ)፤ 3 (ሀ)



4\. «ሁለት ወንዶች በሕዝብ ፊት እጅ ለእጅ ተያይዘዋል! ያሳፍራል!»




5\. «ሴቶች ይህን ሥራ ሊሠሩት አይችሉም»



6\. «እንደ አንተ/ቺ ያለ ሰው እዚህ እቃ መግዛት አይችልም»



7\. «እንደ እነርሱ ዓይነት ሰዎች በዚህ አካባቢ መኖር ከጀመሩ የአካባቢው ደኅንነት ይታወካል»




መ) የጾታ ማንነትን መሠረት ያደረገ አድሎ



ሠ) ጾታን መሠረት ያደረገ አድሎ



ረ) የፍቅር ምርጫን (የጾታዊ ግንኙነት አገላለጽን) መሠረት ያደረገ አድሎ



ሰ) ዘርን መሠረት ያደረገ አድሎ

መልሶች፡ 4 (ረ)፤ 5 (ሠ)፤ 6 (መ)፤ 7 (ሰ)

## 1.13 በካናዳ ኢድሎን መቋቋም መቻል

በካናዳ፣ አግላይ እና የሚያዳላ ሆኖ የተሰማዎ አሠራር ወይም ሁኔታ ካለ፣ በአግባቡ የመጠየቅ መብት አለዎት።


***መመሪያ:*** በካናዳ እንዲህ ያሉ ክስተቶችን እንዴት መያዝ/መቋቋም እንደሚገባ የሚረዳ ምክረ ሐሳብ ከታች ይመልከቱ። እርስዎም በካናዳ ሲኖሩ ሊያደርጓቸው የሚችሉት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያኑሩ።






☐ **1.** ስለራስ ጥንካሬን ማሰብ።

☐ **2.** የሚያምኑትን ሰው ማናገር።






☐ **3.** ከተቻለ የማግለል ወይም የአድልዎ ተግባር የሚፈጽምን ሰው እንዲተው መንገር።


☐ **4.** እንዲህ ያለ ነገር ሲያጋጥምዎ፣ ስም፣ ቀን፣ ቦታ እና ሰዓትን ጨምሮ የክስተቱን ዝርዝር ለመጻፍ ይሞክሩ። ይህም የተለመደ የማግለል አካሄድ መኖሩን ለማሳየት ይረዳል።





☐ **5.** ከአእምሮ ጤና ባለሞያዎች ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ።.

☐ **6.** አጋዥ ካስፈለገ ድንገተኛ ባልሆነ በመደበኛ የፖሊስ ስልክ መደወል ይችላሉ፡፡






☐ **7.** በሥራ ቦታ ላይም ትንኮሳ ከገጠምዎ፣ ቀጣሪዎ ጸረ ትንኮሳ ህገ ደንብ ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የህገ ደንቡን መመሪያ ይከተሉ።

☐ **8.** አደጋ ውስጥ ከሆኑ፣ 911 ይደውሉ

**አድሎ አንዳንዴ ወደ ብጥብጥ ሊያመራ ይችላል። በካናዳ ከፍተኛ እና ወደ ብጥብጥ የሚያደርስ አድሎ የተለመደ አይደለም። እንደዚህ አይነት ብጥብጥ ከባድ የሆነ የሕግ ጥሰት ነው።**

# 1.14 በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች የሚያደርጓቸው ነገሮች

በካናዳ ሕዝብ በሚንቀሳቀስባቸው ቦታዎች አንዳንድ ሰዎች ለየት ያለ የሚመስል እና እርስዎ ከመጡበት አካባቢ ያለመዱትን እንቅስቃሴዎች ሲያደርጉ ሊመለከቱ ይችላሉ።


**መመሪያ:** በካናዳ ያለውን የሕዝብ የሆኑ የተለመዱ ጸባዮችን ይመልከቱ። አዲስ የሆነብዎትን ወይም ያልተለመደ የሚሉት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያድርጉ።




☐ **1.** መሰለፍ




☐ **2.** የሚሳሳሙ ጥንዶች (ተመሳሳይ ጾታ ያላቸውን ጨምሮ)




☐ **3.** መተያየት



☐ **4.** የማያውቋትን ሰው ሰላም ማለት ወይም በፈገግታ መመልከት




☐ **5.** የሐይማኖት መገለጫ አልባሳትን ወይም ምልክቶችን መልበስ



☐ **6.** ቁምጣና ሙሉ እጅ የሌላቸው ሸሚዞችን መልበስ




☐ **7.** ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ሕጻን ልጅን ጡት ማጥባት



☐ **8.** ዶድራንት መጠቀም

**በካናዳ የሕዝብ መንቀሳቀሻ በሆኑ አካባቢዎች እና መንገዶች ላይ ቆሻሻ መጣል፣ መትፋት፣ መሽናት ወይም አፍና አፍንጫን ሳይሸፍኑ ማስነጠስ እና ማሳል ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት ናቸው።**



## 1.15 ሕጎች በካናዳ

በካናዳ ሕጎች ሦስት ደረጃ አሏቸው



1. **የፌዴራል ሕጎች**
   ይህ በካናዳ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የሚሠራ ነው። ከዚህም ለምሳሌ የፍልሰት እንዲሁም የገቢ ግብር ሕግ ተጠቃሽ ናቸው።




2. **የግዛት እና ክልላዊ ሕጎች**
   እነዚህ ሕጎች እንደየ ግዛት እና ክልሉ የተለያዩ ናቸው። ለምሳሌ የቤት፣ ጤና፣ የትምህርት እና የቤተሰብ ሕጎችን መጥቀስ ይቻላል።




3. **የማዘጋጃ ቤት ሕጎች**
   እነዚህ ሕጎች በተወሰኑ ከተማዎች የሚሠሩ ናቸው። እነዚህም ለምሳሌ የድምጽ፣ የሲጋራ ማጨስ፣ የቆሻሻ እና የመኪና ማቆሚያ ሕጎች ናቸው።



ሀ) በካናዳ ሕግ ፊት አንድ ተጠርጣሪ ወንጀለኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹህ ሰው እንደሆነ ይቆጠራል።



ለ) በካናዳ ያለ ፖሊስ ሁሉንም እኩል ማስተናገድ አለበት። ፖሊሶች በአደጋ ጊዜ እርዳታ ሊሰጡ ይችላሉ።



ሐ) ፖሊሶች በሁሉም ጾታዎች ይገኛሉ።



መ) ፖሊስ የማኅበረሰብን ደኅንነት የመጠበቅ፣ ወንጀሎችን የመመርመር እንዲሁም በወንጀል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች የመርዳት ሥራን ይሠራል። ሰዎችን ሊያስሩ እና በጣሱት ሕግ ምክንያት ለፍርድ ሊያቀርቧቸው ይችላሉ።

**ህጎችን ከጣሱ፤ የሚያመጡትን ውጤት የመረዳት እና የማወቅ ኃላፊነት አለብዎት።**

# 1.16 በካናዳ ሕገወጥ የሆነ

***መመሪያ:*** በካናዳ ሕገወጥ የሆኑ ተግባራትን ይመልከቱ። የተግባራቱ ውጤት ወይም የሚከተለው ቅጣት የገንዘብ ከሆነ የ "$" ምልክት በሳጥኑ ውስጥ ያስቀምጡ፣ ውጤቱ እስር ቤት መግባት ከሆነ ደግሞ የ "Ⅲ" ምልክትን ያስቀምጡ።



[Ⅲ] **1.** ያለፈቃድ መሳሪያ መያዝ



[ ] **2.** የተሽከርካሪ ቀበቶ ሳያስሩ መኪና ማሽከርከር



[ ] **3.** በሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ሲጋራ ማጨስ



[ ] **4.** በተከፋፈለ ሐሳብ እና ስሜት ውስጥ ሆኖ መኪና ማሽከርከር



[ ] **5.** ፈቃድ ሳያገኙ አሳ ማስገር ወይም ማደን



[ ] **6.** ያልተፈቀዱ የጾታዊ ንክኪዎች ወይም ለከፋ



[ ] **7.** የቤተሰብ አባል የሆነን ሰው ጨምሮ በማንኛውም ሰው ላይ አካላዊ ጥቃት መፈጸም

መልሶች፡ 1 (Ⅲ)፤ 2 ($)፤ 3 ($)፤ 4 ($)፤ 5 ($)፤ 6 ($ ወይም Ⅲ)፤ 7 (Ⅲ)






8. የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ኃላፊን በገንዘብ መደለል



9. ሕገወጥ የሆኑ አደገኛ ዕጾችን መሸጥ፣ መጠቀም ወይም ማዘዋወር




10. በአንድ ጊዜ ከአንድ ሰው በላይ ጋር ትዳር መመሥረት



11. የሕጻናት የእርቃን ፎቶ ማንሳት፣ ማጋራትም ሆነ መያዝ



12. በተለያየ ነገሮች ተጽእኖ ስር ሆኖ መኪና ማሽከርከር (ለምሳሌ አልኮል መጠጥ፣ አደገኛ ዕጽ እና የተለያዩ መድኃኒቶች)



13. ሰዎችን ለጋብቻ ማስገደድ



14. ከሕጻናት ጋር ወሲብ መፈጸም



15. የሴቶች ግርዛት

**ከእነዚህ በካናዳ ካሉ ሕጎች መካከል አዲስ የሆነብዎ የትኛው ነው?**


መልሶች፡ 8 (ሀ)፤ 9 (ሀ)፤ 10 (ሀ)፤ 11 (ሀ)፤ 12 (ሀ)፤ 13 (ሀ)፤ 14 (ሀ)፤ 15 (ሀ)

ጨዋታ 1 - ህግ እና ስርዓትን ማክበር

# 1.17 በካናዳ ሕጋዊ የሆነ

በካናዳ ያሉ ሰዎች እርስዎ ከኖሩበት አንጻር ለየት ያለ ነጻነት ሊኖራቸው ይችላል። በካናዳ ስለኖሩ ብቻ በእነዚህ መስማማት ወይም እነዚህን ተግባራት መፈጸም አይጠበቅብዎትም። ሆኖም ግን ባይስማሙባቸውም እንኳን፣ እነዚህን ነጻነቶች ሰዎች እንዲጠቀሙባቸው መብት ያላቸው መሆኑን እንዲያከብሩ ይጠበቃል።





1. ከ18 ዓመት በላይ ሲሆኑ ማንን እና መቼ እንደሚያገቡ መወሰን፣ ተመሳሳይ ጾታ ቢሆን እንኳ



2. ጽንስን ማቋረጥ (ውርጃ)



3. የካናቢስ ምርቶችን መጠቀም (ለአዋቂዎች ብቻ)



4. አልኮል መጠቀም (ለአዋቂዎች ብቻ)



5. ሊድን የማይችል እና ቀስ በቀስ ለሞት የሚዳርግ ሕመም ያለበት ሰው በሐኪሞች እርዳታ እስትንፋሱ እንዲቋረጥ ማድረግ (በዶክተር የታገዘ ሞት)



**6.** *መንግስትን በሠላማዊ መንገድ መቃወም*



**7.** *ልጆች መውለድ/ማሳደግ፣ ያላገቡ ሰዎችም ሆኑ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ጥንዶች*




**8.** *በማንኛውም ሐይማኖት መኖር ወይም ሐይማኖት የለሽ መሆን*





**9.** *በሕጋዊ መንገድ ጾታን መቀየር (ወንድ ♂ ፣ ሴት ♀ ሌላ ጾታ (✕)*

**በካናዳ አንድ ሰው አዋቂ የሚባለው 18 ወይም 19 ዓመት ጀምሮ ነው። ይህም ከአንድ ግዝት እና ክልል ወደ ሌላው የተለያየ ሊሆን ይችላል።**



# 1.18 የቤተሰብ ሁኔታ

በካናዳ የሚገኙ ቤተሰቦች ሁኔታ እርስዎ ከኖሩበት እና ከለመዱት የተለየ ሊሆን ይችላል። እንደየቤተሰቡም የየአንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ድርሻ ይለያያል።






1. ኑሮን ወደ አዲስ ሀገር መቀየር ብዙ ጊዜ ቤተሰብ ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል። ምክንያቱ ደግሞ የቤተሰብ አባላትን ድርሻ እና ኃላፊነት ስለሚቀያይር ነው። እነዚህ ለውጦች ጭንቀት ሊፈጥሩ ይችላሉ።



2. እነዚህን ለውጦች በጥሩ መንገድ ለማስተናገድ የሚያስችሉ መንገዶች አሉ። እነዚህም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያለ የቤተሰብ አባልን መደገፍ እና ማናገር የመሳሰሉ ናቸው።



3. አንዳንድ ወደ ካናዳ አዲስ መጪ ወላጆች በካናዳ መኖር ፈታኝ እንደሆነባቸው ይናገራሉ። ከእነርሱ ይልቅ ልጆቻቸው በካናዳ ካለው አዲስ ባህል ጋር በቶሎ ይላመዳሉ። አንዳንዴም ወላጆች ልጆቻቸው በሚያደርጓቸው ነገሮች ደስተኛ ላይሆኑ ይችላሉ፣ ለምሳሌ አለባበሳቸው፣ አነጋገር ወይም አኳኋናቸውን በሚመለከት።

**ምንም ዓይነት አስጨናቂ ነገር ቢኖር እንኳን፣ በካናዳ የቤተሰብ ውስጥ ብጥብጥ/ሁከት ሕገወጥ እንደሆነ ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ያንብቡ፤**

**መመሪያ:** ተከታዮቹን የቤተሰብ ውስጥ ብጥብጥ/ሁከት ምሳሌዎችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ምሳሌ እና በዝረዝሩ መካከል መስመር በማስመር ያዛምዱ።



1.



2.



3.



4.



5.



6.

ሀ) የልጆችን ወይም በእድሜ የገፉ ትልቅ ሰዎችን መሠረታዊ ፍላጎቶች መዘንጋት

ለ) የቤተሰብ አባላትን ሰነዶች መቆጣጠር ወይም ገንዘባቸውን ያለአግባብ መጠቀም

ሐ) የቤተሰብ አባላትን መምታት


መ) የቤተሰብ ክብርን ለመጠበቅ በሚል የቤተሰብ አባልን መግደል

ሠ) ቃላታዊ እና/ወይም ስሜታዊ ጥቃት መፈጸም

ረ) የቤተሰብ አባል ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ ማስገደድ

መልሶች: 1 (ሐ)፣ 2 (ረ)፣ 3 (ለ)፣ 4 (ሠ)፣ 5 (ሀ)፣ 6 (መ)

አንድ ሰው በትዳር ውስጥ መቆየት አልፈልግም ካለ፣ ከሁለቱ አንዳቸው የፍቺ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። በካናዳ ፍቺን ማጽደቅ የሚችለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው። ፍቺ ከተፈጸመ በኋላም ሁለቱም ወላጆች ልጆቻቸውን በገንዘብ መደገፍ ያለባቸው ሲሆን የልጆች እንክብካቤን በሚመለከትም ስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው።




**በካናዳ ያለዎትን የስደት ሁኔታ ለማቆየት ሲሉ አደገኛ በሆነ ግንኙነት ውስጥ መቆየት የለብዎትም። የቋሚ ነዋሪነት ሁኔታዎትን ለመጠበቅ ሲሉም ከድጋፍ አድራጊዎ ጋር መኖር የለብዎትም (የትዳር ጓደኛም/አጋርን ጨምሮ) ።**

በማንኛውም መንገድ ማስፈራሪያ ወይም ጉዳት የሚደርስብዎት ከሆነ አልያም ግጭትን እየሸሹ ካሉ፣ ተከታዮቹን ማድረግ ይችላሉ፤




1. በድንገተኛ ፖሊስ ጋር በ911 መደወል
2. ለማኅበራዊና የጤና አገልግሎት 211 ላይ መደወል ወይም 211.ca ድረገጽ መጎብኘት



3. www.sheltersafe.ca ድረገጽ ላይ መጠለያ መፈለግ



4. ከአማካሪዎች ጋር በመነጋገር ምክር መውሰድ

# 1.19 በካናዳ ልጆችን ስርዓት ስለማስያዝ



በካናዳ ያለው ሕግ ልጆችን ችላ ከመባል እና ከጥቃት ይጠብቃል። ሁሉም ሰው በልጆች ላይ የሚደርስን ጥቃት ከተመለከተ የመጠቆም ኃላፊነት አለበት። እንዲሁም ደግሞ ልጆችን ለመጠበቅ እና ቤተሰብም ሳይለያይ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያግዝ ድጋፍ ለቤተሰቦች ይሰጣል። ያም ሆኖ መንግስት ልጆችን ደኅንነት ከሌለበት ቤት ውስጥ እንዲወስድ ሕግ ይፈቅድለታል።

ተከታዮቹ ልጆችን ስርዓት ማስያዣ መንገዶች በካናዳ ፍጹም ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው።



1. መግረፍ፣ መደብደብ፣ በእርግጫም ሆነ በቡጢ መምታት



2. ለመጉዳት ወይም ለመግደል ማስፈራራት




3. ምግብ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን መከልከል



4. ፍቅር እና እንክብካቤን መንፈግ

በአንጻሩ ወላጆች ሊያደርጓቸው የሚችሉትን ይመልከቱ።



1. ሲበሳጩ ለመረጋጋት ጊዜ መውሰድ



2. በልጆች እና በአዋቂዎ መካከል ያለውን የብስለት፣ የእድሜ፣ የእውቀት፣ የጥንካሬ እና የልምድ ልዩነት ማስታወስ/ማስተዋል



**3.** ልጅ ብቻውን ሆኖ ለአንድ ሁለት ደቂቃዎች/ ለአፍታ የሚረጋጋበትን እድል መስጠት




**4.** የልጅ ትኩረት ወደ ሌላ ጉዳይ/ እንቅስቃሴ እንዲቀየር ማድረግ




**5.** ጥሩ ፀባይ ሲያሳይ መሸለም



**6.** እኩይ ምግባር የሚያስከትለውን ውጤት በግልጽ ማሳወቅ



**7.** እንዲህ ያለ ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም ከሌሎች ወላጆች ጋር መገናኘት እና መመካከር



**8.** ሌላ ልጆችን ስርዓት ማስያዣ መንገዶችን በሚመለከት ከአማካሪዎች ጋር ተገናኝቶ መነጋገር



**9.** የተለዩ ጥቅሞችን መከልከል ወይም/እና ገደብ ማድረግ



**ከተዘረዘሩት መካከል በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ይሠራል የሚሉት ልጆችን ስርዓት እንዲይዙ ማድረጊያ መንገድ የትኛው ነው?**

# ምዕራፍ 2
# ጉዞ



# ምዕራፍ 2
# ጉዞ



## 2.1 የመኖሪያ ስፍራን መቀየር፤ ተስፋ እና ስጋቱ

ከነበሩበት አገር ቀይረው ኑሮዋቸውን ወደ ካናዳ ሊያደረጉ ያሉ ሁለት ሰዎችን ይተዋወቁ። ወደ ካናዳ ስትዘዋወሩ ሕይወታችሁ እንዴት ሊቀየር ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። እያንዳንዳቸውም በካናዳ በሚኖራቸው አዲስ ሕይወት ተስፋ የሚያደርጉትን እና የሚያስጋቸውን አስረድተዋል።

**መመሪያ:** ታሪኮቹን ያንብቡ። እርስዎም በካናዳ መኖርን በሚመለከት ካላችሁ ተስፋ እና ስጋት ጋር የሚመሳሰሉት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ“ ✓ ” ምልክት ያድርጉ፤



**1.** ________________________ን ይተዋወቁት
24 ዓመቱ ነው። ትምህርቱን ሳያጠናቅቅ ነው ሀገሩን ለቅቆ የወጣው። ላለፉት ሦስት ዓመታትም ከትውልድ ሀገሩ ውጪ በራሱ እንደ ስደተኛ ሲኖር ቆይቷል።

በካናዳ እንዲኖር ፈቃድ/ተቀባይነት ሲያገኝ፣ ተከታዩን ዝርዝር አዘጋጀ፤

ተስፋ ያደረገው፤




☐ ሀ) የእንግሊዘኛ ወይም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታውን ማሻሻል



☐ ለ) ደኅንነት እና ሰላም ባለበት ሀገር መኖር




☐ ሐ) ትምህርቱን መቀጠል እና ራሱን ማኖር የሚያስችለው ሥራ ማግኘት


ስጋቶቹ፤



☐ ሀ) ካናዳ ውስጥ ብቻውን መሆን።



☐ ለ) ረጅሙ እና ቀዝቃዛው የክረምት ወቅት



☐ ሐ) ከዚህ ቀደም የተማረው ትምህርት በካናዳ ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑ እና ከእንደገና መጀመር ያለበት መሆኑ።

**2.** ______________________________ን ይተዋወቋት




45 ዓመቷ ነው። የሕይወት አጋሯ በሞት ተለይቷታል። ላለፉት 15 ዓመታት በስደተኛ መጠለያ ነው የኖረችው፣ መደበኛ ትምህርትም አልተከታተለችም። ወደ ካናዳ ለኑሮ ያቀናችው ከሁለት ልጆቿ ጋር ነው።

በካናዳ ኑሮዋን እንድታደርግ ተቀባይነት ስታገኝ፤ ተከታዩን ዝርዝር አዘጋጀች፤


ተስፋ ያደረገችው፤



☐ **ሀ)** ለእርሷ እና ለልጆቿ የተሻለ ወደፊት እንደሚኖር




☐ **ለ)** በሰላማዊ ስፍራ መኖር



☐ **ሐ)** በምትገባበት ማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት እና ጓደኛ ማግኘት

ስጋቶቿ፤




☐ **ሀ)** በእንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ ቋንቋ መግባባት አስቸጋሪ ሊሆንባት መቻሉ



☐ **ለ)** ከትውልድ ሀገሯ እና ከዘመዶቿ በእጅጉ መራቋ



☐ **ሐ)** ልጆቿን በአዲስ ባህልና ስርዓት ውስጥ ማሳደጉ

ኑሮዎን በካናዳ ለማድረግ በሚመጡ ጊዜ የተደበላለቀ ስሜት መኖሩ የተለመደ ነው።

እርስዎም ያለዎትን ተስፋ እና ስጋት ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ ይጻፉ።

______________________________________________________________


______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## 2.2 ጉዞዎ



ወደ ካናዳ የሚያደርጉት ጉዞ ረጅም እና አድካሚ ሊሆን ይችላል። ከሚኖሩበት ሀገር ወደ ካናዳ ቀጥታ በረራ ላይኖር ይችላል። የመጨረሻ ማረፊያዎ ለመድረስ ከአንድ በላይ በረራ መጠቀም ይኖርብዎታል። ጉዞውም ብዙ ሰዓታት ወይም የተወሰኑ ቀናት ሊወስድ መቻሉ የተለመደ ነው።


**መመሪያ:** የዓለምን ካርታ ይመልከቱ። አሁን የሚኖሩበትን ቦታ ይፈልጉ እና በላዩ ላይ የ "✕" ምልክት ያድርጉበት። ካናዳ በማፕል ቅጠል ምልክት ተደርጎባታል። በሁለቱ መዳረሻዎች መካከል የሚያገናኝ መስመር ያስምሩ።



## 2.3 ወደ ካናዳ የሚያደርጉት ጉዞ


ወደ ካናዳ ለሚያደርጉት ጉዞ ተከታዮቹ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

**መመሪያ:** ወደ ካናዳ የሚያደርጉትን ጉዞ በሚመለከት ተከታዮችን መረጃዎች ይሙሉ። ለጉዞ ከመነሳትዎ ጥቂት ቀናት በፊት ድረስ እነዚህን መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ላያውቁ ይችላሉ፤ ይህም የተለመደ ነው። በቀረቡት ባዶ ቦታዎች ላይ መረጃዎቹን ሙሉ ወይም ከጉዞዎ ጋር በተገናኘ የተቀመጡ መልሶች ላይ "◯" ያክብቡ።



**1.** የሚነሱበት አየር መንገድ የሚከተለው ነው:


______________________________



**2.** ወደ ሌላ በረራ ለመሻገር የሚያርፉበት አየር መንገድ የሚከተለው ነው:

_______________________________________


_______________________________________



**3.** ከሚኖሩበት ሀገር እስከ ካናዳ ድረስ የሚደረግ ጉዞ የሚከተለውን ያክል ሰዓት ይፈጃል:

_______________________________________


_______________________________________



**4.** የመጀመሪያው በካናዳ የሚያርፉበት አየር መንገድ:

**ሀ)** ቶሮንቶ **ሐ)** ቫንኮቨር

**ለ)** ሞንትሪያል **መ)** ካልጋሪ



**5.** የመጨረሻ የሚያርፉበት አየር መንገድ የሚከተለው ነው:

_______________________________________


_______________________________________



**6.** በካናዳ የሚኖሩበት አካባቢ ወይም ከተማ የሚከተለው ነው:

_______________________________________

_______________________________________



**7.** ካናዳ ሲደርሱ ከአየር መንገዱ ወደሚኖሩበት ከተማ/አካባቢ የሚወስድዎ የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት:

**ሀ)** አውሮፕላን

**ለ)** የከተማ አውቶቢስ

**ሐ)** የግል መኪና ወይም ታክሲ


## 2.4 የኢሚግሬሽን ብድርዎ

በዚህ የኢሚግሬሽን የብድር አገልግሎት ፕሮግራም፣ የካናዳ መንግሥት በእርስዎ ስም የጉዞዎን ወጪ በሙሉ ይሸፍናል። ይህንንም ብድር እንዲመልሱ ይጠበቃል።






1. ለጉዞ ከመነሳትዎ በፊት የብድር ሰነድ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ይህም የጉዞ ወጪን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ያለው ነው። ይህም ካናዳ ከደረሱ በኋላ የሚከፍሉት ብድር ነው። እነዚህ ወረቀቶችም እንደ ሕጋዊ ሰነድ ይቆጠራሉ።



2. በአጠቃላይ ይህ ብድር ለጉዞ ከሚነሱበት ቦታ ጀምሮ በካናዳ የመጨረሻ መዳረሻዎ እስኪደርሱ ድረስ ያለውን ወጪ የሚሸፍን ነው።




3. ይህን ብድር መክፈል የሚጀምሩት ካናዳ ከደረሱ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው።




4. ብድሩ ከወለድ ነጻ ነው።



5. ብደሩን መክፈል የሚጀምሩበትን ጊዜ፣ ከፍሎ ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እና እንዴት እንደሚከፈል ዝርዝሩን በተመለከተ የሚያስረዳ መግለጫ መንግስት ይልክልዎታል። ይህን ብድር በሚመለከትም ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ቢኖርዎ፣ እባክዎ በሥልክ ቁጥር 1-800-667-7301 ይደውሉ ወይም በኢሜይል አድራሻ collection@cic.gc.ca መልዕክት ይላኩ፤ በጉዳዩም የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ይህንን ያንብቡ፣



6. ብድሩን ለመክፈል ችግር ቢገጥምዎ የካናዳን መንግስት ማሳወቅ አለብዎት። አስፈላጊ ከሆነ የወርሃዊ ክፍያዎ መጠን ለመቀነስ የሚያስችል ማስተካከያ ይደረጋል።

# 2.5 የሻንጣ ዓይነቶች



1. **የእጅ ሻንጣ**
   በመጠኑ አነስተኛ ነው። ተሳፋሪዎች አውሮፕላን ውስጥ ይዘውት ሊገቡ ይችላሉ። ይህም በአውሮፕላኑ ካለው መቀመጫ ወንበር ስር ወይም ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ሊገባ የሚችል መሆን አለበት።



2. **ተለይቶ የሚጫን ሻንጣ**
   ይህ በአብዛኛው ተሳፋሪ ሊይዘው የሚችለው ትልቁ ሻንጣ ነው። አየር መንገዱ እነዚህን ሻንጣዎች ለብቻ ባዘጋጀው በአውሮፕላኑ መጋዘን/ማስቀመጫ ቦታ ያስቀምጣል። ተሳፋሪዎች ሻንጣዎቻቸውን ለአየር መንገዱ ሲሰጡ በምላሹ የሚቀበሉት ደረሰኝ አለ። ይህንንም ደረሰኝ በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል፣ ሻንጣቸው ቢጠፋባቸው የሚጠይቁት ደረሱኝን አቅርበው ስለሆነ። በረራው ሲጠናቀቅም ተሳፋሪዎች ሻንጣቸውን ይረከባሉ።





3. **የግል ዕቃዎች**
   እነዚህ ትንንሽ እቃዎች ሲሆኑ በቦርሳ ውስጥ ያለ የላፕቶፕ ኮምፒዩተር፣ የስራ ሻንጣ፣ እና የእጅ ቦርሳን ያጠቃልላል።

**ተለይተው የሚጫኑ ሻንጣዎች ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ መጠን፣ ቅርጽ እና ቀለም አላቸው። የራስዎን ቦርሳ መለየት መቻል አለብዎት። በሻንጣዎችዎ ላይ ሙሉ ስምዎን ይጻፉ። በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችልዎም በሻንጣው ላይ መለያ ምልክት ያኑሩ።**



# 2.6 የሻንጣ ገደቦች

እያንዳንዱ አየር መንገድ የየራሱ የሻንጣ መጠን ወሰን አለው። ስለዚሁ የሻንጣ መጠን ወሰን/ገደብን በተመለከተ የጉዞ ዝርዝር መግለጫን ይመልከቱ፣ አልያም የዓለማቀፉ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) ሠራተኞችን ይጠይቁ። እነዚህ ገደቦች ተከታዮቹን ይወስናሉ፤










1. የሚይዙት ማንኛውም ሻንጣ ከፍተኛ መጠን በሴንቲሜትር፤ ስፋት፣ ቁመት፣ ከፍታ እና ወርዱን በመለካት መጠኑን ሊያገኙ ይችላሉ።
2. የእያንዳንዱ ሻንጣ ክብደት መጠን፤ በኪሎግራም ሚዛን በመጠቀም እያንዳንዱን ሻንጣ መመዘን ይጠበቅብዎታል።
3. አንድ ግለሰብ ሊይዛቸው የሚችላቸው ሻንጣዎች ብዛት፤ እድሜን መሠረት አድርጎ ነው።

***መመሪያ:*** በቀረበው ባዶ ቦታ ላይ ለጉዞዎ የተቀመጠውን የሻንጣ ገደብ ይጻፉ።





1. **ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተሳፋሪዎች** እድሜው ከሁለት ዓመት በላይ የሆነ እያንዳንዱ ተሳፋሪ ከየአንዳንዱ የሻንጣ ዓይነት ስንት ይዞ እንዲገባ ይፈቀድለታል?

_______________


_______________

2. **ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ተሳፋሪዎች** እድሜው ከሁለት ዓመት በታች የሆነ እያንዳንዱ ተሳፋሪ ከየአንዳንዱ የሻንጣ ዓይነት ስንት ይዞ እንዲገባ ይፈቀድለታል?

_______________

_______________

3. የእያንዳንዱ ሻንጣ ከፍተኛ የቁመት እና ወርድ እንዲሁም የክብደት መጠን ምን ያህል ነው?



_______________

_______________

_______________

እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት በአውሮፕላን ውስጥ ለራሳቸው መቀመጫ ወንበር አይኖራቸውም። ለዚህም ነው የተለያየ ዓይነት የሻንጣ ፈቃድ ያላቸው።



**በአየር መንገዱ ያለውን የሻንጣ መጠን ገደብ ይከተሉ። ይህን ካላደረጉ ግን አየር መንገዱ ሻንጣዎን ላይቀበል ይችላል አልያም ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፍሉ ግድ ይልዎታል። ይህ ክፍያም ብዙ ጊዜ ከፍተኛ ነው።**

## 2.7 በየትኛው ሻንጣ ምን ይቀመጣል?

***መመሪያ:*** እቃዎቹን ይመልከቱ።

**በእጅ ቦርሳ** ውስጥ ሊቀመጡ የሚችሉት እቃዎች ላይ የ "◯" ምልክት ያኑሩ።



**ተለይቶ በሚጫን ሻንጣ ሊቀመጡ የሚችሉት እቃዎች** ላይ የ "□" ምልክት ያኑሩ።




በእጅ ሊያዙ የሚችሉ **የግል እቃዎች** ላይ የ "△" ምልክት ያኑሩ።




የትኛውን እቃ የትኛው ሻንጣ ውስጥ ላስቀምጥ የሚለው ላይ ሲወስኑ፣ የየሻንጣዎቹን የቁመት እና ወርድ እንዲሁም ክብደት መጠን ገደብ አይዘንጉ።



△ **1.** መጠናቸው አነስተኛ የሆኑ የሕጻናት የዱቄት ምግቦችና ዳይፐሮች




□ **2.** ላፕቶፕ እና ታብሌቶች




□ **3.** ስልኮች እና ዘመናዊ/ስማርት ስልኮች



□ **4.** ካሜራ



□ **5.** ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች (ከ110-120 ቮልት ጋር የሚስማሙ)



□ **6.** ጌጣጌጦች



□ **7.** ልብስ እና ጫማ



□ **8.** አሻንጉሊቶች



□ **9.** ሃይማኖታዊ እቃዎች


መልሶች: 1(▽)፡ 2(▽)፡ 3(▽)፡ 4(▽)፡ 5(□)፡ 6(◯)፡ 7(□)፡ 8(□)፡ 9(□)

ክፍል 2 - ጉዞ


“○” =  “□” =  “△” = 




10. የግል መገልገያ ምርቶች (ለምሳሌ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ)




11. በመጠን ትንሽ የሆኑ ፈሳሽ ቅባቶች፣ ክሬም እና ጄሎች (እያንዳንዳቸው ከ100 ሚ/ሊትር በታች የሆኑ፣ በግልጽ በሚታዩ ፕላስቲክ እቃዎች ውስጥ የተቀመጡ)




12. ፈሳሽ ቅባቶች፣ ክሬም እና ጄሎች (ከ100 ሚ/ሊትር በላይ)



13. ሲጋራ (እስከ 200 የሚደርሱ የተጠቀለሉ ሲጋራዎች፣ 50 ሲጋራ እና 200 ግራም ትንባሆ)




14. የጸጉር ብሩሽ፣ ማበጠሪያ እና የጥርስ ብሩሽ



15. አልኮል/መጠጥ (እስከ 8.5 ሊትር ቢራ፣ 1.5 ሊትር ወይን፣ 1.14 ሊትር)



16. ሰነዶች እና የምስክር ወረቀቶች



17. የግል ፎቶዎች



18. ገንዘብ



19. መጽሐፍት እና መዝገበ ቃላት




20. በዶክተር የተጻፉ የመድሀኒት ማዘዣዎች እና መድኃኒቶች



21. የታሸጉ ምግቦች

መልሶች፡ – 10: (□) 11: (○) 12: (□) 13: (□) 14: (○) 15: (□) 16: (△) 17: (○) 18: (△) 19: (□) 20: (○) 21: (□)

“○” =  “□” =  “△” = 




☐ **22.** ይህንን የመልመጃ መጽሐፍ



☐ **23.** ድምጽ የሌላቸው ለጉዞው የሚያዙ




☐ **24.** የታሸጉ ቀላል ምግቦች




☐ **25.** ሊደርቡት የሚችሉት ልብስ



☐ **26.** ዣንጥላ (እንደ አየር ጸባዩ ሁኔታ)



☐ **27.** ሰዓቶች



☐ **28.** መጽሐፍ ወይም መጽሔቶች



☐ **29.** የልጅ ጋሪ



☐ **30.** የመዋቢያ እቃዎች

**ወደ ካናዳ ይዘው የሚገቡት የገንዘብ መጠንን በተመለከተ ገደብ የለም። ይዘው የገቡት ገንዘብ በአንድ ቤተሰብ ከ10 ሺሕ የካናዳ ዶላር (CAD) በላይ ከሆነ፣ ለካናዳ ጉምሩክ ማሳወቅ አለብዎት። ካልሆነ ግን ቅጣት ሊከፍሉ ወይም ሌሎች ቅጣቶች ሊያጋጥምዎ ይችላል።**

**ወደ ካናዳ ገንዘብዎን በጥሬ፣ በገንዘብ ትዕዛዝ፣ በቼክ፣ በአክሲዮን ወይም በባንክ ዝውውር ከባንክዎ ወደ ካናዳ ባንክ ሊያስገቡ ይችላሉ። ለጉምሩክ የሚያሳውቁት የገንዘብ መጠን የሚቀበሉት የገንዘብ ድጋፍ መጠን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።**




መልሶች፡ – 22: (□) 23: (○) 24: (○) 25: (○) 26: (○) 27: (○) 28: (○) 29: (△) 30: (□)

# 2.8 ትተው የሚመጧቸው ነገሮች

ወደ ካናዳ ተይዘው የማይገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ። ወደ ካናዳ ይዘዋቸው ከገቡ እና ካላሳወቁ ግን ካናዳ ሲገቡ ቅጣት ሊከፍሉ ወይም ክስ ሊቀርብብዎት ይችላል።


ትተዋቸው መምጣት ያለብዎት እና በካናዳ የሚከለከሉ ነገሮች፤




1. ምግብ (ስጋ፣ ወተት፣ የእንስሳት ተዋጽኦ እና ፍራፍሬ/አትክልት)




2. ተክሎች፣ አፈርና እንጨት



3. ቆዳን ጨምሮ የእንስሳት ክፍሎች




4. እጽዋት፣ ቅመማ ቅመም እና ዘር



5. ግዙፍ የኤክትሮኒክስ መሣሪያዎች (ቴሌቭዥን እና የቤት ውስጥ መገልገያን ጨምሮ)



6. የጦር መሣሪያዎች እና ጥይት



7. የሰው አጥንት




8. ተሽከርካሪዎች



9. አደንዛዥ እጽ

## 2.9 በእጅ ቦርሳ ውስጥ እንዳይያዙ የሚከለከሉ ነገሮች







1. ፈሳሽ ቅባቶች፣ ክሬም እና ጄል (እያንዳንዳቸው ከ100 ሚሊ በላይ)



2. ስለታማ እና አደገኛ እቃዎች (ጥፍር መቁረጫ፣ ክብሪት፣ የሲጋራ መለኮሻ፣ ሴንጢ/ቢላ፣ ተቀጣጣይ ቁሳቁስ እና የስፖርት እቃዎች)



3. እንስሳትን ወደ ካናዳ ማምጣትን በተመለከተም ገደቦች አሉ። አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳን ወደ ካናዳ ማስገባት ከተፈለገ፣ ለትራንስፖርት እንዲሁም ለሕክምና እና ክትባትም መክፈል አለብዎት።



4. ህጻናት ጋር ጉዞ ለሚያደርጉ ሰዎች፣ በእጅ ቦርሳ ውስጥ ለልጆች የሚሆኑ እንደ ወተት እና የልጆች ምግብ(በትናንሽ መያዣዎች) ያሉትን ለመያዝ ፈቃድ መኖርን ያጣሩ።

# 2.10 ለጉዞ ከመነሳትዎ በፊት

***መመሪያ:*** ለጉዞ ሲዘጋጁ ሊያደረጓቸው የሚችሏቸውን ነገሮች ይመልከቱ። በእያንዳንዱ ተግባራት እና በዝርዝሩ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



1.



2.



3.



4.



5.

**ሀ)** በጣም ግዙፍ፣ ሕገወጥ የሆኑ እና በካናዳ ሊያገኟቸው የሚችሉትን ነገሮች ያስቀሩ

**ለ)** በጣም ወሳኝ እና አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችን በእጅ ቦርሳዎ ውስጥ ያስቀምጡ

**ሐ)** ጠቃሚ ሰነዶችን ሰብስበው ኮፒ/ቅጂ ያድርጉ

**መ)** ሻንጣዎን መለየት እንደሚችሉ እና መዘጋት እንደሚችል እርግጠኛ ይሁኑ

**ሠ)** ሊሸከሉ የሚፈልጓቸውን ንብረቶችዎን ጥቅማቸውን፣ የተቀመጠላቸው የደኅንነት ገደብ እና ክብደታቸውን መሠረት አድርገው ይሰብስቧቸው።

**ጉዞ በሚያደርጉበት ቀን በላዩ ላይ የዓለማቀፉ ፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) የድርጅቱ (IOM) አርማ ያለበት ቦርሳ ይሰጥዎታል። ይህን ሻንጣ በጉዞዎ ሁሉ በሚታዩበት ቦታ ላይ በጥንቃቄ ይያዙት።**





መልሶች፡ 1 (ሐ)፤ 2 (ሠ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (መ)፤ 5 (ለ)

# 2.11 በዚህ የ IOM ቦርሳ ውስጥ ምን ዓይነት ሰነዶች አሉ?


***መመሪያ፡*** ሰነዶቹን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ሰነድ እና በመጠሪያ ስሞቹ መካከል በማስመር ያዛምዱ።




1.




2.




3.



4.



5.



6.

ሀ) የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ

ለ) ሌሎች ሰነዶች፣ አስፈላጊ ከሆነ፣ የመውጫ ፈቃድን ጨምሮ

ሐ) ፓስፖርት ወይም የጉዞ ሰነድ


መ) ቪዛ

ሠ) የአየር መንገድ ትኬት

ረ) የኢሚግሬሽ የሕክምና/የጤና ጉዳይ ሰነዶች አስፈላጊ ከሆነ

**የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ ይፋዊ የኢሚግሬሽን ሰነድዎ ነው። ካናዳ ከደረሱ ከተወሰኑ ሳምንታት በኋላ የቋሚ መኖሪያ ካርድ ያገኛሉ። ይህ ካርድ የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫ ሰነድን የሚተካ አይደለም። ስለዚህም ሁሌም የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ማረጋገጫውን በጥንቃቄ መያዝ አለብዎት።**

መልሶች፡ 1 (ሐ)፤ 2 (መ)፤ 3 (ሠ)፤ 4 (ረ)፤ 5 (ሀ)፤ 6 (ለ)



ወደ ካናዳ በሚደረገው ጉዞ፣ የጾታ ገለጻቸው በሰነድ ላይ ካለው የተለየ የሆኑ ሰዎችን ዓለማቀፍ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) ይረዳቸዋል። ለተጨማሪ መረጃ ከIOM ሠራተኞች ጋር በምስጢር ማውራት ይችላሉ።

## 2.12 ሊይዙት የሚገባ ሰነድ የትኛው ነው?


**መመሪያ:** ያለዎትን ተጨማሪ ሰነዶች ይመልከቱ። ያለዎትን እና ይዘውት ሊሄዱ ያቀዷቸውን ሰነዶች ካሉ የ “✓” ምልክት በሳጥኑ ውስጥ ያስቀምጡ።



☐ **1.** በዶክተር የተጻፈ የሕክምና የመድሀኒት ማዘዣ እና መዝገቦች




☐ **2.** የትምህርት የምስክር ወረቀቶች




☐ **3.** የክትባት መዝገቦች



☐ **4.** የልደት የምስክር ወረቀቶች



☐ **5.** የትዳር/የፍቺ የምስክር ወረቀቶች



☐ **6.** አስፈላጊ የሆኑ ትርጉም ሰነዶች

**መመሪያ:** ከዚህ ሌላ የትኛውንም ዓይነት የሚያስፈልግዎትን ሰነድ በተሰመረው ክፍት ቦታ ላይ ይጻፉ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

# 2.13 አየር መንገድ ውስጥ

ወደ አዲሱ ቤትዎ ወደ ካናዳ ሲያመሩ፣ በየአየር መንገዱ የሚያሳልፏቸው የተለያዩ ተግባራት አሉ። በእነዚህም ሂደቶች ከአንድ ጊዜ በላይ ሊያልፉ ይችላሉ።

***መመሪያ:*** የአየር መንገዱን የአሠራር ሂደት ይመልከቱ። በየአንዳንዱ የአየር መንገዱ ሂደት እና በማብራሪያው መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**የአየር መንገድ መግቢያ ማሳወቂያ ዴስክ**

**1.**



**የኢሚግሬሽን ኬላ**

**2.**



**የፍተሻ ኬላ**

**3.**




**የመነሻ መግቢያ**

**4.**



**የጉምሩክ ኬላ**

**5.**



**የሻንጣ መቀበያ**

**6.**

**ሀ)** በፍተሻ ወቅት በቦርሳዎ ወይም በላይዎ ላይ አደገኛ ነገር ይኖር እንደሆነ የሚፈትሹ የባለሞያዎችን ትዕዛዝ ይከተሉ። እርስዎ እንዲሁም ሻንጣዎ በመፈተሻ መሳሪያ ውስጥ ማለፍ አለባችሁ። በፍተሻውም ፈታሹ አደገኛ ነገሮች መኖር ወይም አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ሊነካዎ ያስፈልግ ይሆናል።

**ለ)** ሻንጣዎን ይመዝኑ እንዲሁም ልዩ ምልክት ይለጥፉበት። የመሳፈሪያ ይለፍ ወረቀት እንዲሁም የሻንጣ ምዝገባ ተለጣፊ መለያ ይቀበሉ። ሻንጣዎን ለአየር መንገዱ ሠራተኞች ይተዉላቸው።

**ሐ)** የሚቀመጡበትን ወንበር እንዲሁም የሚጠብቁበትን ቦታ በትክክል ለማወቅ/ለማየት ትኬትዎን ይመልከቱ። ይህም በአውሮፕላኑ ውስጥ የሚሳፈሩበት ነው። በተጫማሪም የተለያዩ ማሳወቂያዎች ሲነገሩ በጥንቃቄ ያዳምጡ።

**መ)** በሻንጣዎችዎ ስላሉ እቃዎች ለሚቀርብልዎ ጥያቄ መልስ ይስጡ።

**ሠ)** ከሚሽከረከረው የሻንጣ ማቆያ ሻንጣዎን ውሰዱ። ሻንጣዎች ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ መስለው ይታያሉ። የሚወስዱት ሻንጣ የራስዎ መሆኑን በሚገባ ያረጋግጡ።

**ረ)** አንድን ሀገር ለቅቀው ሲወጡ ወይም ወደ ሌላው ሲገቡ፣ ለሚመለከተው የመንግስት ኃላፊ አስፈላጊውን ሰነድ ያቅርቡ።

መልሶች፡ 1 (ለ)፤ 2 (ረ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሐ)፤ 5 (መ)፤ 6 (ሠ)

# 2.14 በአየር መንገድ ያሉ መሣሪያዎች

ተከታዮቹ በጉዞዎ መካከል ሊያግዝዎ የሚችሉ እና በአየር መንገዱ ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸው መሣሪያዎች ናቸው።

**መመሪያ:** በአየር መንገድ ያሉትን መሣሪያዎች ይመልከቱ። በየአንዳንዱ መሣሪያ እና በማብራሪያው መካከል በማስመር ዛምዱ።




የሻንጣ ጋሪ

1.



ተንቀሳቃሽ መሄጃዎች

2.



የመረጃ ዘጋቢ ሰሌዳ

3.




የአቅጣጫ መጠቆሚያ

4.



አውቶማቲክ ደረጃዎች

5.



አሳንሰሮች

6.

ሀ) በረራዎች የሚነሱበትን እና የሚያርፉበትን ጊዜ የሚገልጽ፣ የሰዓት እና የመግቢያ በሮች መረጃ ያሳያል።

ለ) ለአካል ጉዳተኞች እና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በጋሪ ሻንጣ ይዘው ለመንቀሳቀስ።

ሐ) ሊሄዱ ወደሚፈልጉበት በመጠቆም ይረዳል።

መ) አየር መንገድ ውስጥ ሻንጣ ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ያግዛል።

ሠ) በአየር መንገዱ ከአንዱ ደረጃ ወደሌላው መንቀሳቀስ ሲፈልጉ።


ረ) ረጅም መንገድን በተሻለ ፍጥነት ለመሄድ ይረዳል።

መልሶች፦ 1 (መ)፤ 2 (ረ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሐ)፤ 5 (ሠ)፤ 6 (ለ)

# 2.15 የመሳፈሪያ ይለፍ ወረቀት ላይ ያለ መረጃ

የመሳፈሪያ ቅፅ ወረቀትዎን በየጊዜው ማሳየት ይጠበቅብዎታል። እያንዳንዱ መንገደኛ የራሱ አለው። እንዳይጠፋብዎት በጥንቃቄ ይያዙት።


**መመሪያ:** የመሳፈሪያ ቅፅ ወረቀትዎን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ የቅፅ ወረቀት ቃላት እና በምስሉ መካከል በማስመር ያዛምዱ።




መልሶች፡ 1 (ለ)፣ 2 (መ)፣ 3 (ሠ)፣ 4 (ረ)፣ 5 (ቀ)፣ 6 (በ)፣ 7 (ሸ)፣ 8 (ሰ)፣ 9 (ሐ)፣ 10 (ሀ)

# 2.16 አውሮፕላኑ

***መመሪያ:*** የአውሮፕላኑን የውስጥ ካርታ ይመልከቱ። በየአንዳንዱ የአውሮፕላኑ ክፍሎች እና በካርታው ላይ የሚገኙበትን ቦታ ያመላክቱ።




መልሶች: (ሀ) 3፤ (ለ) 1፤ (ሐ) 2

# 2.17 ወንበርዎ ላይ


**መመሪያ:** በአውሮፕላኑ ውስጥ ባለው መቀመጫ ወንበር ላይ ምን እንዳለ ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ምስል እና በተቀመጠው ማብራሪያ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.** **በከፍታ ላይ ለሚያጋጥም ሕመም የሚያገለግል ቦርሳ/ላስቲክ**



**2.** **ትሪ**



**3.** **የ‹ቀበቶውን ይሠሩ› ምልክት**



**4.** **መጥሪያ**


ሀ) ራስዎን ለመጠበቅ መከተል ያለብዎት መመሪያ

ለ) አውሮፕላን ውስጥ ሲቀመጡ የሚጠቀሙበት ጠፍጣፋ ቦታ

ሐ) የበረራ አስተናጋጆችን ትኩረት ማግኛ መንገድ

መ) ሊያስመልስዎ ካለ/ወደላይ ካለዎት የሚጠቀሙት የወረቀት ወይም የፕላስቲክ ቦርሳ

መልሶች፡ 1 (መ)፤ 2 (ለ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሐ)



5.

**መብራት**


ሠ) በአውሮፕላኑ ውስጥ ስላለው የደኅንነት ጉዳይ የሚያስረዳ በራሪ ወረቀት



6.

**የበረራ የመዝናኛ ስርዓት**

ረ) የእጅ ቦርሳዎን ሊያስቀምጡበት የሚችሉበት ስፍራ



7.

**ከራስ በላይ የሻንጣ ማስቀመጫ**

ሰ) ባሉበት አካባቢ ሆነው ለማንበብ ወይም ሌላ ሥራ ለመሥራት ጨለማ ከሆነብዎት የሚጠቀሙት



8.

**የደኅንነት መመሪያ ካርድ**

ሸ) ፊልም በማየት፣ ሙዚቃ በማዳመጥ ወይም ጨዋታዎችን በመጫወት ጊዜን ማሳለፊያ መንገድ

**እንደ ሕይወት አድን ጃኬቶች ያሉ በአውሮፕላን ውስጥ የሚገኙ የደኅንነት ቁሳቁሶችን ከነበሩበት ማንሳት ሕገወጥ ተግባር ነው።**

መልሶች፡ 5 (ሰ)፣ 6 (ሸ)፣ 7 (ረ)፣ 8 (ሠ)

# 2.18 አውሮፕላን ውስጥ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው ነገሮች

**መመሪያ:** አውሮፕላን ውስጥ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸውን ተግባራት ይመልከቱ። በበረራ ቆይታዎ እርስዎም ሊያደርጉ ያሰቧቸው ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያስቀምጡ።




☐ **1.** ምግብዎን በአግባቡ ይመገቡ፣ ፈሳሽ በብዛት ይውሰዱ



☐ **2.** አይጨነቁ፣ ይተኙ



☐ **3.** ሕጻናት ልጆች በተቀመጡበት እንዲቆዩ ተግባሮችን መስጠት




☐ **4.** መጸዳጃ ቤት ይጠቀሙ



☐ **5.** አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መድኃኒት ይውሰዱ



☐ **6.** ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር ሲነጋሩ በለሰለሰ አነጋገር ይሁን



☐ **7.** የበረራ አስተናጋጆችን መመሪያ ይከተሉ

**አውሮፕላን ሲነሳ፣ ሲያርፍ እንዲሁም በበረራ አስተናጋጆቹ ሲናገሩ ቀበቶዎን ማጥበቅ ግድ ነው።**

## 2.19 ማን ሊረዳችሁ ይችላል?

**መመሪያ:** ወደ ካናዳ በሚያደርጉት ጉዞ ይረዱኛል የሚሏቸውን ሰዎች ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ሁኔታ እና በጉዳዩ ላይ ምን ዓይነት ሰዎች ሊረዱዎ ይችላሉ በሚለው መካከል ያዛምዱ። የተወሰኑ ሁኔታዎች ከአንድ በላይ መልስ አላቸው።



6. ሻንጣ መቀበያ ስፍራ ሆነው ነገር ግን ሻንጣዎችዎን ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ



1. ርቦዎት፣ ጠምቶዎት ወይም አውሮፕላን ውስጥ ሆነው እርዳታ ሲፈልጉ




2. በአየር መንገዱ ውስጥ ሳይረን ይጮሀል፣ ድንገተኛ ክስተት አለ ማለት ነው

**ሀ**




**የመግቢያ ማሳወቂያ ዴስክ ሠራተኞች**

**ለ**



**የአየር መንገድ ፈታሾች**

**ሐ**



**የአየር መንገድ ሠራተኞች**

**መ**



**የአየር መንገዱ የመረጃ ዴስክ**


**ሠ**



**የበረራ አስተናጋጆች**



5. ወደ መሸጋገሪያ በረራዎ ሲገቡ ነገር ግን መግቢያውን ሳያውቁ ሲቀሩ




4. በአውሮፕላን ውስጥ የተቀመጡበት ወንበር ቤተሰብዎ ከተቀመጠበት ሲርቅ



3. አየር መንገድ ውስጥ ቢጠፉ

**በአየር መንገድ ውስጥ ይሁን ወይም አውሮፕላን ውስጥ አልያም መሸጋገሪያ ጉዞዎ ላይ፣ ቤተሰብዎ እንዳይለያይ ያድርጉ፣ ልጆችዎንም ይከታተሉ።**


መልሶች: 1 (ሠ)፣ 2 (ለ፣ ሐ፣ መ)፣ 3 (ሐ፣ መ)፣ 4 (ሀ፣ ሠ)፣ 5 (ሐ፣ መ)፣ 6 (ሐ፣ መ)

# 2.20 የቋሚ ነዋሪነት ሁኔታዎ

ካናዳ ሲደርሱ፣ አየር መንገድ ላይ ከአንድ የሚመለከተው ኃላፊ ጋር አጠር ያለ ቃለመጠይቅ ይኖርዎታል። ቀጥሎም አንዳንድ ሰነዶችን እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

ይህን ሲጨርሱ በካናዳ ለመኖር መብት ያለዎ ቋሚ ነዋሪ ይሆናሉ።

**በካናዳ በጀመሩት አዲስ ኑሮ አብርዎት እየኖረ ያልሆነ አጋር፣ የትዳር ጓደኛም ወይም ልጅ እና የልጅ ልጅ አለ? ወደፊት ወደ ካናዳ መጥተው ኑሮዋቸውን ያደርጋሉ? እንደዛ ከሆነ፣ ካናዳ ከመድረስዎ በፊት ስለጉዳዩ ለመንግሥት ማሳወቅ አለብዎት። ለመንግሥት ይህን ማሳወቅ አለመቻል ወደፊት ከእነዚህ ሰዎች ጋር በካናዳ ዳግም የመገናኘት ሁኔታዎን ከባድ ያደርገዋል።**




የካናዳ ቋሚ ነዋሪ መሆንዎን የሚያሳይ ካርድ በፖስታ ቤት ይላክልዎታል። ይህም የቋሚ ነዋሪነት ካርድ ይባላል። የቋሚ ነዋሪነት ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜው አያበቃም። የካርዱ የአገልግሎት ጊዜ ግን ያበቃል። ካርዱ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ ግን ለአዲስ ካርድ ማመልከት አለብዎት።

የቋሚ ነዋሪነት ካርድ ማመልከቻዎ ሂደቱን ጨርሶ እስኪደርስዎ ድረስ ብዙ ጊዜ ይጠይቃል።

**ካናዳ ሲደርሱ የሚቀበሏቸው ሰነዶች በጣም ወሳኝ እና ጠቃሚ ናቸው። በጥንቃቄ ይያዟቸው።**



# 2.21 በካናዳ መብት እና ግዴታዎች

በካናዳ ቋሚ ነዋሪ ሲሆኑ፣ የብዙ መብቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ። እነዚህን ተከትሎ ደግሞ ግዴታዎች አሉ።

**መመሪያ:** በካናዳ እንደ ቋሚ ነዋሪ ያለዎትን መብት እና ግዴታ ይመልከቱ። ግንኙነት ባለው በየአንዳንዱ መብት እና ግዴታ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.** **የመሥራት ወይም የግል የንግድ ሥራ ባለቤት መሆን**



**2.** **አስተያየትዎን ማሰማት**



**3.** **ለሁሉም የሚሆን ሰብአዊ መብት**



**4.** **ሐይማኖትዎን የማራመድ**



**5.** **ነጻ እና መሠረታዊ የትምህርት አገልግሎት**




**ሀ)** የሁሉንም ሰው ሰብአዊ መብት ማክበር




**ለ)** ራስዎን፣ ቤተሰብዎን መርዳት እንዲሁም ግብር መክፈል



**ሐ)** ሁሉንም ሐይማኖቶች ማክበር




**መ)** ልጆች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ እንደሆነ ማረጋገጥ



**ሠ)** የሌሎችን አመለካከት ማክበር

መልሶች፦ 1 (ለ)፤ 2 (ሠ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሐ)፤ 5 (መ)




**6.**

**ንብረት መያዝ**



ረ) አካባቢን መጠበቅ




**7.**

**የሕዝብ የጤና አገልግሎት ማግኘት**




ሰ) ወደ ካናዳ በድጋሚ ለመግባት ትክክለኛ የሆነ የቋሚ የመኖሪያ ካርድ ማሳየት




**8.**

**ጤናማ እና ንጹህ ከባቢ ውስጥ መኖር**




ሸ) ግብር መክፈል



**9.**

**ከከናዳ ውጪ የመጓዝ**





ቀ) የንብረት ግብር መክፈል

**በስደተኝነት ካናዳ መኖሪያቸውን ያደረጉ ሰዎች ተመልሰው ወደ መጡበት ሀገር የሚያቀኑ ከሆነ፣ በካናዳ የቋሚ መኖሪያ ፈቃዳቸው ሕጋዊ ሁኔታ በአሉታዊ መንገድ ተጽእኖ ሊደርስበት ይችላል። በሚመለሱ ጊዜ በካናዳ አየር መንገድ ያሉ የመንግሥት ኃላፊዎች ጥያቄዎችን ያቀርቡላቸዋል። በዚህ ጊዜ ወደ አገራቸው የተመለሱበትን እውነተኛ ምክንያት መግለጽ አለባቸው።**

መልሶች፡ 6 (ቀ)፤ 7 (ሸ)፤ 8 (ረ)፤ 9 (ሰ)

# 2.22 ቋሚ ነዋሪዎች

በካናዳ ቋሚ ነዋሪ ሲሆኑ እንደ ዜጋ የሁሉም መብቶች ተጠቃሚ ነዎት። ነገር ግን ተከታዮቹን ማድረግ አይችሉም፤









1. በፌደራል ምርጫ መምረጥ አይችሉም
2. ለከፍተኛ የመንግስት ሥራ ማመልከት አይችሉም
3. በካናዳ የቋሚ መኖሪያ ፍቃድዎ እንዲጸና የተወሰነ ጊዜ ካናዳ ውስጥ በአካል መገኘት አለብዎት


**በከፍተኛ ወንጀል ክስ የተከሰሱ ቋሚ ነዋሪዎች የቋሚ ነዋሪነት ፈቃዳቸውን ሊያጡ ይችላሉ።**



# 2.23 ለካናዳ ዜግነት ማመልከት የሚችሉት መቼ ነው?

ለካናዳ ዜግነት ከማመልከትዎ በፊት ተከታዮቹን ማድረግ ይጠበቅብዎታል፤








1. ለተወሰነ ጊዜ በካናዳ ይቆዩ። ለዜግነት ጥያቄ ማመልከቻ መቼ ማስገባት እንዳለብዎት ለማስላት ተከታዩን ያንብቡ፤
2. የእንግሊዘኛ ወይም የፈረንሳይኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ ይኑርዎ።
3. ስለካናዳ የተወሰነ እውቀት እንዳለዎ ፈተና በማለፍ አረጋግጡ




የካናዳ ዜግነት ከተሰጠዎት በኋላ፤ የካናዳ ፓስፖርት ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።

# ምዕራፍ 3
# ድጋፍ እና አገልግሎቶች



# ምዕራፍ 3

# ድጋፍ እና አገልግሎቶች



በዚህ ምዕራፍ የተቀመጠው በካናዳ ስለሚገኙ አገልግሎቶች ነው። ካናዳ ከደረሱ በኋላ ደግመው ማንበቡ ጠቃሚ ነው።

ቋሚ ነዋሪ የሚሆኑት በካናዳ በሚያርፉበት የመጀመሪያው አየር መንገድ ያለውን የኢሚግሬሽን ሂደት ሲያልፉ ነው። እንደ ቋሚ ነዋሪም በካናዳ ተረጋግቶ ለመኖር የሚያስችሉ የተለያዩ ድጋፎችን ያገኛሉ።



እንዳሉበት የሰፈራ ፕሮግራም የሚያገኙት ድጋፍ ይለያያል።

## 3.1 ኑሮን በካናዳ ለማድረግ የሚያስችሉ (የሰፈራ) ፕሮግራሞች

***መመሪያ:*** ተከታዩን በሰፈራ ፕሮግራሞች ላይ ያለውን መረጃ ያንብቡ። እርስዎ በካናዳ ከነበሩበት ፕሮግራም ጋር የሚገናኘው ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።



GAR / RPG

☐ 1. ***በመንግሥት የተደገፈ የስደተኞች ፕሮግራም (GAR/RPG)***

በዚህ ፕሮግራም ግለሰቦች ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ ይቀበላሉ። እንዲሁም በመንግስት ከሚደጎሙ ድርጅቶች አስቸኳይ የመኖሪያ (የሰፈራ) ድጋፍ ያገኛሉ። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፤



**PSR/ PPPR**

2. **በግል ለሚደገፉ ስደተኞች ፕሮግራም (PSR/PPPR)**
ግለሰቦች ከግል ድርጅት እና ቡድኖች የገንዘብ ልገሳ እና ድጋፍ ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ፣ ከዚህ ፕሮግራም የገንዘብ እርዳታ እና አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍ የሚያገኙት ከግል ለጋሾች/ስፖንሰሮች ነው። አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍም ከእነዚህ የግል ለጋሾቻቸው ያገኛሉ። በዚህ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ፤



**JAS/ PAC**

3. **ጥምር የእርዳታ ድጋፍ ፕሮግራም (JAS/PAC)**
ግለሰቦች የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙት ከመንግሥት ነው። አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍም በመንግስት ከሚደጎሙ ድርጅቶች ያገኛሉ። በካናዳ ተጨማሪ ድጋፍ የሚሰጧቸው የግል ለጋሾች/ስፖንሰሮች አሏቸው። ለበለጠ መረጃ ይህን ማስፈንጠሪያ በመንካት ያንብቡ፤



**BVOR/ RDBV**

4. **የተቀላቀለ የእርዳታ ድጋፍ ፕሮግራም (BVOR/RDBV)**
በዚህ ፕሮግራም ስር ግለሰቦች ከመንግስት እና ከግል ስፖንሰሮች የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍ ከግል ለጋሾች ይቀበላሉ። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፤

**በየትኛውም ፕሮግራም ውስጥ ቢሆኑ፣ በመንግስት ከሚደጎሙ ድርጅቶች የረጅም ጊዜ አገልግሎቶች ማግኘት አለብዎት። በመንግሥት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ እንዲያገናኙዎት ይጠይቁ። ለበለጠ መረጃ ምዕራፍ ሦስት 3.11 ላይ ያሉ ተግባራትን ይመልከቱ፤**



## 3.2 የአስቸኳይ ድጋፍ ገደብ

በካናዳ የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ውስን ነው።




በመንግስት ከሚደጎም ድርጅትም ሆነ ከለጋሾችዎ የሚገኙት የአስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍም በተመሳሳይ ውስን ነው። እነዚህ ድጋፎች የሚቆዩበት ጊዜም ባሉበት የሰፈራ ፕሮግራም የሚወሰን ነው። ያሉበትን ሁኔታ መሠረት አድርጎም ይህ ጊዜ ሊቀያየር ይችላል።




## 3.3 በሰፈራ ፕሮግራሞች የጋራ የሆኑ አገልግሎቶች

ድጋፍ የሚያገኙት በየትኛውም ፕሮግራም ውስጥ ቢሆን፣ ማንኛውም በስደተኝነት ወደ ካናዳ የመጡ እና ኑሮዋቸውን በዚያ የሚያደርጉ ሁሉም ቋሚ ነዋሪዎች ተከታዮቹን አገልግሎቶች ያገኛሉ፤




1. ካናዳ ከመድረስዎ በፊት በካናዳ ለሚኖርዎ ኑሮ ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችል ነጻ በአካል ወይም በበይነ መረብ አገልግሎት፤ ለበለጠ መረጃ ይህን ያንብቡ፤



2. ካናዳ ሲደርሱ በኢሚግሬሽን እና ጉምሩክ ሲያልፉ ያለው ሂደት ላይ የሚግዝዎ እንዲሁም ወደ መዳረሻዎ ሲሄዱ የሚረዳዎ የአየር መንገድ የእንግዳ ተቀባዮች አገልግሎት።



3. ወደ ካናዳ የሚመጡበት የጉዞ ወጪ የሚሸፍን ብድር ከካናዳ ማግኘት። ካናዳ ከገቡ አንድ ዓመት በኋላ ነው ይህን ወለድ አልባ ብድር መክፈል እንዲጀምሩ የሚጠየቁት።




4. ከጊዜያዊ የጤና ፕሮግራም (IFHP/PFSI) ስር ጊዜያዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን ማግኘት። ይህም በመኖሪያ አካባቢዎ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ማግኘት እስኪጀምሩ ድረስ ወሳኝ የሆነ የጤና አገልግሎት ወጪዎን የሚሸፍን ነው። ከመንግስት ወይም ከለጋሾችዎ ከሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ ይህ አገልግሎት የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ወጪውን ይሸፍናል። ለበለጠ መረጃ ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ እንዲሁም ይህንን ያንብቡ፤

# 3.4 አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፎች

***መመሪያ:*** በካናዳ ኑሮዎን ለማድረግ ካሉበት ፕሮግራም ጋር የሚገናኘው ላይ የ "✓" ምልክት ያድርጉ፤






- ☐ **GAR/ RPG**
- ☐ **PSR/ PPPR**
- ☐ **JAS/ PAC**
- ☐ **BVOR/ RDBV**

***መመሪያ:*** በካናዳ የሚያገኙትን አስቸኳይ የመኖሪያ ድጋፍ ይመልከቱ። ከታች እያንዳንዱን አገልግሎት ከሚሰጠዎ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።

**1.** በክረምት ወቅት ከሆነ የደረሱት፤ የክረምት አልባሳትን ማን ያቀርብልዎታል?



- ☐ ሀ) ካናዳ አየር መንገድ ከኦክቶበር 15 እስከ ኤፕሪል 15 ባለው ጊዜ ከደረሱ፤ በመንግሥት ድጎማ ከሚያገኙ ድርጅቶች



- ☐ ለ) የመጨረሻ መዳረሻ ከተማዎ ሲደርሱ በግል ለጋሾችዎ



**2.** ከደረሱበት ቦታ ወደ ማረፊያ ስፍራዎ የሚያደርስ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥዎት ማን ነው?



- ☐ ሀ) በመንግሥት የሚደጎመው ድርጅት



- ☐ ለ) ለጋሾችዎ



**3.** ካናዳ ሲደርሱ ጊዜያዊ ማረፊያ የሚያዘጋጅልዎት ማን ነው?



- ☐ ሀ) በመንግሥት የሚደጎመው ድርጅት



- ☐ ለ) ለጋሾችዎ



መልሶች GAR/RPG 1(ሀ)፡ 2(ሀ)፡ 3(ሀ)፡ PSR/PPPR 1(ለ)፡ 2(ለ)፡ 3(ለ) JAS/PAC 1(ሀ)፡ 2(ሀ)፡ 3(ሀ) BVOR/ RDBV 1(ለ)፡ 2(ለ)፡ 3(ለ)

ክፍል 3 - ድጋፍ እና አገልግሎቶች

**4.** ቋሚ መኖሪያ እንዲያገኙ የሚረዳዎ እንዲሁም አዲስ ወይም ያገለገሉ የቤት እቃዎችን የሚያቀርብልዎ ማን ነው?



☐ **ሀ)** በመንግሥት የሚደጎመው ድርጅት



☐ **ለ)** ለጋሾችዎ



**5.** በካናዳ የተረጋጋ ኑሮ እንዲጀምሩ የሚያስችል የረጅም ጊዜ ድጋፍ እንዲያገኙ ወደሚያስችሉ ደጋፊዎች ማን ያመላክትዎታል?



☐ **ሀ)** በመንግስት የሚደጎመው ድርጅት




☐ **ለ)** ለጋሾችዎ



**6.** የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ የሚያቀርብልዎ ማን ነው?



☐ **ሀ)** መንግሥት



☐ **ለ)** ለጋሾችዎ



☐ **ሐ)** መንግሥት እና ለጋሾችዎ፤ ሁለቱም



መልሶች
GAR/RPG 4(ሀ)፡ 5(ሀ)፡ 6(ሀ)፡ PSR/PPPR 4(ለ)፡ 5(ለ)፡ 6(ለ)፡ JAS/PAC 4(ሀ)፡ 5(ሀ)፡ 6(ሀ)፡ BVOR/RDBV 4(ለ)፡ 5 (ለ)፡ 6 (ሐ)

# 3.5 ድርሻ እና ኃላፊነት

በአንድ አገር ውስጥ ኑሮን መምራት ጊዜ እና ጥረትን የሚጠይቅ ነው።

እርስዎም ድጋፍ የሚያቀርብልዎትም የሚጋሯቸው ኃላፊነቶች አሉ።

***መመሪያ:*** ከመኖሪያዎ ጋር በተገናኘ ያለዎትን ኃላፊነት ይመልከቱ። በመንግስት ድጎማ በሚደረግላቸው ድርጅቶች እና ለጋሾችዎ እንዲሁም እርስዎ ባለዎት ኃላፊነት መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.** ካናዳ ሲገቡ አቀባበል ማድረግ።



**2.** የሚቀበሉትን ውስን የሆነ የድጋፍ ገንዘብ እንዴት በኃላፊነት መጠቀም እንዳለብዎት መምከር።



**3.** ቋሚ ቤት እንዲያገኙ እንዲሁም የኪራይ ውልን ሁኔታ እንዲረዱ ማገዝ።



**4.** በማረፊያዎ እንዴት በደኅንነት እንደሚቆዩ ማሳየት።



**ሀ)** በሚቀበሉት ገንዘብ ኑሮዎን መምራት እንዲችሉ የገንዘብ በጀት በመመደብ። ከልክ በላይ ወጪ ካወጡ፣ ተጨማሪ ገንዘብ አይሰጥዎትም።



**ለ)** በርዎን ይቆልፉ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችንም በጥንቃቄ ይጠቀሙ።



**ሐ)** ሻንጣዎችዎን እንዲሁም ሰነዶችዎን ሁሉ ይያዙ። የተሰጠዎትን የዓለማቀፉ የፍልሰተኞች ጉዳይ ድርጅት (IOM) ሻንጣ በሚታይ ቦታ ያስቀምጡት፤ ሰዎች በቀላሉ ሊያገኙዎ እንዲችሉ።



**መ)** የሚኖሩበትን ስፍራ ንጹህ አድርገው በጥሩ ሁኔታ ያቆዩ። የኪራይ ውልዎንም ይረዱ እንዲሁም በሚገባ ያክብሩ።

መልሶች፡ 1 (ሐ)፤ 2 (ለ)፤ 3 (መ)፤ 4 (ሀ)




5\. በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉ አዋቂ ሰዎች ነጻ የቋንቋ ትምህርት መማሪያ ክፍል እንዲሳተፉ መርዳት።



6\. በሚኖሩበት ግዛት ወይም አካባቢ ያለውን የትምህርት ስርዓት እንዲገነዘቡ ማገዝ። በቤተሰብዎ ያሉ ልጆች ትምህርት ቤት እንዲገቡ መርዳት።



7\. የባንክ የሂሳብ መለያ/ቁጥር እንዲከፍቱ መርዳት። እንዲሁም በካናዳ ገንዘብን እንዴት ማግኘት እና መጠቀም እንደሚቻል ማስረዳት።



8\. በካናዳ ያሉ ወሳኝ ሕግ እና ደንቦችን ማብራራት።



ሠ) የባንክ መረጃዎችዎን በጥንቃቄ ይያዙ፡፡ ከባንክ ዱቤና ከብድር/ክሬዲት ካርድ ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን ይክፈሉ፡፡




ረ) የእንግሊዘኛ ወይም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታዎን ለማሻሻል በቋንቋ ትምህርት መሳተፍ።



ሰ) በካናዳ ያሉ ሕግ እና መመሪያዎችን መከተል።




ሸ) በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉ ልጆችን ትምህርት ቤት ማስገባት። የትምህርት እንዲሁም ማኅበራዊ እድገታቸው ላይ ያለውን ለውጥ መከታተል።

መልሶች፡ 5 (ረ)፤ 6 (ሸ)፤ 7 (ሠ)፤ 8 (ሰ)



**9.**

አስቸኳይ ሕክምና እርዳታ ከተፈለገ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ መርዳት



**ቀ)** ራስዎን ችለው የሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም እና ምንአልባት እንዳይጠፉ አስፈላጊ የሆኑ አድራሻዎችን ማወቅ።



**10.**

በአዲሱ ማኅበረሰብዎ ውስጥ ያለውን የሕዝብ ትራንስፖርት እንዴት መጠቀም እንዳለብዎ ማብራራት።




**በ)** በሚኖሩት አዲሱ ማኅበረሰብ ውስጥ ተግባቢ መሆን እና ከሰዎች ጋር መቀራረብ።



**11.**

ስለሚኖሩበት አዲሱ ማኅበረሰብ ገለጻ መስጠት።




**ተ)** ሰነዶችዎን በጥንቃቄ መያዝ፣ እንዴት መጠቀም እንዳለብዎት እና ጊዜው ሲደርስ እንዴት ማደስ እንዳለብዎ ማወቅ።




**12.**

በካናዳ የሚያስፈልግዎን ሰነዶች ለመጠየቅ መማልከቻ እንዲስገቡ መርዳት እና ጠቀሜታቸውን ማስረዳት።




**ቸ)** ስለሚያስፈልግዎ የሕክምና እርዳታ፣ አለርጂ ከሆኑና እና ልዩ የአመጋገብ ፍላጎትን በተመለከተ ለሚያምኑት ሰው ማሳወቅ።




**ከሁለቱ አስቸኳይ የሰፈራ ድጋፎች የትኞቹ ለእርስዎ እጅግ አስፈላጊ ናቸው?**

መልሶች፡ 9 (ቸ)፤ 10 (ቀ)፤ 11 (በ)፤ 12 (ተ)

## 3.6 መዳረሻን መቀየር

በካናዳ መኖር የሚፈልጉበትን ቦታ የመምረጥ መብት አለዎት። ሆኖም መጀመሪያ ሊሄዱ ወደነበረበት ስፍራ እንዲሄዱ ይበረታታሉ። በዚያ በሰፈራ ፍላጎትዎ መሠረት ድጋፍ ያገኛሉ። ቦታ ከመቀየርዎ በፊትም እነዚህን ነጥቦች ከግምት ያስገቡ፤





1. ወደ ሌላ አካባቢ ሊቀይሩ ከፈለጉ፣ በተቻለ ፍጥነት ለጋሾችዎን ወይም በመንግሥት የሚደጎሙ ድርጅቶችን ማሳወቅ አለብዎት፤ ይህ ሲሆን የሚያገኙት የገንዘብ እንዲሁም የኑሮ ድጋፍ እንዳይቋረጥ ያደርጋል።



2. ቦታ ሊቀይሩ ከወሰኑ እና ከመረጡ ለመቀየር የሚያስፈልግዎን ወጪ የሚሸፍኑት እርስዎ ነዎት። ይህም የማረፊያ ስፍራን እና የትራንስፖርት ወጪን ይጨምራል።




3. በአዲሱ ማረፊያዎ ሲደርሱ ለሚኖረው ሁኔታ እና ጊዜያዊ መኖሪያዎን በሚመለከት ቀድመው መዘጋጀት ይኖርብዎታል።



GAR/RPG

4. የድጋፍ ገንዘብን ለመቀበል የተወሰነ መዘግየት ሊኖር ይችላል።



PSR/PPPR

5. ለጋሾችዎ በሚኖሩበት ማኅበረሰብ የማይኖሩ ከሆነ፣ የገንዘብም ሆነ የኑሮ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ላይሆኑ ይችላሉ።


## 3.7 ከሊጋሾችዎ ጋር ያለዎት ግንኙነት

**መመሪያ:** በሊጋሾችዎ ዙሪያ ቅሬታ ከተሰማዎት መውሰድ ያለብዎትን እርምጃ ያንብቡ። እነዚህን እርምጃዎች ከ**1** እስከ **3** ቁጥሮችን በሳጥኑ ውስጥ በማስቀመጥ ቅደም ተከተል ይስጧቸው።



PSR/PPPR

ሀ) ☐




እርስዎ እንዲሁም ሊጋሾችዎ መፍትሔ ለማግኘት ከካናዳ መንግስት እርዳታን መጠየቅ ይችላሉ። ለመንግስት በኢሜይል አድራሻ IRCC.PSR-CaseReview-RevuedecasPSR.IRCC@cic.gc.ca ላይ ኢሜይል ይላኩ።

ለ) **1**



ያለመግባባት ካለ ከሊጋሾችዎ ጋር በመነጋገር እና በመጠየቅ ችግሩን ለመፍታት መሞከር።

ሐ) ☐



በአካባቢዎ ላሉ አዲስ መጪዎች በመንግስት ወደሚደገም ድርጅቶች ይሂዱ። በዚያ ያለ የነዋሪነት ጉዳይ ባለሞያ ጠቃሚ ምክሮችን ሊሰጥዎ ይችላል።


**PSR/PPPR: ሊጋሾችዎ እርስዎን ገንዘብ ሊጠይቁዎ ወይም ሊጋሽ ለማግኘት ቅድመ ክፍያ መክፈል አለብዎት ማለት አይፈቀድላቸውም። ካናዳ ሲመለሱ ገንዘብዎ እንደሚመለስልዎት ቃል ቢገባልዎት እንኳ ምንም አይክፈሉ። ሊጋሾችዎ በሕጉ መሠረት ለእርስዎ የተወሰነ ገንዘብ እንዲሰጡ ይገደዳሉ።**



መልሶች፦ (ሀ) 3፣ (ለ) 1፣ (ሐ) 2


## 3.8 በካናዳ ጠቃሚ ሰነዶች

ማንነትዎን የሚገልጹ ሰነዶች የእርስዎ ናቸው። ማንም ቢሆን፣ ለጋሾችዎ፣ የስፈራ ፕሮግራም ሠራተኞች፣ የቤተሰብ አባላት ወይም ቀጣሪዎም ቢሆኑ፣ ሰነዶችዎን መያዝ የለባቸውም። በካናዳ አዲስ ቋሚ ነዋሪ እንደሆነ ሰው፣ ወደ ካናዳ በደረሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከታዮቹን ጠቃሚ ሰነዶች መያዝ አለብዎት፡





### 1. የቋሚ መኖሪያ ካርድ

ይህ በካናዳ ቋሚ ነዋሪ መሆንዎን የሚያሳይ ሕጋዊ ማረጋገጫ ነው። ይህ ሰነድ በፖስታ ቤት የሚላክልዎ ይሆናል። ይህ ሰነድ ካናዳ ሲደርሱ የሚፈርሙትን የቋሚ ነዋሪነት ማረጋገጫዎን ግን የሚተካ አይደለም። ሁለቱንም ሰነዶች በጥንቃቄ መያዝ አለብዎት።




### 2. የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SIN/NAS)

ይህ ቁጥር በካናዳ ሥራ ለመሥራት እንዲሁም የመንግስት የድጋፍ ፕሮግራሞች ላይ ለማመልከት ያስፈልጋል። ይህን ቁጥር በጥንቃቄ ይያዙ፣ እናም ሌሎች እንዲጠቀሙበት አያድርጉ። ለበለጠ መረጃ ይህን ይህንን ያንብቡ፤




### 3. ክልላዊ የጤና ካርድ


በሚኖሩበት ግዛት ወይም ክልል የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት የጤና መድኅን ካርድ ያስፈልግዎታል። ይህ ካርድ ለእርስዎ ጥቅም ብቻ ነው። ወደ ካናዳ እንደደረሱ በተቻለ ፍጥነት የጤና ካርድ ለማግኘት ያመልክቱ።



**ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶችን ቅጂ/ኮፒ ያድርጉ እና በጥንቃቄ ያስቀምጧቸው። ሰነዶችዎ ቢጠፉ ወይም ቢሰረቁ ለመተካት ክፍያ መፈጸም ሊኖርብዎ ይችላል።**



# 3.9 በመንግስት የሚደጎሙ ድርጅቶች ለሁሉም አዲስ መጪዎች




እነዚህ ድርጅቶች በሌላ ስማቸው ‹የሰፈራ ኤጀንሲዎች› ተብለው የሚጠሩ ሲሆን በካናዳ የተለመዱ እና የታወቁ ናቸው። ሁሉም አዲስ መጪዎች በሚገቡበት ማኅበረሰብ ውስጥ ተረጋግተው ኑሮዋቸውን እንዲጀምሩ ሁሉንም አዲስ መጪዎችን ይረዷቸዋል። እንደ ቋሚ ነዋሪ፣ የካናዳ ዜግነትን እስኪያገኙ ድረስ የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች በነጻ የሚሰጡ ናቸው። በተከታዮቹ መንገዶች ሊረድዎት ይችላሉ፤




1. ለነጻ የቋንቋ ትምህርት እንዲመዘገቡ (እንግሊዘኛ/ፈረንሳይኛ)።



2. ሥራ እንዴት መፈለግ እንደሚችሉ ማወቅ።




3. ለማስረጃዎችዎ እንዴት እውቅና ማግኘት እንደሚችሉ ማማከር።



4. ብቃትዎን ለማሻሻል ከእርስዎ ጋር ይሠራሉ።



5. ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ።




6. የመኖሪያ ሁኔታ ላይ የሚገጥሙ ችግሮችን መፍታት።

የካናዳ መንግሥት የቀጥታ ድረገጽ መሣሪያን በመጠቀም ለአዲስ መጪዎች በመንግሥት የሚደጎሙ ድርጅቶችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፤



የሰፈራ አገልግሎቶች በፈረንሳይኛም ይገኛሉ። አስቸኳይ እንዲሁም የረጅም ጊዜ የመኖሪያ ድጋፍ የሚያቀርቡ በመንግሥት የሚደጎሙ ድርጅቶች በማኅበረሰቡ ካሉ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ተቋማት ወይም የፈረንሳይ አገልግሎቶች ጋር ሊያገናኝዎ ይችላሉ።

ለአዲስ መጪዎች ከፈረንሳይኛ ጋር በተያያዘ የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ተከታዮቹን ይመልከቱ፤




1. Carte interactive sur les collectivités francophones ያንብቡ፤




2. የካናዳ መንግስት ድህረ ገጽን ያንብቡ፡




3. በኲቤክ ያለውን አገልግሎት በሚመለከት፣ የኲቤክ መንግሥትን የቀጥታ የድረገጽ ላይ መሣሪያዎችን ይህንን በመጠቀም ያንብቡ፡፡

በመንግሥት የሚደጎሙ ድርጅቶች በሙሉ አዲስ መጪዎችን የመደገፍ ግዴታ አለባቸው። ምስጢርዎን መጠበቅ አለባቸው። እርስዎን በሚመለከት መረጃዎችን ለሌሎች ከማጋራታቸው በፊት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የሚያምኑትን ሰው ሲያገኙ፣ ያለዎትን ማንኛውንም ስጋት እንዲሁም ችግር ያጋሯቸው።



# 3.10 የሰፈራ ሁኔታ

**መመሪያ:** የሰፈራ ሁኔታውን በተመለከተ ያንብቡ። በየአንዳንዱ ሁኔታ እና በቀረቡ የመፍትሔ ምክረ ሐሳቦች መካከል በማስመር ያዛምዱ፤



**1.** አዲሱ ቤትዎን በሚመለከት ብዙ ችግሮች አሉ።



**2.** የካናዳ አየር መንገድ ቢደርሱም አቀባበል የሚያደርግልዎ ማንም የለም።



**3.** ለአንድ ሳምንት ያህል በመንግስት ከሚደጎሙ ድርጅቶችም ሆነ ከለጋሾችዎም ምንም የሰሙት ነገር የለም። አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማግኘት፣ የቋንቋ ትምህርት ለመጀመር እንዲሁም ልጆችን ትምህርት ቤት ለማስገባት ማመልከቻ ማስገባት ይፈልጋሉ።




**4.** በሌላ ግዛት ወይም አካባቢ ጓደኛ አለዎት። በቶሎ ወደዚያ ግዛት ወይም አካባቢ እንዲቀይሩ ይፈልጋሉ።



**ሀ)** ወደ የአየር መንገዱ እንግዳ መቀበያ በማቅናት አገልግሎቱን የሚሰጡ ሠራተኞች እንዲያግዝዎ መጠየቅ ወይም የድርጅቱ IOM ቦርሳ ማሳየት።



**ለ)** መኖሪያ ቦታ ለመቀየር ከመወሰንዎ በፊት ያንን ተከትሎ የሚመጣው ምንድን ነው የሚለውን በሚመለከት በመንግስት ድጎማ ከሚያገኝ ድርጅት ወይም ከለጋሾችዎ ምክር መቀበል።



**ሐ)** በመንግስት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ ጋር በመደወል ችግሮችዎን በትህትና ያስረዱ።



**መ)** ይደውሉላቸው፣ ሁኔታውን ያስረዱ እናም ለቀጠሮ ቀን እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።

መልሶች፡ 1 (ሐ)፤ 2 (ለ)፤ 3 (መ)፤ 4 (ሀ)

# 3.11 በማኅበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የረጅም ጊዜ የኑሮ ድጋፍ አገልግሎቶች

ብዙ ማኅበረሰቦች፣ ቋሚ ነዋሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ሰው የተለያዩ አገልግሎቶችን በነጻ ወይም በዝቅተኛ ወጪ ማግኘት እንዲችል አድርገዋል። አዲሱ ማኅበረሰብዎ እነዚህን ዓይነት ሁሉንም ወይም ጥቂት ብቻ የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችን ሊኖረው ይችላል።

***መመሪያዎች:*** የረጅም ጊዜ የመኖሪያ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ አገልግሎት እና አገልግሎቱ በሚገኝበት ቦታ መካከል በማስመር ያዛምዱ፤

ነጻ ኮምፒዩተሮች፣ በይነመረብ፣ መጽሐፍት፣ ጋዜጣ፣ ሙዚቃ እና ፊልሞች ተደራሽ መሆን። የተለያዩ በቡድን የሚከወኑ ፕሮግራሞች አሉ።



**1.**

የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እና ጊዜ ማሳለፊያዎችን መተግበር።



**2.**

በአካባቢዎ ካለ ሰው ጋር በመንሸራሸሪያዎች መገናኘት እና መተዋወቅ። ልጆች ከቤት ውጪ ባለ መጫወቻ ስፍራ ሊጫወቱ ይችላሉ።




**3.**

እምነትዎን ከተለያዩ ሰዎች ጋር መተግበር።



**4.**

ከተለየ ሀገር ከመጡ ወይም የተለያየ ባህል ካላቸው ሰዎች ጋር መተዋወቅ።



**5.**

እንግሊዘኛ እና/ወይም ፈረንሳይኛ በነጻ ማጥናት፣ እንዲሁም የካናዳን ባህል መማር እና አዳዲስ ሰዎችን መተዋወቅ። በአንዳንድ ክልሎች እና ግዛቶች፣ የቋንቋ ትምህርት ሲከታተሉ የገንዘብ ድጋፍ ይቀበላሉ።




**6.**

የካናዳን ታሪክ፣ ባህል እና ጥበብን በሚመለከት ይማሩ።



**7.**



**ሀ) የሕዝብ መናፈሻዎች**




**ለ) የባህል ማዕከላት**



**ሐ) የሕዝብ ቤተመጻሕፍት**



**መ) ቤተመዘክሮች**



**ሠ) የማኅበረሰብ ማዕከላት**



**ረ) የአምልኮ ስፍራዎች**




**ሰ) በመንግስት የሚደጎሙ የቋንቋ መማሪያ ማዕከላት**

መልሶች፦ 1 (ሐ)፤ 2 (ሠ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ረ)፤ 5 (ለ)፤ 6 (ሰ)፤ 7 (መ)

ከከፋዎ፣ ሐሳብ ከገባዎ ወይም ጭንቀት ከተሰማዎ ከሰዎች ጋር ያውሩ። ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ የሚያስችል ነጻ፣ ምስጢራዊ እንዲሁም ፍርጃ ያልታከለበት አገልግሎት ነው።



8.

ከገንዘብ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን ጠይቁ።



9.

በሚኖሩበት አዲስ ማኅበረሰብ ውስጥ ከትምህርት እንዲሁም ሥራ ጋር በተገናኘ የረጅም ጊዜ የመኖሪያ ድጋፍ እንዲያገኙ ይጠይቁ።




10.

ከሕግ ጋር በተገናኘ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ምክር ይጠይቁ።



11.

የሥራ ልም ለማጻፍ፣ ሥራ ለመፈለግ እንዲሁም ለሥራ ቃለመጠይቅ ለመዘጋጀት የሌሎችን እርዳታ ያግኙ።





12.

ከመንግሥት እና/ወይም ከለጋሾች የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልግዎትን ምግብ ለመግዛት በቂ ካልሆነ፣ ነጻ ምግብ ይቀበሉ።



13.


አደገኛ ሁኔታ በሚከሰት ጊዜ ደኅንነት ያለበት ቦታ ከፈለጉ ማደሪያ ያግኙ።



14.



ሸ) ሕጋዊ እርዳታ የሚሰጡ ክሊኒኮች



ቀ) መጠለያዎች እና ደኅንነት ያለባቸው ቦታዎች




በ) ባንኮች



ተ) ነጻ የአእምሮ ጤና ክሊኒኮች



ቸ) የሥራ ቅጥር ማዕከላት



ኀ) በመንግስት የሚደገሙ ድርጅቶች ለአዲስ መጪዎች



ነ) የምግብ ባንኮች

መልሶች፡ 8 (ተ)፤ 9 (በ)፤ 10 (ኀ)፤ 11 (ሸ)፤ 12 (ቸ)፤ 13 (ነ)፤ 14 (ቀ)

## 3.12 መረጃ የሚገኝባቸውን ነጻ ምንጮች የት ማግኘት ይቻላል?

**1.** ይፋዊ መረጃ በካናዳ መንግሥት እና መንግሥታዊ አገልግሎቶች

Government of Canada / Gouvernement du Canada


በwww.canada.ca ወይም በ 1-888-622-6232(የካናዳ አገልግሎት ማዕከል) መደወል፤

**2.** በፌዴራል፣ በግዛት እንዲሁም በየክልሉ ለአዲስ መጪዎች ተጠቃሚነትን የሚመለከት መረጃ



www.benefitsfinder.services.gc.ca

**3.** አምቡላንስ፣ ለእሳት አደጋ ወይም ፖሊስ የሚያገኙበት ስልክ ቁጥር





911 ላይ ይደውሉ

**4.** እንደየአገልግሎት ዘርፉ ነጻ፣ ምስጢራዊ፣ ብዙኀ ቋንቋ ያለው መረጃ በቀን 24 ሰዓት የሚያገለግል




211 ላይ ይደዉሉ

**5.** በማኅበረሰብዎ ውስጥ በነጻነት እንዴት መንቀሳቀስ ይቻላል የሚለውን የሚመለከት



ካርታዎች

**የእሳት አደጋ አጥፊዎችን፣ አምቡላንስ ወይም ፖሊስ ለማግኘት 911 ላይ ይደውሉ።**




ምዕራፍ 3 - ድጋፍ እና አገልግሎቶች

# ምዕራፍ 4
# መኖሪያ ቤት




# ምዕራፍ 4
# መኖሪያ ቤት



## 4.1 ጊዜያዊ ማረፊያ

በመንግስት የሚደጎመው ድርጅትም ሆነ ለጋሾችዎ ገና ካናዳ ሳይደርሱ በፊት የሚኖሩበትን ማረፊያ ቤት ሊያገኙልዎ ይተጋሉ። እንደሚኖሩበት ማኅበረሰብ ቋሚ መኖሪያ የማግኘት እድል፣ ለተወሰኑ ሳምንታት በጊዜያዊ ማረፊያ ሊቀመጡ ይችላሉ። እንደየሰፈራ ፕሮግራሙ፣ የጊዜአዊ ማረፊያ ዓይነቱም የተለያየ ነው።



ምቹ እና ቋሚ ቤት እንደተገኘልዎ፣ ከነበሩበት ጊዜያዊ ቤት መውጣት ይጠበቅብዎታል።

***መመሪያ:*** በካናዳ እንደሚኖሩበት የኑሮ ሁኔታ አንጻር፣ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት ያለው ፕሮግራም ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያድርጉ።



☐ **GAR/ RPG**



☐ **PSR/ PPPR**



☐ **JAS/ PAC**



☐ **BVOR/ RDBV**

***መመሪያዎች:*** የጊዜያዊ ማረፊያዎችን ዝርዝር ይመልከቱ። እንዳያሉበት የሰፈራ ፕሮግራም፣ ሊያርፉበት የሚችሉት የማረፊያ ስፍራ ዓይነት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያስቀምጡ።





☐ **1. የእንግዳ ማረፊያ ማዕከላት**

በ GAR/RPG ፕሮግራም ስር አዲስ መጪዎች በጋራ የሚያፍሩበት የአንድነት ማረፊያ። ክፍሎች መሰረታዊ ናቸው። አንዳንድ ማዕከላት የእጅ መታጠቢያቸው እንዲሁም የመመገቢያ ስፍራቸው የጋራ ነው።




## 2. የሆቴል ወይም የሞቴል ክፍሎች

መሰረታዊ ክፍሎች ያሉት፣ አብዛኛውን ጊዜ እያንዳንዳቸው ክፍሎች የራሳቸው መጸዳጃ ያላቸው፣ በመንግሥት በሚደጎም ድርጅት ወይም በለጋሾች የተከፈለበት።



## 3. ጊዜያዊ የኪራይ ማረፊያዎች

ይህም በቅርቡ ካናዳ ለደረሱ ሰዎች በመንግሥት የሚደጎመው ድርጅት ወይም በለጋሾች የሚከራዩት ቤት ነው። ብዙውን ጊዜም አዲስ መጪዎች እነዚህን ቤቶች ለሌሎች አዲስ መጪዎች እንዲለቁ ያስፈልጋል።



## 4. ሌሎች ጊዜያዊ ማረፊያዎች

ምቹ እና ቋሚ መኖሪያ ቤት እስኪገኝ ድረስ የለጋሽ ወይም የዘመድ ቤት ውስጥ የሚጋሩት ጊዜያዊ ማረፊያ።

**በጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ እያሉ፣ እንዲጠብቋቸው የሚገቡ ሕጎች አሉ። እነዚህም አካባቢያችሁን በንጽህ እና እና በጥሩ ሁኔታ መያዝ፣ እንዲሁም ሌሎችን አለመረበሽ ይጠበቅብዎታል።**

ምንጮች: GAR/RPG (1, 2, 3); PSR/PPPR (2, 3, 4); JAS/PAC (1, 2, 3); BVOR/RDBV (2, 3, 4)

# 4.2 በካናዳ ቋሚ መኖሪያ ቤት

በካናዳ ብዙ ወጪ የማያስወጣ ቤት ማግኘት ከባድ ነው። የቤት አማራጮችም የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ። በመንግሥት የሚደጎመው ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ ከፍላጎትዎ እንዲሁም ከገንዘብ አቅምዎ ጋር የሚመጣጠን የተወሰነ አማራጭ እንዲመለከቱ እና እንዲለዩ ይረድዎታል። ለአዲሱ ቤትዎም ቁሳቁሶችን እና ወሳኝ የቤት ውስጥ እቃዎችን በማሟላትም ያግዝዎታል።



**መመሪያ:** ሕንጻውን ተመልከቱ። ለቋሚ መኖሪያ ቤት ምሳሌ የሚሆኑ ሕንጻዎች ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።



☐ 1.




☐ 2.



☑ 3.



☐ 4.



☐ 5.



☐ 6.



☐ 7.



☐ 8.



☐ 9.

አንድን ቤት በቋሚነት በሚከራዩ ጊዜ ቦታ፣ ወጪ እና መጠን የሚባሉት ሦስት ነጥቦች ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጠቃሚ ጉዳዮች ናቸው።





መልሶች: 3፣ 4፣ 6፣ 7፣ 8 (✓)


# 4.3 በካናዳ የቋሚ መኖሪያ ቤት ዓይነት

**መመሪያ፡** በካናዳ ስላሉ የተለያዩ ዓይነት ቋሚ ቤቶች ያንብቡ።

## 1. አፓርትመንት



**ሀ) አጭር ቁመት ያላቸው የአፓርትመንት ሕንጻዎች፤**
እነዚህ ሕንጻዎች በጣም ከፍ ያሉ አይደሉም፣ ብዙውን ጊዜ አሳንሰር (ሊፍት) የሌላቸው ናቸው። እያንዳንዱ የፎቅ ወለል ከአንድ በላይ አፓርታማ ሊኖረው ይችላል።



**ለ) ረዥም ቁመት ያላቸው የአፓርትመንት ሕንጻዎች**
ረጃጅም እና በትልልቅ ከተማዎች የሚገኙ ናቸው። አሳንሰር አላቸው። በአንድ የፎቅ ወለል ላይ ከአንድ በላይ አፓርትመንት ሊኖራቸው ይችላል።



**ሐ) ባለሁለት ፎቅ አፓርትመንቶች**
ከመደብር ወይም ሬስቶራንት በላይ የሚገኙ ሲሆኑ፣ በርዝመት አጭር ወይም ረዥም ከሆኑት የአፓርትመንት ሕንጻዎች አንጻር ዋጋቸው የሚቀንስ ነው።



**መ) ከወለል በታች አፓርትመንቶች**
ከወለል በታች አፓርትመንቶች በካናዳ የተለመዱ ናቸው። በተወሰነ መልኩ ከወለል በታች ሲሆኑ፣ ለፀሐይ ማስገቢያ ትንንሽ መስኮቶች አሏቸው። ከወለል በታች አፓርትመንቶች ከሌሎቹ አንጻር ዋጋቸው ይቀንሳል።



**በካናዳ ያሉ አፓርትመንቶች ብዙ ጊዜ ከአንድ እስከ ሦስት መኝታ ቤቶች ያሏቸው ናቸው። አራት እና ከዚያ በላይ መኝታ ክፍሎች ያሏቸው አፓርትመንቶች ለማግኘት ውስን ከመሆናቸውም በላይ በዋጋም ውዶች ናቸው።**



ክፍል 4 - መኖሪያ ቤት

## 2. ቤቶች



**ሀ) ነጠላ ቤቶች**
ብዙውን ጊዜ በእነዚህ ቤቶች አንድ ቤተሰብ ብቻ ይኖርባቸዋል። እንዲህ ያሉ ቤቶች ለመግዛትም ሆነ ለመከራየት በጣም ውድ ሊሆኑ ይችላሉ።



**ለ) ተያያዥ ቤቶች**
ተያያዥ በሆኑ ቤቶች፣ እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ በር አለው፣ ግድግዳውን ግን ይጋሩታል። እያንዳንዱ ቤት በተለያዩ ሰዎች ባለቤትነት የተያዘ ወይም የተከራየ ሊሆን ይችላል።

## 3. ሌሎች ቋሚ ቤቶች



**ሀ) ተደራሽ የመኖሪያ ቤቶች**
እንዲህ ያሉ ቤቶች ራሳቸውን ለመንከባከብ እና ለመንቀሳቀስ የሚቸገሩ ሰዎችን የተለየ ፍላጎትን የሚያሟላ ነው።



**ለ) የጋራ መኖሪያዎች**
ይህ ደግሞ መኖሪያ ስፍራን የሚጋሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚከራዩት ነው። ብዙውን ጊዜም እያንዳንዳቸው የተለያየ የመኝታ ክፍል የሚኖራቸው ሲሆን፣ ከኪራዩ የድርሻቸውን ይከፍላሉ።

**ብዙ ቤተሰብ ላሏቸው ቤት ማግኘት አስቸጋሪ እና ከባድ ነው። በአንድ ቦታ ሊኖሩ ለሚችሉ ሰዎች ቁጥር ገደብ አለ።**




# 4.4 ከቤት ጋር በተገናኘ ጠቃሚ ቃላት


**መመሪያ:** ከመኖሪያ ቤት ጋር የሚገናኙ ቃላቶችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ቃላት እና በዝርዝሩ መካከል ያስምሩ።

1\. 

ተከራይ

2\. 


አከራይ

3\. 

መሣሪያዎች

4\. 

የተከራይ ዋስትና

5\. 

ጭስ ጠቋሚ

6\. 

ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት

ሀ) ለሌሎች ሰዎች ያከራየው ቤት ያለው ሰው።

ለ) በቤት ውስጥ ሥራ የሚያግዝ የኤሌክትሪክ ማሽን ነው። የሚከራዩ ቤቶች ብዙውን ጊዜ ይህን ያሟላሉ። የቤቱ ባለቤት ከሆኑት ትልልቅ መገልገያዎች ውጪ የሚከራዩ ቤቶች ብዙ ጊዜ የቤት እቃዎች የላቸውም።

ሐ) እሳት የተፈጠረ እንደሆነ አስቀድመው በፍጥነት የሚያሳውቁ እና ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ መሣሪያዎች።

መ) መኖሪያ ቤት የሚያከራይ ሰው።


ሠ) እንደ ዝርፊያ፣ ጥቃት ወይም እሳት ያሉ አደጋዎች እና ያልተጠበቁ ችግሮች ሲከሰቱ ለሚፈጠረው ኪሳራ የሚደረግ ክፍያ።

ረ) ያገለገሉ ፕላስቲኮች፣ ጣሳዎች፣ ወረቀቶች እና ጠርሙሶች የሚያስቀምጡበት። ብዙ ከተማዎች እነዚህን እቃዎች ሰብስበው ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ።

መልሶች: 1 (መ)፤ 2 (ሀ)፤ 3 (ለ)፤ 4 (ሠ)፤ 5 (ሐ)፤ 6 (ረ)

# 4.5 የመኖሪያ ቤት ሕጎች

እነዚህ ሕጎች የተከራይ እና የቤት ባለቤት/አከራይን የሚመለከቱ መብት እና ግዴታዎች ናቸው። እነዚህም በእያንዳንዱ ክልልና ግዛት የተለያዩ ናቸው።



**መመሪያ:** ጥያቄዎቹን ያንብቡ። መብት እና ግዴታዎች ናቸው ያሏቸው ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያስቀምጡ። አንዳንድ ጥያቄዎች ከአንድ በላይ መልስ አላቸው።





☑ ሀ) ተከራይ

**1.** የቤት ኪራይ በሙሉ እና በጊዜ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ማን ነው?

☐ ለ) አከራይ





☐ ሀ) ተከራይ

**2.** በጽሑፍ ማሳሰቢያ እና በተወሰነ ገደብ ብቻ፣ የቤት ኪራይ መጠን መጨመር መብት ያለው ማን ነው?

☐ ለ) አከራይ





☐ ሀ) ተከራይ

**3.** የመኖሪያ ቤቱን በንጽህና፣ በእንክብካቤ የማቆየት እና ደኅንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ የማን ኃላፊነት ነው?

☐ ለ) አከራይ





☐ ሀ) ተከራይ

**4.** የሕንጻውን ሕግ እንዲሁም እንደ ድምጽ ብክለትን መቀነስ የመሰለ የከተማውን ስርዓት ማክበር የማን ኃላፊነት ነው?

☐ ለ) አከራይ







☐ ሀ) ተከራይ

**5.** ሕንጻው ደኅንነቱ የተጠበቀ እና በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ ሆኖ እንዲቆይ የማድረግ ኃላፊነት የማን ነው?

☐ ለ) አከራይ

መልሶች፡ 1 (ሀ)፤ 2 (ለ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሀ)፤ 5 (ለ)






ሀ) ተከራይ

**6.** በተከራዩ የተደረጉ ጉዳቶችን የመክፈል ኃላፊነት የማን ነው?

ለ) አከራይ






ሀ) ተከራይ

**7.** የቤት እድሳት ለማከናወን የኪራይ ቤት ወዳለበት ለመግባት ፈቃድ የሚጠይቀው ማን መሆን አለበት?

ለ) አከራይ






ሀ) ተከራይ

**8.** ለመደበኛ ጥገና እና እድሳት እንዲደረግ የማስተባበር እና ክፍያ የመፈጸም ኃላፊነት ያለበት የማን ነው?



ለ) አከራይ


ሀ) ተከራይ

**9.** የኪራይ ውል ማቋረጥ ሲፈልግ አስቀድሞ ማን ነው ሕጉን መከተል ያለበት?

ለ) አከራይ

ሀ) ተከራይ

**10.** የቤቱን የመጀመሪያ ወር ኪራይ እንዲሁም የጉዳት ተቀማጭ ወይም ዋስትና መጠየቅ የሚችለው ማን ነው?

ለ) አከራይ



**አከራዩ የቤት ኪራይ የሚቀበል፣ ቤቱን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ለማስቻል የሚከታተል እንዲሁም ጥገናዎች መደረጋቸውን የሚያረጋግጥለት ሰው ሊቀጥር ይችላል። ይህ ተቀጣሪ ሰውም የንብረት አስተዳዳሪ ተብሎ ይጠራል።**




መልሶች: 6 (ሀ); 7 (ለ), 8 (ለ), 9 (ሀ, ለ); 10 (ለ)

# 4.6 የኪራይ ውል

የኪራይ ውል በተከራይና በአከራይ መካከል የሚደረግ የጽሑፍ ስምምነት ነው። ይህን ውል ከመፈረምዎ በፊት ማንበብ እና በሚገባ መረዳት አለብዎት።

ተከታዮቹ መረጃዎች በብዙዎቹ ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ ናቸው:





**በመንግስት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ሊጋሮችዎን በሚኖሩበት ግዛት/ክልል የመኖሪያ ቤት ጉዳይን የሚከታተለው አካል ማን እንደሆነ ይጠይቁ። ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ድርጅቱን ማግኘት ይችላሉ፤ ወይም የቤት አገልግሎትን በተመለከተ ቅሬታ ማስገባት ይችላሉ።**


# 4.7 በቤትዎ በደኅንነት መቆየት


በቤትዎ በደኅንነት ለመቆየት የሚያስችልዎ የተወሰኑ ጠቃሚ ነጥቦች ከታች ይገኛሉ። እነዚህን ነገሮች እንዴት ማድረግ እንደሚችሉም በመንግስት የሚደገሙ ድርጅቶችን ወይም ለጋሾችዎን መጠየቅ ይችላሉ።

***መመሪያ:*** በቤትዎ በደኅንነት ለመቆየት የሚያስችልዎትን ጠቃሚ ነጥቦች ያንብቡ። እርስዎ ካናዳ እንደደረሱ በመንግሥት ለሚደገመው ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ሊጠይቁ ያቀዷቸው የደኅንነት ጥንቃቄዎች ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያስቀምጡ።



1. በሮችን መቆለፍ






8. መሣሪያዎችን እንዴት በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚቻል እንዲሁም በቤትዎ አደጋ እንዳይከሰት ምን ማድረግ እንደሚችሉ መጠየቅ

2. የጭስ ጠቋሚው እየሠራ መሆኑን ማረጋገጥ እና የአደጋ ጊዜ መውጫዎች የት እንዳሉ ማወቅ












7. የተከራይ ዋስትና መግዛት

3. ጌጣጌጦች እና ውድ ዋጋ ያላቸው ነገሮችን ደኅንነቱ የተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ








6. በቤትዎ አካባቢ ያዩአቸው እና የተጠራጠሯቸው ሰዎች ካሉ ለሚመለከተው ማሳወቅ

4. ጎረቤቶችዎን ማወቅ

5. የማያውቋቸውን ሰዎች ወደ ውስጥ እንዲገቡ አለመፍቀድ


# 4.8 ቤትዎን በንጽህና መያዝ

ጤናማ ሆኖ ለመቆየት የሚኖሩበትን ስፍራ በንጽኅና መያዝ ወሳኝ ነው።

***መመሪያ:*** ቤትዎን ንጹህ በማድረግ እንዴት ጤናማ መሆን እንደሚችሉ ያንብቡ። አዲስ የሆኑብዎ የጽዳት ዓይነቶች ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያድርጉ።




1. ሁሌም ቆሻሻን መለየት፣ ማውጣት እና በሚሰበሰብ ቀን መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል መስጠት



2. መሬቱን መጥረግ እና መወልወል



3. በቤትዎ ያሉ ክፍሎችን ማጽዳት



4. ሳህኖችን ማጠብ



5. ልብሶችን እንዲሁም የአልጋ ልብሶችን ማጠብ



6. መጸዳጃ ቤቶችን፣ ሲንኮችን፣ ገንዳ እና መታጠቢያ ክፍሎችን ማጽዳት



7. የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ ዳይፐር እና መሰሎችን ከተጠቀምን በኋላ ሽንት ቤት ውስጥ ሳይሆን ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ መጣል



# ምዕራፍ 5
# ጤና



# ምዕራፍ 5


# ጤና



## 5.1 በካናዳ የሕዝብ የጤና አገልግሎት


እያንዳንዱ ክልልና ግዛት ለነዋሪዎቹ በመንግስት የሚደገፍ የህዝብ የጤና አገልግሎት ያቀርባል። ይህ አቅርቦት ከአንድ ክልልና ግዛት ወደ ሌላው ይለያያል። ብዙ ጊዜ በካናዳ የጤና አገልግሎት ሲያገኙ በቀጥታ ክፍያ መክፈል አይጠበቅብዎትም። ይህ አገልግሎት ሰዎች በሚከፍሉት ግብር የሚደጎም ነው።




ይህ በመንግስት የሚደገፍ የሕዝብ የጤና አገልግሎትን ለመጠቀም፣ የጤና ካርድ ያስፈልግዎታል። ከሚኖሩበት ግዛት ወይም ክልል የጤና ካርድ ለማግኘት ማመልከት ይኖርብዎታል። የጤና ካርድ ለማግኘት በቶሎ ማመልከቻ ለማስገባትም በመንግሥት የሚደጎም ድርጅት እና ለጋሾችዎ እንዲረድዎ ይጠይቋቸው።

አንዳንድ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ሙሉ ለሙሉ ሽፋን የሚያገኙ ሲሆን፣ ሌሎች በከፊል አንዳንዶቹ ደግሞ ጭራሽ ሽፋን የማያገኙ ናቸው። ሰዎች በቀጥታ እንዲከፍሉባቸው የሚፈለጉ የጤና እንክብካበቤ አገልግሎቶች መካከል ተከታዮቹ ይገኛሉ፤



1. በማዘዣ የሚደረግ መነጽር



2. የጥርስ ሕክምና



3. በማዘዣ የሚሰጡ መድኃኒቶች



4. የአምቡላንስ አገልግሎት



5. የተለየ የሕክምና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የሚሰጥ የቤት ውስጥ አገልግሎት


ለበለጠ መረጃ በመንግሥት የሚደጎመውን ድርጅት እና ለጋሾችዎን ይጠይቁ አልያም የክልሉን ወይም የግዛቱን ድረገጽ ይጎብኙ።።




1. እርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ አባል መካከል አንድ ሰው ሥራ ቢጀምር፣ ቀጣሪውን የሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት የማይሸፍነውን የጤና አገልግሎት ሽፋን ይሰጥ እንደሆነ ይጠይቁ።




2. በአንዳንድ ክልሎች ወይም ግዛቶች፣ የመድኃኒት አቅርቦት እና የጥርስ ሕክምና ለአንዳንድ ሰዎች በቅናሽ ዋጋ ወይም በነጻ ይቀርባል። በመንግሥት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን በጉዳዩ ዙሪያ ይጠይቁ።



3. በካናዳ፣ መቼ እና ምን ያህል ልጆች ሊኖርዎ እንደሚፈልጉ መምረጥ ይችላሉ። የቤተሰብ እቅድን በሚመለከት ከሕክምና ባለሞያዎች ጋር ይነጋገሩ። የራስዎ ሰውነት ነውና የራስዎ ምርጫ ነው።



4. ልጆች በተፈጥሮ ሁለት የጾታ ባህርያትን ይዘው ሲወለዱ በሕክምና አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ቀዶ ጥገና አይደረግላቸውም።



5. ሰዎች የስርዓተ ጾታ ማንነታቸው በተፈጥሮ ካገኙት የተለየ ከሆነ፣ ያንን እውን ለማድረግ ቀዶ ጥገና ማድረግ ሕጋዊ ነው።




**በማንኛውም ጊዜ በመንግስት የሚደገፍ የህዝብ የጤና አገልግሎት ሲያገኙ የጤና ካርድዎን ማሳየት አለብዎት። እንዲሁም የራስዎን የጤና ካርድ ይጠቀሙ፣ ካርድዎንም ለሌላ ለማንም ሰው አያውሱ።**




ክፍል 5 - ጤና

# 5.2 ጊዜያዊ የፌዴራል የጤና ፕሮግራም


በሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት ያለውን የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈጅብዎት ጊዜ፣ በካናዳ በሚኖሩበት አካባቢ ላይ መሠረት ያደረገ ነው።




ጊዜያዊ የፌዴራል የጤና ፕሮግራም (IFHP/PFSI) የጤና ካርድ እስኪያገኙ እንዲሁም በመንግስት የሚደገፍ የህዝብ የጤና አገልግሎት ማግኘት እስኪጀምሩ ድረስ ላለው የሕክምና አገልግሎት ሽፋን ይሰጣል። እንዲሁም ደግሞ ከመንግስት ወይም ከለጋሾችዎ የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኙ ወቅት፣ ተጨማሪ የጤና አገልግሎት ሽፋን ይሰጥዎታል። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፣





የ IFHP/PFSI የምስክር ወረቀትዎን ካናዳ ሲደርሱ ይቀበላሉ። ይህን ሰነድ በጥንቃቄ ይያዙ።



ይህን የምስክር ወረቀትም አገልግሎት ወይም የህክምና ምርቶችን በሚፈልጉ ጊዜ ለተመዘገበ የጤና እንክብካቤ ሰጪ ማቅረብ አለብዎት። በዚህም የጤና ሽፋን እንዳለዎት ማረጋገጥ ይችላሉ።

በጊዜያዊ የፌዴራል የጤና ፕሮግራም፣ የሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት ከሚሰጥዎት የጤና አገልግሎት ሽፋን በተጨማሪ ተከታዮቹን አገልግሎቶች ያገኛሉ፤



**1.** የተወሰነ የዐይን ሕክምና (የዐይን መነጽር በማዘዣ)








**4.** እንደ አምቡላንስ፣ የመድኃኒት ትዕዛዝ እና የማስተርጎም ያሉ ተጨማሪ አገልግሎቶች

**2.** አስቸኳይ የጥርስ ሕክምና




**3.** የአእምሮ ጤና አገልግሎት




ከካናዳ መንግስት እና/ወይም ከሊጋሾችዎ የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኙበት ወቅት እነዚህን ጥቅሞችንም ያገኛሉ። ይህ የጊዜያዊ የፌዴራል የጤና ፕሮግራም (IFHP/PFSI) ሽፋን ጊዜ ሲጠናቀቅ፣ ለእነዚህ ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶች ክፍያ እንዲፈጽሙ ይጠበቅብዎታል።

**ጊዜያዊ የፌዴራል የጤና ፕሮግራም (IFHP/PFSI) በሚጠቀሙ ጊዜ፣ የሚገኙት የሕክምና አገልግሎት ሽፋን የሚሰጠው ለየትኛው እንደሆነ መጠየቅ አለብዎት። ካልሆነ፣ እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይችላሉ ወይም በሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት ያለውን የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሽፋን እስኪያገኙ ይጠብቃሉ። በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ሊጋሾችዎ፣ የትኞቹ አገልግሎቶች በፕሮግራሙ ሽፋን እንደሚያገኙ እንዲለዩ ሊረድዎ ይችላሉ። የፕሮግራሙን የጤና ባለሞያዎች ለመመልከትም ይህንን ማገበብ ይችላሉ፤**



# 5.3 ለተለያዩ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ወዴት መሄድ ያስፈልጋል?

በካናዳ የተለያዩ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ።


**መመሪያ:** በካናዳ ያሉ የተለያዩ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ እንክብካቤ አቅራቢ እና በዝርዝሩ መካከል በማስመር ያዛምዱ።




የቤተሰብ ሐኪሞች



የማኅበረሰብ ጤና ባለሞያዎች




የድንገተኛ አደጋ ክፍሎች



ሆስፒታሎች

**1.**

**2.**

**3.**

**4.**

**ሀ)** አስቸኳይ እና ድንገተኛ የሆነ የጤና ጉዳይ ሲገጥምዎ የሚሄዱበት የሆስፒታል ክፍል ነው። እንደ ጤናዎ ሁኔታ ወደዚህ ቦታ በራስዎ አልያም 911 ላይ በመደወል በአምቡላንስ እርዳታ ሊደርሱ ይችላሉ።

**ለ)** ጠቅላላ የሕክምና እንክብካቤ ምክሮችን እና ሕክምናዎችን የሚሰጡ ባለሞያዎች ናቸው። በስፔሻሊስት እንዲታከሙ ሊመሩዎት ይችላሉ። ካናዳ ከመድረስዎ በፊት የተቀበሉትን የሕክምና እና የክትባት ውጤትዎን ያሳዩ።

**ሐ)** ከባድ የጤና ጉዳይ ሲገጥምዎ ወይም መመርመር እና ቀዶ ጥገና ማድረግ ሲያስፈግዎ የሚሄዱበት ግዙፍ የጤና እንክብካቤ ማዕከል።


**መ)** በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የቤተሰብ ሐኪም ወይም ተንከባካቢ ነርሶችን አገልግሎት ለማግኘት የሚሄዱበት።




**በካናዳ፣ የግል ጤና ጉዳይዎን በሚመለከት ማን ማወቅ አለበት የሚለውን የሚወስኑት እርስዎ ነዎት። ሌሎች እንዲሰሙት ካልፈቀዱ ወይም ራስዎ ካልገለጹ በቀር፣ ለሌሎች ሰዎች የሚነገር አይደለም። የጤናዎ ጉዳይ ላይ የመወሰን ኃላፊነት እና ድርሻ የራስዎ ነው።**



መልሶች፡ 1 (ለ)፤ 2 (መ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ሐ)


የመደበኛ አገልግሎት ክሊኒኮች

5\. **ሠ)** በተወሰነ የጤና ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ እና በዚያው ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ሥልጠና ያገኙ የሕክምና ባለሞያዎች። ብዙ ጊዜ የቤተሰብዎ ሐኪም ወደ እነዚህ የሕክምና ባለሞያዎች ሊመሩዎት ይችላሉ። አስቸኳይ ያልሆነ ሲሆን ግን እነዚህን ባለሞያዎች ለማየት ብዙ ወራትን ሊወስድ ይችላል።


ስፔሻሊስቶች

6\. **ረ)** ጥርስዎን በተመለከተ ችግር ሲኖር ሄደው ሊያናግሩት የሚገባ ባለሞያ ነው። እንዲህ ያሉ አገልግሎቶች ብዙ ጊዜ በመንግሥት በሚደጎሙ የጤና አገልግሎቶች አይሸፈኑም። ሆኖም ግን አንዳንድ የሕዝብ ጤና እንክብካቤ እቅድ፣ ለአስቸኳይ እና በሆስፒታል ውስጥ ለሚከወን የጥርስ ሕክምና ሽፋን ሊሰጥ ይችላል።


የጥርስ ሐኪሞች

7\. **ሰ)** ለሕይወት አስጊ ያልሆነ ግን ባሳሰበዎ የጤና ጉዳይ ምክንያት፣ የቤተሰብ ሐኪም ሳይኖርዎ ሲቀር ወይም የቤተሰብ ሐኪምዎ በቅርበት ባይገኝ የሚሄዱባቸው ናቸው። ለመሄድ እና ለመታከም ምንም ዓይነት ቀጠሮ ማስያዝ አይጠበቅብዎትም።


መድኃኒት ቤቶች

8\. **ሸ)** ከስሜት ጋር በተገናኘ ሕመም ሲሰማዎ ሊረዱዎ የሚችሉ ባለሞያዎች ናቸው። እንዲህ ያለ ችግር በየእለት ሕይወትዎ ውስጥ የሚገጥምዎ ከሆነ፣ ከባለሞያዎች እርዳታን ይጠይቁ።


የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች

9\. **ቀ)** የታዘዘልዎትን መድኃኒት ወይም ሌሎች ጤና ነክ ምርቶችን ለመግዛት የሚሄዱበት። በዚህ ስፍራ የሚገኙ የጤና እንክብካቤ ባለሞያዎችም መድኃኒቶች እና ሌሎችም ከትባቶችን በተመለከተ ያለዎትን ጥያቄዎች ሊመልሱልዎት ይችላሉ።




**በካናዳ የቤተሰብ ሐኪም ማግኘት ጊዜን ይወስዳል። ካናዳ እንደደረሱም በመንግስት የሚደጎሙ ድርጅቶችን ወይም ሊጋሾችዎን ይጠይቁ። በተመሳሳይ ጊዜ፣ አስቸኳይ ያልሆነ የጤና ስጋት ካለብዎት እና ሐኪም እንዲያክምዎት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ክሊኒኮች ወይም የማኅበረሰብ የጤና ማዕከላት ጋር መሄድ ይችላሉ።**



መልሶች፡ (ሠ) 5 ፤ (ረ) 6 ፤ (ሰ) 7 ፤ (ሸ) 8 ፤ (ቀ) 9

# 5.4 የሕክምና ቀጠሮዎች





ለሕክምና ቀጠሮ በሰዓቱ መገኘት አስፈላጊ ነው። አርፍደው ከደረሱ ሐኪም ሊያክምዎ ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። ያረፈዱት ክፍያ ሊፈጽሙበት ለሚገባ የሕክምና አገልግሎት ከሆነ፣ አገልግሎት አያገኙም፣ እንዲያም ሆኖ ግን ክፍያውን መፈጸም ይኖርብዎታል። ስለዚህም የሕክምና ቀጠሮዎን ለማስታወስ እንዲረዳዎ ሰዓት እና ቀኑን ይመግዝቡ።

**መመሪያ:** በካናዳ የእነዚህን ቤተሰቦች የሕክምና ቀጠሮ ተሞክሮ ይመልከቱ፤


1.



2.





3.





4.




5.




6.




# 5.5 የአእምሮ ጤና




የአእምሮ ጤና በሕይወት በሚኖረው ውጣውረድ መካከል የሚሰማዎ ሥሜት፣ ከሚያስቡት እና በተግባር ከሚገልጡት ጋር የሚገናኝ ነው። ንዴት፣ ጭንቀት እና ሐዘንን የሚቋቋሙበትን መንገድንም ያመላክታል።



**1.** ማንኛውም ሰው የአእምሮ ጤና ችግር ሊያጋጥመው ይችላል። በሁሉም የጾታ፣ እድሜ፣ የባህል እና የትምህርት ወይም የገቢ ሁኔታ ላይ ያለ ሰው ላይ ተጽእኖ ሊያደርስ ይችላል።



**2.** በየአመቱ በካናዳ፣ ከአምስት ሰዎች ውስጥ አንድ ሰው የአእምሮ ጤና ችግር ያጋጥመዋል።




**3.** እድሜው 40 ዓመት ከደረሰ ሕዝብ 50 በመቶ የሚሆነው የአእምሮ ጤና ችግር ገጥሞታል ወይም ይገጥመዋል።




**4.** በ211 በመደወል ወይም በቀጥታ የድረ-ገጽ ፍለጋ ምን ዓይነት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ያጣሩ። በዚህ እንዲያግዝዎ ከቤተሰብ ሐኪም፣ ነርስ ወይም ማኅበራዊ ዘርፍ ባለሞያ ጋር መነጋገር ይችላሉ። ወደ ካናዳ አዲስ መጪ የሆኑ ሰዎች የአእምሮ ጤናን እንዴት መከታተል ይችላሉ የሚለውን በሚመለከት ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ።




**5.** የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ልጆች፤ በስልክ ቁጥር 1-800-668-6868 ይደውሉ፤ ወይም ይህንን ያንብቡ፤

# 5.6 አዲስ መጪዎች የሚገጥማቸው አንዳንድ ፈተናዎች


**መመሪያ:** ወደ ካናዳ የገቡ አንዳንድ አዲስ መጪዎች የሚገጥማቸውን ፈተና ይመልከቱ። እርስዎም በካናዳ ሊገጥመኝ ይችላል የሚሉት ተግዳሮት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።




**1.** ደኅንነት የሌለበትን የዓለማችንን ክፍል እንዲሁም ቤት፣ ቤተሰብ እና ጓደኞችን ለመተው መገደድ





**2.** መኖሪያ ቦታ መፈለግ



**3.** አዲስ ጓደኞች ማፍራት




**4.** ሥራ ማግኘት



**5.** ቤተሰብን ማገዝ



**6.** በአዲስ ማኅበረሰብ ውስጥ ኑሮን መመሥረት



**7.** ከአየር ጸባዩ ጋር መላመድ



**8.** አዲስ ትምህርት ቤት መግባት

# 5.7 እርዳታ መቼ እንጠይቅ?

በአዲስ አገር ላይ ሕይወትን መጀመር ከባድ እና ለመረጋጋት ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ይችላል። ለመረጋጋት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የስሜት መለዋወጥ መኖሩ የተለመደ ነው። ሆኖም ግን እነዚህ ስሜቶች የእለት ተለት እንቅስቃሴዎ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ከሆነ፣ እርዳታ ይጠይቁ። በችግሮች ዙሪያ ከሌሎች ጋር ማውራት እና መነጋገር ራስን የማገዝ የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ተከታዮቹ ምልክቶች ሲሰማዎትም ሆነ በሌሎች ላይ ሲያስተውሉ፣ እርዳታን ይጠይቁ።



**1.** ማዘን እና ተስፋ ማጣት



**2.** መጥፎ ሕልም ማየት እና ቀድሞ የሆነውን ደጋግሞ ማሰብ




**3.** የምግብ ስሜት ማጣት



**4.** እንቅልፍ ማጣት



**5.** ድካም እና ዝለት




**6.** ብስጭት እና ቁጣ



**7.** በጣም ማሰብ ወይም መጨነቅ




**8.** ብቸኝነት፣ ራስን ማግለል ወይም በሐሳብ መዋጥ




**9.** ራስን የመጉዳት እና የመሞት ሐሳቦች

# 5.8 ሌሎችን እና ራስዎን እንዴት ሊረዱ ይችላሉ?


ሐዘን ከተሰማዎ ወይም ከተጨነቁ፣ ራስዎን ከዚያ ውስጥ ለማውጣት ወይም ሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ለማገዝ የሚረዱዎ ነገሮች አሉ። ይህንንም የሚጀምሩት በቅድሚያ ደስተኛ የሚያደርግዎን ነገር በማድረግ ነው።




**መመሪያ:** ተከታዮቹን ተግባራት ይመልከቱ። በካናዳ የተረጋጋ ኑሮ በመምራት ውስጥ ችግር ሲገጥምዎ ሊረዳኝ ይችላል የሚሉት ተግባር ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ " ✓ " ምልክት ያድርጉ።




**1.** ከሌሎች ጋር ወይም ለሌሎች ምግብ ማብሰል




**2.** ሌሎችን መርዳት




**3.** ከቤተሰብ እና ጓደኞች ጋር መገናኘት



**4.** ከቤት ውጪ ጊዜ ማሳለፍ




**5.** ጤናማ አመጋገብ መመገብ።
ለበለጠ መረጃ ይህን ያንብቡ፡፡



**6.** መጸለይ ወይም መመሰጥ




**7.** ስፖርቶችን መጫወት ወይም የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን ማድረግ




**8.** ከሚያምኑት ሰው ጋር ማውራት



**9.** በሕይወት በጎ ጎኖች ላይ ማተኮር




**10.** በባህልዎ የለመዷቸውን ተግባራት መከወን



**11.** የሚወዱትን ነገር ለማድረግ ጊዜ መስጠት፣ ለምሳሌ መጽሐፍ ማንበብ ሊሆን ይችላል ወይም አንዳች ነገር መፍጠር



**የአእምሮ ጤንነትዎ እንደ አካል ጤንነትዎ ሁሉ አስፈላጊ ነው፤ ሁለቱም ተያያዥ ናቸው። አካላዊ ሕመም ሲገጥምዎ የሕክምና እርዳታ እንደሚያስፈልግዎ ሁሉ፣ የአእምሮ ሕመም ሲገጥምዎዎም እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።**



# 5.9 ንጽህናን በመጠበቅ የጤና ችግርን መከላከል

ጥሩ የግል ንጽህና ራስንም ሆነ ሌሎችን ከበሽታ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው።


***መመሪያ:*** ተከታዮቹን የጤና ጉዳዮች ይመልከቱ። በእያንዳንዱ የጤና ጉዳይ እና በመከላከያ መንገዱ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.** **መጥፎ የአፍ ጠረን እና የጥርስ መበላሸት**



**2.** **ጉንፋን፣ ተቅማጥ እና ጥገኛ ተዋህስ**



**3.** **የበሽታ መሰራጨት**




**4.** **ቅማል/ቱሃን**



**ሀ)** ሕመም ሲሰማዎ የፊት ጭምብል መጠቀም፣ ሲያስነጥሱ እና ሲያስሉ አፍን መሸፈን እንዲሁም ከዚያ በኋላ እጅን በሚገባ መታጠብ



**ለ)** ልብስ፣ የጥርስ ብሩሽ እና ፎጣን ከሌሎች ሰዎች ጋር አለመጋራት



**ሐ)** ጥርስን በመደበኛ ወይም በየእለቱ በቀን ሁለት እና ሦስት ጊዜ መፋቅ እና በጥርሶች መሃል የሚገባውን በክር ማስወገድ



**መ)** እጅን ቢያንስ ለ20 ሰከንድ በሳሙና በየጊዜው መታጠብ፣ በተለይም መጸዳጃ ቤት ከተጠቀምን በኋላ እንዲሁም ምግብ ለመመገብ ከመቅረባችን በፊት

**በወር አበባ ጊዜ የንጽህና መጠበቂያ ምርቶች እንዲሁም የሕጻናት ዳይፐር ለግል ንጽህና በጣም ወሳኝ ናቸው። እነዚህም ቤት ውስጥ ወይም እንደ የሕዝብ መጸዳጃ ያሉ ለዚሁ የተሰየሙ ቦታዎች ላይ የሚወገዱ ናቸው።**



መልሶች፡ 1 (ሐ)፤ 2 (መ)፤ 3 (ሀ)፤ 4 (ለ)

# ምዕራፍ 6

# ትምህርት



# ምዕራፍ 6

# ትምህርት




## 6.1 ትምህርት በካናዳ

በሕጉ መሠረት በካናዳ የሚኖሩ ሕጻናት ትምህርት ማግኘት አለባቸው። እንደ ግዛቱ ወይም ክልሉ፣ ልጆች ትምህርት የሚጀምሩት እድሜያቸው ከ4 እና 6 ዓመት መካከል ሲሆን ትምህርታቸውንም የሚቀጥሉት እድሜያቸው ከ16 እስከ 18 እስኪደርስ ነው።






በካናዳ ክልሎች እና ግዛቶች ለትምህርት ተጠያቂነት አለባቸው። ስለዚህም እንደሚኖሩበት ግዛትና ክልል ልዩነት ሊኖር ይችላል ማለት ነው። በሚኖሩበት አካባቢ በሚኖረው ትምህርት ላይ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ ይህንን ያንብቡ፤




ካናዳ ሁለት ብሔራዊ ቋንቋዎች አሏት፤ እንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ። የመንግስት ትምህርት ቤቶች ብዙ ጊዜ በሁለቱም ቋንቋዎች ትምህርት ይሰጣሉ።

በእንግሊዘኛ ትምህርት ቤቶች፣ ትምህርቶች በእንግሊዘኛ ይሰጣሉ፤ ፈረንሳይኛን ደግሞ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ይሰጣል። በፈረንሳይኛ ትምህርት ቤቶች ደግሞ እንግሊዘኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ይሰጣል። ፈረንሳይኛን የሚያስገቡ ትምህርት ቤቶች ሁለቱንም ቀላቅለው ያስተምራሉ። ለበለጠ መረጃ በመንግስት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ይጠይቁ።

**‹ኩቤክ› የተባለችው ግዛት ብሔራዊ ቋንቋዋ ፈረንሳይኛ ነው። አዲስ መጪ ሕጻናት ትምህርቶች በፈረንሳይኛ በሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች እንዲገቡ ይደረጋል። በሌሎች ክልሎችና ግዛቶች በፈረንሳይኛ የሚሰጠውን ትምህርት በሚመለከት ይህንን ያንብቡ፤**



# 6.2 ለልጆች ያለው የትምህርት አማራጭ

***መመሪያ:*** በካናዳ ልጆችን ለማስተማር ያሉትን የተለያዩ አማራጮች ያንብቡ። እንደሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት ሊለያይ ይችላል። ካናዳ ከደረሱ በኋላ በመንግሥት የሚደጎመውን ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ለመጠየቅ ያቀዱት የትምህርት አማራጭ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ " ✓ " ምልክት ያድርጉ።




☐ **1. *የመንግሥት ትምህርት ቤቶች***

***ሀ)*** ይህ በካናዳ በብዛት ያለ የትምህርት ቤት ዓይነት ነው። ሰዎች በሚከፍሉት ግብር የሚደጎሙ ናቸው። በእነዚህ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥራት ያለው ትምህርት እየተሰጠ ስለመሆኑ እያንዳንድ ክልልና ግዛት ያረጋግጣል። መምህራንም በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው እና የመንግስትን ስርዓተ ትምህርት ሊከተሉ ይገባል።




☐ ***ለ)*** ***የተለዩ ትምህርት ቤቶች***

ይህም በማኅበረሰብ የሚደጎም ትምህርት ቤት ሲሆን፣ የሚገኘው በተወሰኑ ክልልና ግዛቶች ነው። እንዲህ ባሉ ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ የሮም ካቶሊክ ሐይማኖት ድርሻ አለው።




☐ **2. *የግል ትምህርት ቤቶች***

እነዚህ ትምህርት ቤቶች ቤተሰቦች ለተማሪዎች ትምህርት ክፍያ የሚፈጽሙባቸው ናቸው። አንዳንዱ የግል ትምህርት ቤት በመንግስት የተቀመጡ ሕጎችን ይከተላሉ። ሌሎች ደግሞ ተማሪዎቻቸው ምን እንደሚማሩ እና ማን እንደሚያስተምራቸው ይወስናሉ። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ሃይማኖት ድርሻ ሊኖረው ይችላል።





☐ **3. *በቤት ውስጥ ማስተማር***

አንዳንድ ቤተሰቦች ተማሪዎችን በቤታቸው ማስተማርን ይመርጣሉ። እንዲያም ሆኖ ልጆች ትምህርት እያገኙ መሆኑን ለማሳየት መመዝገብ አለባቸው። በዚህም ቤተሰቦች ብዙውን ወጪ የሚሸፍኑ ሲሆን ልጆች የሚማሩትን ይወስናሉ። በቤት ውስጥ የማስተማር ደንቦች እንደ ክልሉና ግዛቱ ይለያያል።


ትምህርትን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ የሚኖሩበትን ክልል ወይም ግዛት የትምህርት ሚኒስቴር ድረገጽ ይጎብኙ።

# 6.3 የመንግሥት ትምህርት በካናዳ

***መመሪያ:*** በካናዳ ስለተለመዱ እና መደበኛ ስለሆኑ የልጆች የትምህርት ሁኔታዎች ያንብቡ።



1. የካናዳ የትምህርት ዘመን ኦገስት መጨረሻ ወይም ሴፕቴምበር መጀመሪያ ላይ ጀምሮ ጁን ላይ ይጠናቀቃል፤ በመካከልም የእረፍት ጊዜ ይኖራል። ካናዳ የደረሱት የትምህርት ዘመኑ ከጀመረ በኋላ ቢሆን እንኳ ልጆችዎን ትምህርት ቤት ማስገባት ይችላሉ።



2. ሕዝባዊ አልያም የትምህርት ቤት በዓላት የዋሉበት ቀን ካልሆነ በቀር፤ በካናዳ ተማሪዎች ከሰኞ እስከ አርብ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ይጠበቃል።




3. ተማሪዎች በቀን ከ7 እስከ 8 ሰዓታት ድረስ ትምህርት ቤት ናቸው። በዚያ ጊዜም በሙሉ በትምህርት ቤት ውስጥ ይቆያሉ።



4. ፈረንሳይኛ ወይም እንግሊዘኛ መናገር የማይችሉ ቢሆኑ እንኳ፤ አዲስ መጪ ተማሪዎች በእድሜያቸው ሊገኙበት የሚገባ የክፍል ደረጃ ላይ እንዲገቡ ይደረጋል። ቋንቋ እንዲማሩ ተጨማሪ እርዳታ ይሰጣቸዋል።




5. አካላዊ፣ የምግባር ወይም የመማር ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ አለ። ይህ እርዳታ በትምህርት ቤት አልያም ከዚያ ውጪ ሊሰጥ ይችላል። ይህን በሚመለከት ካናዳ እንደደረሱ ከለጋሾችዎ፣ በመንግሥት ከሚደጎመው ድርጅት ወይም ከትምህርት ቤቱ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

# 6.4 በካናዳ መሠረታዊ የትምህርት ደረጃዎች

**መመሪያ:** እነዚህን የተማሪዎች የትምህርት ደረጃዎች ይመልከቱ። በአንዳንድ ክልሎችና ግዛቶች እነዚህ ደረጃዎች በተወሰነ መልኩ የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ።



**መዋዕለ ሕጻናት:** ከ3 እስከ 5 ዓመት እድሜ



**የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት:** ከ6 እስከ 10 ዓመት እድሜ (ከ1-5ኛ ክፍል)



**መካከለኛ ደረጃ ትምህርት:** ከ11 እስከ 13 ዓመት እድሜ (ከ6-8ኛ ክፍል)



**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት**
(ሃይ ስኩል): ከ14 እስከ 18 ዓመት እድሜ (ከ9-12ኛ ክፍል)



**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ**





**ትምህርት ቤት የሚገቡ ተማሪዎች ለተለያዩ ሕመሞች የሚሰጡ ክትባቶችን የወሰዱ መሆን አለባቸው። የክትባት መረጃን እያደሱ መቆየት አስፈላጊ ነው።**




# 6.5 በካናዳ ተማሪ መሆን

**መመሪያ፡** በካናዳ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪ መሆን ምን ይመስላል የሚለውን ያንብቡ። ከሚኖሩበት ከነበረው ሀገር አንጻር ለየት ብሎ ያገኙት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ " ✓ " ምልክት ያድርጉ።



☐ **1.** ተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) በተለምዶ አይለብሱም፡፡



☐ **2.** መምህሩ ወደ ማስተማሪያ ክፍል ሲገባ ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች ከወንበራቸው አይነሱም።



☐ **3.** የሚሰጣቸውን የቤት ሥራ ያለ ጾታ፣ ባህል ወይም ችሎታ ልዩነት በጋራ ይሠራሉ፣ እንዲሁም ያጠናሉ።



☐ **4.** ለተማሪዎች ቤታቸው ወስደው እንዲሠሩት የሚጠበቅባቸው የትምህርት ቤት ሥራ አለ። ይህም የቤት ሥራ ይባላል።



☐ **5.** ተማሪዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ በትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ጉዳት ሊደርስባቸው አይገባም/አይችልም። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሆነ ብለው ሌሎችን የሚጎዱ ላይ የሚወሰደው እርምጃ ከባድ ነው።



☐ **6.** የሁሉም ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ተማሪዎች በጋራ ይማራሉ፣ ሁሉንም ሃይማኖቶች እኩል ያከብራሉ።



☐ **7.** ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚመገቡትን ምግብ ከቤት ይዘው ይመጣሉ።




በርካታ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ አዲስ መጪ ቤተሰቦችን ለመርዳት የተመደቡ ሠራተኞች አሏቸው። እነዚህም አዲስ መጪ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች በካናዳ ያለው የትምህርት ስርዓት እንዴት እንደሚሠራ እና እንዴት ከዚህ ጋር አብረው ሊሄዱ እንደሚችሉ በማስረዳት የሚያግዙ ናቸው።





8. ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸው ግብዓት ይቀርብላቸዋል። ቤተሰቦችም እንደ ቦርሳ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ባይንደር እና የመሮጫ/የስፖርት ጫማ እንዲገዙ ይጠበቅባቸዋል።



9. ተማሪዎች ሰውነታቸው እንዴት እያደገ እና እየተለወጠ እንደሚሄድ ይማራሉ። ይህም የጾታ ትምህርት ይባላል። በዚህ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ትምህርት ቤቶችን ይጠይቁ።



10. ተማሪዎች እንደ አልኮል እና አደንዛዥ ዕጾችን በትምህርት ቤት እንዲጠቀሙ አይፈቀድላቸውም።



11. በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚማሩት በሐሳቦች ዙሪያ በመነጋገር፣ በቡድን በመሥራት እና ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው። በአብዛኛውም ተማሪዎች የተማሩትን እንዲሸመድዱ ብቻ አይጠየቁም።




12. ተማሪዎች ትምህርት የሚያገኙት በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ አልያም በሁለቱም ነው።



13. ከመማሪያ ክፍል ውጪ በሚኖሩ ተግባራት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። ለምሳሌ ስፖርት፣ በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ እና ወደ ቤተመዘክሮች በሚደረጉ ጉዞዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ መንገድ ነው ተማሪዎች ፍላጎት የሚፈጠርባቸው እና አዳዲስ ጓደኞችን የሚያፈሩት።



14. ተማሪዎችና መምህራን በብሔር/በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታ አገላለጽ እና ችሎታ ብዝኀነት ያላቸው እና የተለያዩ ናቸው።



**እርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ አባል መካከል ተማሪ የሆነ ሰው፣ ከላይ በተጠቀሱት በየትኛዎቹ ልዩነቶች ምክንያት ሊቸገር ይችላል? በጉዳዩ ላይ በሚኖርዎ ስጋት ዙሪያ በመንግስት ከሚደጎም ድርጅት ወይም ከሰጋሾችዎ ጋር ይነጋገሩ።**


# 6.6 ማስፈራራት/ጉልበተኝነት

ማስፈራራት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከሰት የአድልዎ ወይም የማግለል ዓይነት ነው። ይህም ከማንኛውም ስፍራ የመጡ ወጣት ልጆችን በአሉታዊ መንገድ ተጽእኖ የሚያሳድርባቸው ነው።



**1.** በቃላት ማስፈራራት፣ አንድን ሰው መሳደብ፣ ማስፈራራት ወይም ማማት ነው።







**4.** በበይነ መረብ የሚደረግ ምናባዊ ማስፈራራት፣ ማኅበራዊ ሚድያ ወይም የጽሑፍ መልዕክትን በመጠቀም ሌሎች እንዲበሳጩ፣ የበታችነት እንዲሰማቸው፣ ወሬ ለማዳረስ ወይም በአንድ ሰው ላይ መቀለድ ነው።

**2.** አካላዊ ማስፈራራት መምታት፣ መግፋት፣ መቆንጠጥ፣ ማባረር፣ መጣል ፣ ንብረትን ማበላሸት ወይም መስረቅ እንዲሁም አላስፈላጊ ጾታዊ ንክኪ ነው።



**3.** የስሜት ማስፈራራት፣ ቡድን ውስጥ እንዳይገቡ በመከልከል ወይም በሌሎች ፊት እንዲሸማቀቁ በማድረግ ሰዎችን መለየት ወይም መነጠል ነው።

**በሚያሳዝን ሁኔታ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ማስፈራራት/ጉልበተኝነት የሚታይ እውነታ ነው። በመላው ካናዳ ያሉ ትምህርት ቤቶች ይህን ችግር ለማስቀረት ጥረት እያደረጉ ነው። እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው ማስፈራራት የሚገጥምዎ ከሆነ ወይም ቢገጥመው ከሚታመን አዋቂ ሰው፣ መምህር፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ ጋር ያውሩበት።**



# 6.7 ቤተሰብ እና ትምህርት

ቤተሰቦች በልጆች ትምህርት ውስጥ ድርሻቸውን በመወጣት ድጋፍ እንዲያደርጉ እና እንዲያግዟቸው ይበረታታሉ። ይህም ተከታዮቹን ያካተተ ነው፤



1. የቤት ሥራቸውን እንዲሠሩ መርዳት




2. ከመምህራኖቻቸው ጋር መገናኘት እና መነጋገር



3. በትምህርት ቤቶች ውስጥ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት

በቤተሰብዎ ውስጥ ከ12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካሉ፣ ያለ አዋቂ ክትትል ለብቻቸው ሊተዉ አይገባም።

ለልጅ ክብካቤ ያሉ አማራጮች ተከታዮቹ ናቸው፤




1. የቤተሰብ አባል የሆኑ ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች እንዲጠብቋቸው ማድረግ



2. ፍቃድ ባለው የሕጻናት ማቆያ ወይም መዋለ ህጻናት እንዲገቡ ማድረግ



3. የሚታመን የቤት ውስጥ የሕጻናት እንክብካቤ የሚሰጥ ማቆያ መፈለግ



4. ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች እንዲጠብቋቸው መክፈል

**የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት እንደየክልሉና ግዛቱ የተለያየ ወጪ አለው። በአንዳንድ ክልሎችና ግዛቶች በቅናሽ ዋጋ በመንግስት የሚደጎሙ የሕጻናት ማቆያዎች አሉ። ለበለጠ መረጃ በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ይጠይቁ።**

## 6.8 የተማሪዎች ሁኔታ

**መመሪያ፡** የተማሪዎቹን ሁኔታ ያንብቡ። እርስዎ ወይም ከቤተሰብዎ መካከል የሚገኝ ተማሪ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ቢገኙ ምን እንደሚያደርጉ ይግለጹ።



**1.** ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት አልሄድም አለ።



**2.** እድሜው 15 ዓመት የሆነ ተማሪ የስፖርት ቡድንን ከተቀላቀለ በኋላ የትምህርት ውጤቱ አሽቆለቆለ።



**3.** አንድ ተማሪ በትምህርት ክፍል ውስጥ በጸጥታ ትምህርት መከታል ሲኖርበት መምህር ሲናገር ጣልቃ በመግባት እና እርስ በእርስ በማውራት ካስቸገረ።



**4.** የ17 ዓመት ልጅ የሆነ ተማሪ በሁሉም ጾታ ድግስ ላይ ከተጋበዘ።

## 6.9 አዋቂ ተማሪች

**መመሪያ፡** በካናዳ አዋቂ ሰዎች ለምን ትምህርት ቤት እንደሚገቡ ያንብቡ። እንደ አዋቂ እርስዎም በካናዳ ሊማሩ የሚፈልጉበት ምክንያት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።



☐ **1.** ያልጨረሱትን ትምህርት ለመጨረስ





☐ **2.** የእንግሊዘኛ እና/ወይ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታን ለማሻሻል



☐ **3.** የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ በማግኘት ችሎታን ለማሳደግ



**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ላላጠናቀቁ አዋቂዎች፣ ዲፕሎማ ለማግኘት የሚያግዛቸው ትምህርት አለ። እንዲህ ያሉ የትምህርት መስጫዎች መካከል አንዳንዶቹ አዋቂዎቹን ማንበብ እና መጻፍ ጭምር ያስተምራሉ፣ ሰዎቹ በራሳቸው ቋንቋ ሳይቀር ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉ ቢሆኑም ይህ ትምህርት ይሰጣቸዋል።**



# 6.10 የአዋቂዎች የቋንቋ ትምህርት

***መመሪያ:*** በካናዳ ቋሚ ነዋሪ ለሆኑ አዋቂዎች የሚሰጥ በመንግስት የሚደጎም የቋንቋ መማሪያን በሚመለከት ያንብቡ።




1. እንግሊዘኛ እና/ወይም ፈረንሳይኛ ለመማር የቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ይገኛሉ።




2. የቋንቋ ትምህርት ለመጀመር በመጀመሪያ ነጻ የቋንቋ ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋል። አንዴ ካናዳ ከገቡ በኋላ ግምገማው የት እና መቼ እንደሚካሄድ በመንግስት የሚደጎመው ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ይጠይቁ። ያሉበትን ደረጃ ለማወቅም ይህንን ያንብቡ፣ በሚያገኙት ፈተና ራስዎን ይገምግሙ።



3. ትምህርቶች የሙሉ ጊዜ፣ የትርፍ ጊዜ፣ ቀን ቀን የሚሰጡ፣ የማታ ወይም የቅዳሜ እና እሁድ ሊሆኑ ይችላሉ።




4. እነዚህ ትምህርቶች የሚያስተምሩት ከቋንቋም በላይ ነው። በካናዳ ስላለው ሕይወትም ይማራሉ።




5. የቋንቋ ትምህርት ወደሚከታተሉበት ሲያቀኑ የሕጻናት ማቆያ፣ የሕዝብ ትራንስፖርት ለመጠቀም የሚያስችል ትኬት ወይም ሌላ ድጋፍ የሚገኝ እንደሆነ ይጠይቁ።

## 6.11 ቋሚ ነዋሪዎች ለምንድን ነው የቋንቋ ትምህርት የሚወስዱት?


***መመሪያ፡*** ቋሚ ነዋሪዎች ለምን የቋንቋ ትምህርት እንደሚማሩ ያንብቡ። ለእርስዎም በካናዳ እንግሊዘኛ እና/ወይም ፈረንሳይኛ ለመማር ምክንያት የሚሉት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።



☐ **1.** ሥራ ለማግኘት



☐ **2.** አገልግሎቶችን በቀላሉ ለማግኘት



☐ **3.** የሕዝብ ትራንስፖርት በመጠቀም በአካባቢዎ ለመንቀሳቀስ



☐ **4.** ልጆችን በትምህርታቸው ለማገዝ



☐ **5.** በአካባቢዎ ወይም በማኅበረሰብዎ ካሉ ሰዎች ጋር ለመግባባት



☐ **6.** ዜግነት እንዲያገኙ የሚጠየቀውን የቋንቋ መመዘኛ መስፈርት ለማለፍ




☐ **7.** ትምህርትዎን ለመቀጠል


# 6.12 ለአዋቂዎች ያለው የትምህርት አማራጭ




1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ አዋቂ ተማሪዎች በኮሌጅ፣ በተቋማት ወይም በዩኒቨርሲቲ ገብቶ ለመማር መምረጥ ይችላሉ።



2. በእነዚህ ቦታዎች ለመግባት ምዝገባው ውድድር የሚጠይቅ ሲሆን፣ ያሉ ቦታዎችም ውስን ናቸው። ሁሉንም መስፈርት ማሟላትዎን እና በጊዜ ማመልከትዎን አይርሱ።



3. የሚማሩትን ከመምረጥዎ በፊት በአካባቢዎ ያለው የሰው ኃይል ገበያ/ፍላጎት ምን እንደሆነ የዳሰሳ ጥናት ያድርጉ። በካናዳ በሚገኙ ኮሌጆች፣ ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞችን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ፤



4. በካናዳ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ መያዝ ሥራ ለማግኘት ዋስትና አይደለም። ሆኖም ግን አንዳንድ ሥራዎች ለማመልከት ብቻ እንኳ ዲፕሎማና ዲግሪ ይጠይቃሉ።

ምዕራፍ 6 - ትምህርት

# 6.13 የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወጪዎች




እንደ ተቋማቱ እና እንደ ፕሮግራሙ ይዘት፣ የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወጪ ይለያያል።

ይህን ወጪ ለማስላት የሚረዳ የሥሌት መንገድን -888-815-4514 በመደወል አልያም ይህንን በማንበብ ማግኘት ይችላሉ



ለድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ እንደ ፍላጎቱ ሁኔታ የሚወሰን ነው። የገንዘብ ድጋፍ በተከታዮቹ ዓይነት መንገዶች ሊገኝ ይችላል፡



1. መክፈል ያለበት እና ከመንግስት የሚገኝ የተማሪዎች ብድር።



2. መልሰው መክፈል የማይጠበቅብዎ ስጦታ ወይም ነጻ የትምህርት እድል።



3. መክፈል የሚጠበቅብዎት እና ከባንኮች የሚገኝ የግል የተማሪዎች ብድር። የዚህ ብደር ደንብ እንደ መንግስት ብድር ጥሩ የሚባል አይደለም።

ለድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍን በሚመለከት ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፡

# 6.14 የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃዎች

**መመሪያ**: ለአዋቂዎች የሚሰጡ የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃዎችን ይመልከቱ። በአንዳንድ ክልሎችና ግዛቶች እነዚህ ደረጃዎች የተወሰነ ልዩነት አላቸው፤ "(crossed-out $)" ምንም ወጪ ለሌለው፣ " $ " ወጪው አነስተኛ ለሆነ፣ "$$" መካከለኛ ወጪ ለሚጠይቅ፣ እና " $$$ " ከፍተኛ ወጪ ላለው።

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ**

**ኮሌጅ**: ከ2 እስከ 3 ዓመት

$ - $$

**ቅድመ ዩኒቨርሲቲ**: (በኩቤክ ብቻ) 2 ዓመት ዩኒቨርሲቲ

(crossed-out $)

**በተቋማት**: ከ1 እስከ 3 ዓመት

$ - $$

**የመጀመሪያ ዲግሪ**: ከ3 እስከ 4 ዓመት

$$ - $$$


**ሁለተኛ ዲግሪ ወይም ማስተርስ**: ከ1 እስከ 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ

$$$

**የሦስተኛ ወይም ዶክትሬት ዲግሪ**: 3 ዓመትና ከዚያ በላይ


$$$

## 6.15 የትምህርት የምስክር ወረቀቶች ግምገማ ሂደት



ከካናዳ ውጪ የተማሩት የኮሌጅ፣ የተቋም ወይም የዩኒቨርስቲ ትምህርት በካናዳ እውቅና እና ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። በካናዳ ትምህርትን ለመቀጠል ወይም በአንዳች የሥራ ዘርፍ ገብቶ ለመሥራት፣ የቀድሞ ትምህርትዎ ላይ ግምገማ ይደረጋል። ይህን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ 416-962-9725 ላይ ይደውሉ ወይም ይህንን ያንብቡ፤

***መመሪያ:*** የትምህርት ማረጃዎች የሚመዘኑበትን አሠራር ሂደቶች ያንብቡ። ወደ ካናዳ ከመድረስዎ በፊት ሊጀምሩት የሚችሉት ሂደት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “✔” ምልክት ያስቀምጡ።



☐ **1.** በተቻለ መጠን ብዙ ሰነዶችን መሰብሰብ። እነዚህም ተከታዮቹን የሚያጠቃልሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤
- **ሀ)** ዲፕሎማ፣ ዲግሪ እና የምስክር ወረቀቶች
- **ለ)** የትምህርት ግልባጮች/ትራንስክሪፕት
- **ሐ)** የሥራ ታሪክ ማረጋገጫ
- **መ)** የቀጣሪ/ተቆጣጣሪ ማጣቀሻዎች



☐ **2.** የሚፈልጉትን የትምህርት ዘርፍ መለየት እንዲሁም መማሪያ ቦታ መፈለግ። የዚህንም የማመልከቻ እና የምዝገባ መስፈርቶችን ማወቅ።



☐ **3.** ምን ዓይነት የትምህርት ማስረጃ እንደሚቀበሉ ለማወቅ ከመመዝገቢያ/ማመልከቻ ቢሮ ጋር መገናኘት።




☐ **4.** የእንግሊዘኛ ወይም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ግምገማ ማድረግ ይጠበቅብዎ እንደሆነ ማጣራት።

**የትምህርት ማስረጃ ምዘናዎች ጊዜ ይወስዳሉ፣ የገንዘብ ወጪም አላቸው። በካናዳ የሥራ ልምምድ ለመከወን እንዲችሉ ማድረግ የሚጠበቅብዎትን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ።**



# ምዕራፍ 7

# ሥራ




# ምዕራፍ 7
# ሥራ

## 7.1 ሥራ በካናዳ


በካናዳ ራስን ለመቻል፣ ሥራ ማግኘት እና መሥራት ወሳኝ ነው።






በካናዳ ሥራ ለማግኘትም ሆነ አዲስ ሕይወትን ለመጀመር በእንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛ የቋንቋ ክህሎቶች አስፈላጊ ናቸው። ለአዲስ መጪዎች የቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ ምዕራፍ 6 ላይ ተግባር 6.10ን ይመልከቱ።



የካናዳ መንግስትም ሆነ በመንግስት የሚደጎመው ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ ካናዳ ሲደርሱ ሥራ ያገኛሉ የሚል ማረጋገጫ አይሰጥዎትም።



በካናዳ ሰዎች በተለያየ የሕይወታቸው ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት የመግባት ልማድ አላቸው። ይህንን የሚያደርጉት ክህሎታቸውን ለማደስ ወይም ለአዲስ የሥራ እድል ብቁ ለመሆን ስለሚፈልጉ ነው።



በመንግስት የሚደጎሙ ድርጅቶች ወይም ለጋሾችዎ ከሥራ ቅጥር ጋር የተገናኘ አገልግሎት ጋር እንዲያገናኙዎ ይጠይቁ።



# 7.2 በካናዳ ስለመሥራት ምን ይሰማዎታል?


**መመሪያ:** በካናዳ ሥራ ከመስራት ጋር የተያያዙ አካሄዶች እና ዕይታዎችን በሚመለከት ያንብቡ። የሚስማሙበት ከሆነ የ" ✓ " ምልክትን በ" 👍 " ሳጥን ውስጥ ያድርጉ። እርግጠኛ ካልሆኑ የ " ✓" ምልክትን በ" 🤷 " ሳጥን ውስጥ ያድርጉ። እንዲሁም የማይስማሙ ከሆነ የ " ✓" ምልክትን በ" 👎 " ሳጥን ውስጥ ያድርጉ።



1. የሚፈልጉትን ደመወዝ የሚከፍል ሥራን ብቻ ይቀበላሉ። ☐ 👍 ☐ 🤷 ☐ 👎



2. ካለዎት አቅም እና ችሎታ በታች ቢሆን እንኳን የሚቀርብልዎትን ሥራ ይቀበላሉ። ☐ 👍 ☐ 🤷 ☐ 👎



3. ራስዎ እና ቤተሰብዎን ለማገዝ ይሰራሉ። ሌሎች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉልዎ አይጠብቁም። ☐ 👍 ☐ 🤷 ☐ 👎





4. ቋንቋውን ለመለማመድ እና ሰዎችን ለመተዋወቅ ፍቃደኛ ነዎት፡፡ ☐ 👍 ☐ 🤷 ☐ 👎

# 7.3 በካናዳ ሥራ የሚሠራው ማን ነው?


**መመሪያ:** ሰዎቹን ይመልከቱ። በካናዳ ሥራ የመሥራት መብት ያላቸው ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ሰዎች ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ " ✓ " ምልክት ያስቀምጡ።



1. ☑


2. ☐



3. ☐


4. ☐



5. ☐



6. ☐



7. ☐


8. ☐


9. ☐


10. ☐


11. ☐


12 . ☐

ቀጣሪዎች ተቀጣሪዎቻቸውን ጾታን፣ እድሜን፣ ዘርን፣ የኑሮ ደረጃን፣ የትዳር እና የቤተሰብ ሁኔታን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ ብሔርን፣ የስደት ሁኔታን፣ ጾታዊ አረዳድን፣ አካል ብቃት ወይም ጉዳትን መሠረት አድርገው ፍትሐዊ ባለሆነ መንገድ እንዳይይዟቸው የሚከላከሉ ሕጎች አሉ።



መልሶች: 1(✓)፡ 2(✓)፡ 3(✓)፡ 4(✓)፡ 5(✓)፡ 6(✓)፡ 7(✓)፡ 8(✓)፡ 9(✓)፡ 10(✓)፡ 11(✓)፡ 12(✓)

# 7.4 ቤተሰብ እና ሥራ

**መመሪያ:** ተከታዩ ቤተሰብ በካናዳ ሥራን በሚመለከት የነበረው ዕይታ እና አስተሳሰብ እንዴት እንደተቀየረ ያንብቡ።

________________________________ን ይተዋወቁት።



ካናዳ ሲደርስ እርሱ 60 ዓመቱ፣ ልጁ ደግሞ 16 ዓመቷ ነበር። ከዚህ ቀደም በውጪ ሀገር ሥራ ሰርቶ የማያውቅ ሲሆን፣ እንግሊዘኛም ሆነ ፈረንሳይኛ ቋንቋ አይናገርም። እሱ በኖረበት ሀገር ሰዎች በ60 ዓመታቸው ጡረታ ይወጣሉ። በካናዳ ያለው ሁኔታ ግን ከዚያ የተለየ ነው።

በካናዳ እርሱ ለምን ሥራ ይሠራል?




1. በጥሩ የጤና ሁኔታ ላይ ስለሚገኝ እና ለአዲሱ ማኅበረሰብ አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚፈልግ።



2. ልጁ 18 ዓመት ሲሞላት ከካናዳ የልጆች ተጠቃሚነት የሚያገኘው ገንዘብ ስለሚቋረጥ።




3. ጡረታ ለመቀበል ብቁ ባለመሆኑ እና በእድሜ የገፉ ሰዎች ዋስትናን ለማግኘት ብዙ ዓመታትን መጠበቅ ስለሚጠበቅበት።



4. የ16 ዓመት ልጁ ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግባት እቅድ አላት። እናም እርሷን በትምህርት ወጪዎቿ ሊያግዛት ይፈልጋል።



5. ምንም ቁጠባ የለውም።


**የዚህ ቤተሰብ ሁኔታ ከእርስዎ ጋር ምን ዓይነት ተመሳሳይነት አለው?**

**መመሪያ:** ይህ ቤተሰብ በካናዳ ሥራን በሚመለከት የነበረው ዕይታቸው እንዴት እንደተቀየረ ይመልከቱ።

1.


2.


3.


4.



5.



6.


በካናዳ በሥራ ቦታዎች ሁሉም ሰው ያለ ጾታ ልዩነት እኩል መብት አለው። ለሰዎች ወይም ለሠራተኞች በጾታቸው ምክንያት ለተመሳሳይ ሥራ የተለያየ ክፍያ መስጠት ሕገወጥ ነው።



# 7.5 በካናዳ ያሉ የሥራ ዓይነቶች









1. **ቁጥጥር የማይደረግባቸው ሥራዎች**
   እነዚህ ሥራዎች ፈቃድ፣ የትምህርት ማረጋገጫም ሆነ ምዝገባ አይጠይቁም። እንደ ሥራ ሁኔታው መስፈርቱ ቢለያይም፣ በተወሰነ መልኩ የክህሎት ወይም የትምህርት ደረጃ ግን ሊጠይቁ ይችላሉ። በካናዳ ካሉ ሥራዎች ውስጥ 80 በመቶው ቁጥጥር የማይደረግባቸው ናቸው።

2. **ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሥራዎች**
   እነዚህ ሥራዎች ከሚኖሩበት ግዛት ወይም ክልል ቁጥጥር ከሚያደርግ አካል የተሰጠ ፈቃድ ይጠይቃሉ። ይህ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል የሕዝብ ወይም የመንግስት ድርጅት ሲሆን፣ ሥራን በተመለከተ ሕጎችን የሚያወጣ ነው። በካናዳ ካሉ ሥራዎች መካከል 20 በመቶዎቹ በዚህ ስር ይገኛሉ።

የእነዚህ ሥራዎች ምሳሌዎች፤




1. የጤና እንክብካቤ



2. የገንዘብ ተቋማት



3. የሕግ አገልግሎት




4. ማስተማር



5. ምህንድስ እና እና ኪነሕንጻ



6. የሂሳብ አያያዝ



7. የቤቶች ግንባታ



8. ማኅበራዊ ሥራ



9. የሙያ ሥራዎች (የኤሌክትሪክ ባለሞያ፣ የቧንቧ ሠራተኛ፣ ሜካኒክ)


ፈቃድ ለማግኘት ፈተና ማለፍ እና ለተቆጣጣሪው አካል ክፍያ መፈጸም ይኖርብዎታል።



## 7.6 በካናዳ የመጀመሪያ ሥራዎ

በካናዳ ብዙ ሰዎች የመጀመሪያ ሥራቸው ቁጥጥር የማይደረግባቸው ሥራዎች ናቸው። ይህ የመጀመሪያ ሥራ አንድ ሰው እስከ መጨረሻው የሚቆይበት ነው ማለት አይደለም። ዋናው ነገር ስራ መጀመሩ ነው።

**መመሪያ:** በሁሉም እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ በካናዳ የሚገኙ ሰዎች የሚሠሩትን የመጀመሪያ ሥራ ይመልከቱ። እርስዎም ራስዎን እና ቤተሰብዎን ለማገዝ እንዲረዳዎ ሊያመለክቱ ከሚችሉባቸው የመጀመሪያ ሥራዎ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።



**1.** ተላላኪ/መልዕክት አድራሽ




**2.** ገንዘብ ተቀባይ (ካሽር)




**3.** ጥበቃ (መሣሪያ አይዝም)




**4.** የግንባታ ሠራተኛ




**5.** አትክልተኛ



**6.** የጸጉር ቆራጭ




**7.** የመገጣጠም ሥራ የሚሠሩ



**8.** ልብስ ሰፊ (የወንድ፤ የሴት)




**9.** የጽዳት ሠራተኛ



**10.** የምግብ አገልግሎት ሠራተኛ



**11.** የክምችት ክፍል/ግምጃ ቤት ጸሐፊ



**12.** ተንከባካቢ

# 7.7 በካናዳ ሥራ የማግኘት ፈተናዎች

**መመሪያ:** በካናዳ አዲስ መጪ የሆኑ ሰዎች ሥራ ለማግኘት የሚገጥማቸውን ፈተና ያንብቡ። በቀጣዩ ገጽ ደግሞ የአዲስ መጪዎቹን ሁኔታዎች ያንብቡ። በሳጥኖች ውስጥ ፊደሎቹን በመጻፍ፣ ፈተናዎቹን ከየአንዳንዶቹ አዲስ መጪዎች ሁኔታ ጋር ያዛምዱ። እያንዳንዱ ሁኔታ ከአንድ በላይ ትክክለኛ መልስ አለው።





**ሀ)** በእንግሊዘኛ እንዲሁም በፈረንሳይኛ ዝቅተኛ የቋንቋ ክህሎት





**ለ)** በካናዳ ምንም ዓይነት የሥራ ልምድ አለመኖር




**ሐ)** በካናዳ ላለው የሥራ ቦታ ባህል እንግዳ መሆን




**መ)** ከካናዳ ውጪ ያለ የሥራ ልምድ እውቅና የሚሰጠው አለመሆኑ




**ሠ)** ሥራ ሊያስገኝ የሚችል ብዙ ግንኙነት ካናዳ ውስጥ አለመኖር



**ረ)** ከካናዳ ውጪ የተገኙ የትምህርት ማስረጃዎች በካናዳ እውቅና የማያገኙ መሆናቸው


**ወደ ካናዳ አዲስ መጪ የሆኑ ሰዎች ሥራ በሚፈልጉበት ጊዜ ሊገጥማቸው ይችላል የሚሏቸው ሌሎች ፈተናዎች ምንድን ናቸው?**

ምዕራፍ 7 - ሥራ





ለ, ሐ, ሠ


1. እንግሊዘኛ እንዲሁም ፈረንሳይኛ መናገር የሚችሉ እንዲሁም የትምህርት ደረጃቸው በካናዳ ተቀባይነት ያገኘ አዲስ መጪዎች፤ በተማሩበት ሙያ ግን ምንም ሠርተው የማያውቁ።




2. ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ነገር ግን በካናዳ እውቅና ያልተሰጠላቸው አዲስ መጪዎች። በተማሩበት ሙያ ግን ከካናዳ ውጪ ሠርተው የሚያውቁ። በካናዳ ያንን ሥራ ለመሥራት የሚሰጣቸውን ፈተና ማለፍ አለባቸው። ከሥራው ጋር የተገናኙ ሙያዊ ቃላትን በእንግሊዘኛም ሆነ በፈረንሳይኛ አያውቁም።




3. ማንበብም ሆነ መጻፍ የማይችሉ አዲስ መጪዎች። የሚሠሩት ሥራ በእጅ የሚሠራ ነው። ብዙ ዓመት የሥራ ልመድ ያላቸው እና ካናዳ ከመግባታቸው በፊት የራሳቸው የንግድ ሥራ የነበራቸው።




4. የተወሰነ ፈረንሳይኛ ማውራት የሚችሉ ነገር ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያላጠናቀቁ አዲስ መጪዎች። በአገራቸው ለበርካታ ዓመታት የሠሩ። አብዛኛውን የሚያገኙት ሥራ በሚያውቋቸው ሰዎች በኩል ያገኟቸው ናቸው።


**ቀድሞ በሚኖሩበት አካባቢ እንደነበርዎ ዓይነት ሥራ ማግኘት ከባድ እንዲሁም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በጎ መንፈስ እና ዝግጅ አእምሮ ይኑርዎ።**



መልሶች፡ 1 (ለ፣ ሐ፣ ሠ)፣ 2 (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ)፣ 3 (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ)፣ 4 (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ)

# 7.8 በካናዳ ሥራ እንዴት ይፈለጋል?


**መመሪያ:** በካናዳ ሥራ እንዴት መፈለግ እንደሚቻል ያንብቡ። እርስዎ በካናዳ ሥራ ለመፈለግ ያቀዱት መንገድ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያስቀምጡ።



☐ **1.** በቀጥታ በድረ ገጽ ላይ፣ በቀጣሪዎች ድረገጾች እና በማኅበራዊ ሚድያ በኩል




☐ **2.** ከጓደኛ፣ ዘመድ፣ የአካባቢ ማኅበረሰብ ወይም ከለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር



☐ **3.** በመንግስት ወደሚደጎም ድርጅት በማቅናት



☐ **4.** ቀጣሪዎችን በአካል በማግኘት/በመተዋወቅ



☐ **5.** በሥራ አውደርዕዮች ላይ መታደም

የሥራ መፈለጊያ ድረገጾች መካከል ተከታዮቹ ይገኛሉ፤ www.jobbank.gc.ca/home እና www.workopolis.com




በካናዳ ሥራ ለማግኘት የተለያዩ መንገዶች አሉ። ምንም እንኳን ብዙ የሥራ እድሎች በቀጥታ በድረገጽ ላይ ቢገለጹም፣ አንዳንዶቹ ለሕዝብ ይፋ የሚደረጉ አይደሉም።



# 7.9 በካናዳ የሥራ መስክ ለመጀመር ያሉዎት አማራጮች


***መመሪያ:*** በካናዳ የሥራ መስክ ለመጀመር ያሉዎትን አማራጮች ያንብቡ። እርስዎ ሊሠሩ ያቀዱት አማራጭ የሚገኝበት ሳጥን ላይ የ “ ✓ ” ምልክት ያስቀምጡ።



☐ 1. ***የመረጃ ምዘና/ግምገማ***
በኖሩበት ሀገር የነበርዎን ልምድ እና ትምህርት በካናዳ እውቅና እንዲያገኝ ማመልከቻ ማስገባት።



☐ 2. ***የመለማመድ ሥራ***
በካናዳ በተገኘው ሥራ ውስጥ በመሳተፍ ገቢ እንዲሁም የካናዳ ልምድ ማግኘት፣ እንዲሁም በአንድ በተወሰነ ሥራ ፈቃድ እስኪያገኙ ድረስ ባለው ጊዜ ቋንቋውን መለማመድ።



☐ 3. ***መሸጋገሪያ ፕሮግራም***
በሚሠሩበት የሥራ ዘርፍ የካናዳ ልምድ ለማግኘት የሚያግዝ ሥልጠና፣ እንግሊዘኛ ወይም ፈረንሳይኛ ቋንቋ መማር ወይም የሥራ ቦታውን ባህል ለመረዳት የሚያግዝ።

☐ 4. ***ኢንተርንሺፕ***
በሥራ መስክዎ ለአጭር ጊዜ እንደጀመሩ የሚሠሩበት ሲሆን፣ በጣም ውስን የሆነ የካናዳ ልምድ የሚገኝበት ነው። ለዚህ አንዱ ምሳሌ የፌዴራል የአዲስ መጪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ነው። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፤




5. **የካናዳ ትምህርት**
በሚፈልጉት ሥራ መስክ ለመሥራት ብቁ ሆኖ ለመገኘት በካናዳ ተቋማት ገብቶ መማር።



6. **በጎ ፈቃደኝነት**
ከተለያዩ ሰዎች እና አካላት ጋር አዳዲስ ግንኙነቶችን እየፈጠሩ ጊዜያዊ፣ ክፍያ የማይደረግበት የካናዳ የሥራ ልምድ ማግኘት። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፤



7. **የምክክር ፕሮግራም**
በሚፈልጉት የሥራ መስክ ካለ አማካሪ ጋር መገናኘት። ይህ አማካሪ በሥራ መስኩ የተለያዩ ትውውቆች እና ግንኙነቶችን እንዲፈጥሩ ጠቃሚ ምክሮችን ይሰጥዎታል።




8. **የራስዎን አዲስ የንግድ ሥራ መጀመር**
በካናዳ የራስዎን የንግድ ሥራ በማሳደግ ወይም የራስዎ ቀጣሪ በመሆን ሥራዎን መጀመር። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፤



## 7.10 የመረጃዎች ግምገማ/ምዘና ጥቅሞች

የመረጃዎች ምዘና የቀደሞ ልምድዎን በካናዳ ካለው የሥራ ቅጥር ደረጃ ጋር የሚያነጻጽር ሂደት ነው። በሌላ ሀገር የነበርዎትን ክህሎት፣ እውቀት፣ የሥራ ልምድ እና ትምህርት መመዘኛ መንገድ ነው።





ይህ ምዘና በካናዳ ያሉ ቀጣሪዎች ብቃትዎን ለመረዳት ያስችላቸዋል። የመረጃ ምዘና ኤጀንሲዎች የትምህርት ማስረጃዎችዎን በነጻ ሊገመግሙልዎት ይችላሉ። ይህን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ፣




በሥራ ልምድ ወረቀትዎ ላይ የግምገማ ውጤቱን ማካተት ጠቃሚ ነው።



የውጪ ሀገር መረጃዎችዎን ለማስገምገም የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ሊረዱ የሚችሉ ፕሮግራሞች አሉ። ለበለጠ መረጃ ይህንን ያንብቡ፣

የመረጃ ምዘናን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘትም ይህንን ያንብቡ፤



**እንደየ ክልሉ ወይም ግዛቱ፣ ተመሳሳይ ሥራ የተለያየ ሥም ሊኖረው እና የሚጠይቀውም መስፈርት የተለያየ ሊሆን ይችላል። የሥራ ዝርዝሩን በጥንቃቄ በማንበብ ያሉበት ደረጃ የሥራውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን ያረጋግጡ።**





# 7.11 የሥራ ማመልከቻ እና የቅጥር ሂደት

**መመሪያ:** ለሥራ ማመልከቻ እና ቅጥር ያለውን ሂደት ይመልከቱ። እነዚህ ሂደቶች እንደ ሥራው ዓይነት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

**1** ሥራ መፈለግ




**2** የሥራ ልምድ እና ብቃት ዝርዝር ያዘጋጁ (የሥራ ልምድ ወይም ሲቪ)




**3** እርስዎ ለሥራው አስፈላጊ እና የተሻለ ሰው የመሆንዎን ምክንያት ያካተተ ደብዳቤ ይጻፉ (የሽፋን ገጽ ደብዳቤ)




**4** ሰነዶችዎን ይላኩ። እያዳንዱን ሥራና የሥራ ልምድ ከማመልከቻ ደብዳቤ ጋር ያያይዙ።




**5** ለቃለመጠይቅ መጠራትዎን የሚወስነው ቀጣሪዎ ነው።




**6** በሥራ ቃለመጠይቅ ላይ እርስዎ ለሥራው ትክክለኛው ሰው መሆንዎን ያረጋግጡ።



**7** ብዙ ሰዎች ለቃለመጠይቅ ከመጠራታቸው በፊት ለበርካታ ሥራዎች ማመልከቻ ያስገባሉ። መሞከርዎን ይቀጥሉ!






**8** ከተወሰነ ጊዜ እና ከብዙ ሙከራ በኋላ የሥራ እድል ያገኛሉ። እንኳን ደስ አልዎት!






በሥራ ዝርዝሩ ውስጥ ቋንቋን በተመለከተ ያለውን መስፈርት ይመልከቱ። ፈረንሳይኛ በይበልጥ በኲቤክ ግዛት የሚፈለግ ሲሆን ብዙ ሥራዎች እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲናገሩ ይጠይቃሉ። ሁለቱንም ቋንቋዎች፣ እንግሊዘኛ እና ፈረንሳይኛን ማወቅ በብዙ የሥራ ዘርፎች ሥራ ለማግኘት ጠቃሚ ነው።




# 7.12 በካናዳ የሥራ ባህል


መመሪያ: በካናዳ ስላለው የሥራ ባህልን በተመለከተ ያንብቡ። ከኖሩበት አካባቢ የተለየ ሆኖ ያገኙት የሥራ ባህል ወይም ልማድ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ያድርጉ።




☐ **1.** የሙሉ ቀን ሥራ ብዙውን ጊዜ በቀን 8 ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ አርብ፣ በሳምንት 40 ሰዓት ነው።




☐ **2.** የትርፍ ሰዓት ሥራ ብዙ ጊዜ ቢበዛ በሳምንት ከ16 እስከ 24 ሰዓት ነው።



☐ **3.** አንዳንድ ሥራዎች ፈረቃ ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ላይ መሥራትን የሚጠይቁ ናቸው።ይህ ማለት የሥራ ቦታዎች ከ8 ሰዓት በላይ ወይም በቀን 24 ሰዓት በሥራ ላይ ናቸው ማለት ነው። በመደበኛ አሠራር ሦስት ፈረቃዎች አሉ፤ የቀን፣ የምሽት እና የሌሊት።



☐ **4.** ትንሽ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ለልጆች መንከባከቢያ ወይም ከትምህርት ቤት በኋላ ላሉ መቆያዎች ማቀድ ያስፈልጓቸዋል። በካናዳ ልጆች ያለ አዋቂ ሰው ክትትል ለብቻቸው እንዲሆኑ አይደረግም። የልጆች እንክብካቤን በሚመለከት ያሉ አማራጮችን በምዕራፍ 6 ተግባር 6.7 ላይ ይመልከቱ።



☐ **5.** በካናዳ ሴቶች ወንድ ሠራተኞችን በማስተባበር ማሠራታቸው የተለመደ ነው።


**እያንዳንዱ የሥራ ቦታ የራሱ የሆነ የሥራ ባህል እና የሥራ መስፈርት አለው። ባገኙት ሥራ ለመቆየት እና የሥራ ልምድን ለማሳደግ፣ ከአዲስ የሥራ ቦታ ባህል ጋር መላመድ እና በሥራ ቦታ የሚጠበቅብዎትን ማሟላት ተገቢ ነው።**



# 7.13 የእርስዎ ደመወዝ



1. በካናዳ ቀጣሪዎች ቢያንስ መሠረታዊውን የደመወዝ እርከን እንዲከፍሉ በሕግ ይጠየቃሉ። የዝቅተኛ ደመወዝ ገደብ እንደ ክልሉና ግዛቱ የተለያየ ነው። በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ የተለያዩ ሥራዎች ያለውን የዝቅተኛውን ደመወዝ ገደብ እና የደመወዝ ደረጃን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት እዚህ ያንብቡ፤




2. በካናዳ ለመሥራት የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SIN/NAS) ያስፈልግዎታል። የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን የሚያቀርቡት በሕጋዊ መንገድ ሲጠየቁ ብቻ ነው።



3. በመደበኛ አሠራር ደመወዝዎን በጥሬ ገንዘብ አይቀበሉም፤ ነገር ግን በቀጥታ በባንክ ሂሳብ መለያ (ይዘዋወራል/ገቢ ይደረጋል) ወይም በቼክ ይሰጥዎታል።



4. ለእያንዳንዱ የክፍያ ጊዜ የክፍያ መግለጫ ይደርስዎታል። የሚያገኙት የተጣራ ገቢ ከጠቅላላ ደመወዝዎ የሚያንስ ነው። እንደ የገቢ ግብር፣ ጡረታ እንዲሁም የሥራ እና የጤና መድኅን ክፍያ ተቀናሾች ከዋናው ደመወዝዎ የሚቀነሱ ይሆናሉ።



5. በካናዳ ሁሉም ሠራተኞች ከደመውዛቸው የጡረታ ክፍያ ይከፍላሉ። ይህም የካናዳ የጡረታ እቅድ ይባላል። ከ65 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እና በካናዳ ለተወሰነ ጊዜ የኖሩ ሰዎች መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ከመንግስት ያገኛሉ፣ ይህም በእድሜ የገፉ ሰዎች ዋስትና ይባላል።




6. በየዓመቱ በኤፕሪል 30 ከሥራ ቦታዎ የገቢ እና የወጪ መግለጫ (T4) በመጠቀም የራስዎን የገቢ ግብር የማስገባት ኃላፊነት አለብዎት።



**‹ምስጢራዊ› ሥራ ገንዘብ የሚያገኙበት ይፋ ያልሆነ ነገር ግን ግብር የማይከፍሉበት ሥራ ነው። እንዲህ ያለው ሥራ ሕገወጥ ነው። ለቀጣሪውም ሆነ ለተቀጣሪ ከባድ ቅጣት ሊያስከትል ይችላል።**



# ምዕራፍ 8
# ገንዘብ አያያዝ



# ምዕራፍ 8

# ገንዘብ አያያዝ



## 8.1 ገንዘብ በካናዳ

የካናዳ ብሔራዊ የመገበያያ ምንዛሬ የካናዳ ዶላር (CAD) ነው። በዶላር ውስጥ 100 ሳንቲሞቹ (¢) አሉ። የካናዳ ባንክ ሁለት ዓይነት ምንዛሬዎችን ይሰጣል፤







1. የታተሙ ገንዘቦች፣ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ነገር ግን በዋጋቸው መሠረት የተለያየ ቀለም አላቸው::

2. የተለያየ ቅርጽ፣ መጠን እና ቀለም ያላቸው ሳንቲሞች ናቸው:: ከጀርባቸው የካናዳ ዓርማ አለባቸው።



በካናዳ የመኖሪያ ወጪ እንደ ክልሉና ግዛቱ ይለያያል። በትልልቅ ከተማዎች እና ከከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች መካከልም ለኑሮ የሚያስፈልገው ወጪ ይለያያል። ከዚህም በተጨማሪ እንደየሚኖሩበት መንደርም ይለያያል።



በቋሚ መኖሪያ ቤት መኖር ሲጀምሩ፣ በየወሩ ለመሠረታዊ እና አስፈላጊ ወጪዎች ክፍያ መፈጸም ይኖርብዎታል።


**ገንዘብን መመደብ ወይም በጀት መያዝ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለዎ ለማወቅ ይረዳል። በመንግስት የሚደጎሙ ድርጅቶች ወይም ሊጋሾችዎ በየወሩ ገንዘብ እንዴት መመደብ እና ያንንም እንዴት መከተል እንደሚችሉ እንዲያውቁ ሊረድዎ ይችላሉ።**

# 8.2 በካናዳ መሠረታዊ የኑሮ ወጪዎች ምንድን ናቸው?


**መመሪያ:** በካናዳ መሠረታዊ የሆኑ ለመኖር የሚያስፈልግዎ ወጪዎችን ይመልከቱ። አዲስ የሆነብዎ ወጪ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ " ✓ " ምልክት ያድርጉ።




☐ 1. **ቤት**
ይህ ከፍተኛ የወር ወጪዎ ነው። ይህም በዋናነት የቤት ኪራይ ሲሆን፣ የኢንሹራንስ እና የእድሳት ወጪዎችን ሊጨምር ይችላል።



☐ 2. **የቤት ውስጥ መገልገያዎች**
በካናዳ አብዛኞቹ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ፣ የማሞቂያ እና የውሃ ወጪዎችን ያካትታል። ከእነዚህ ወጪዎች የተወሰኑት በቤት ኪራይ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ። በክረምት ወቅት ደግሞ የኤሌክትሪክ እና የማሞቂያ ክፍያዎች ከፍ ሊሉ ይችላሉ።



☐ 3. **ምግብ**
ይህም ከወጪዎ ከፍተኛ ድረሻ የሚይዝ ሲሆን ራስዎን እና ቤተሰብዎን ለመቀለብ የሚያወጡት ወጪ ነው።



☐ 4. **መጓጓዣ**
በአካባቢዎ ለመንቀሳቀስ የሕዝብ መጓጓዣን ጨምሮ ለመጠቀም የሚያወጡት ወጪ ነው።




☐ 5. **ግንኙነት**
ይህ የተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም የመስመር ስልክን፣ ቴሌቭዥን፣ የበይነመረብ ተደራሽነትን የሚያካትት ሲሆን፣ እነዚህም በየወሩ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ናቸው።



6. **የሕጻናት እንክብካቤ**
*ሥራ የሚሠሩ ወይም ትምህርት የሚማሩ ወላጆች ልጆቻቸውን ለሚጠብቁ እና እንክብካቤ ለሚያቀርቡላቸው ክፍያ መፈጸም ይኖርባቸዋል።*



7. **ሌሎች ወጪዎች**
*እነዚህ የአልባሳት፣ የንፅህና ቁሳቁሶች፣ የትምህርት መማሪያ ቁሳቁሶችን እና ሌሎች አስፈላጊ እቃዎችን የሚያካትቱ ናቸው።*




8. **የኢሚግሬሽን ብድር**
*ይህ የካናዳ መንግስት በእርስዎ ስም ለጉዞዎ የከፈለው የገንዘብ መጠን ነው።*

*የራስዎን ወጪዎች ይህንን በማንበብ ማስላት ይችላሉ፤*

**በካናዳ የመጀመሪያ ዓመት ቆይታዎ በኋላ፣ ብድርዎን በየወሩ መክፈል የመጀመር ኃላፊነት አለብዎት። በጠቅላላ ለመንግስት የሚከፍሉት እና ያለብዎትን የብድር መጠን እንዲሁም በየወሩ መክፈል የሚጠበቅብዎትን የሚገልጽ ጽሁፋዊ መግለጫ ይቀበላሉ። ለበለጠ መረጃ በምዕራፍ 2 ተግባር 2.4ን ተመልከቱ።**



# 8.3 የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ




የሚቀበሉት የገንዘብ ድጋፍ መጠን በብዙ ምክንያቶች ላይ መሠረት ያደረገ ነው፣ ይህም የቤተሰብ መጠን፣ የቤተሰብ አባላት እድሜ፣ የሚኖሩበት ቦታ እና የቤተሰብዎን መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚያጠቃልል ነው።

**መመሪያ:** የሚገኙት የገንዘብ ድጋፍ እንዲሸፍኑት የሚረዳዎን መሠረታዊ ወጪዎች ይመልከቱ። ከፍተኛ ወጪ ለሆነው የ “ $$$$ ” ምልክት ያድርጉ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ወጪ ላይ ደግሞ የ “ $$$ ” ምልክት ያድርጉ፣ በሁለተና ደረጃ ዝቅተኛ ለሆነ ወጪ የ “ $$ ” ምልክት ያድርጉ እንዲሁም በጣም ዝቅተኛ ወጪ ለሆነው የ “ $ ” ምልክት ያድርጉ።





**1.** የመገናኛ አገልግሎት



**2.** ምግብ




**3.** የቤት እና የቁሳቁስ



**4.** መጓጓዣ/ ትራንስፖርት



**እንዳሉበት ሁኔታ ተጨማሪ ክፍያ ሊያገኙ ይችላሉ። እነዚህም አዲስ የተወለደ ሕጻን ልጅ ያለበት ቤተሰብ፣ እድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች፣ የተለየ አመጋገብ የሚያስፈልጋቸው ሲኖሩ ወይም የመኖሪያ ቤት ክፍያ ድጋፍን ያካትታል። ከእነዚህ ተጨማሪ ክፍያዎች ውስጥ ሊያገኙት የሚገባ ካለ፣ በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ሊጋሾችዎን ይጠይቁ።**




መልሶች: 1 ($)፤ 2 ($$$)፤ 3 ($$$$)፤ 4 ($$)

## 8.4 ገንዘብ እንዴት መቆጠብ ይችላሉ?

***መመሪያ:*** በካናዳ ገንዘብ ለመቆጠብ የሚያስችልዎትን ጠቃሚ ነጥቦች ያንብቡ። እርስዎም ይጠቅመኛል ብለው የሚያስቡት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✓ ” ምልክት ያድርጉ።




☐ **1.** መኖሪያ ቤት ወይም አፓርትመንት ከሌላ ሰው ጋር በመጋራት የቤት ኪራይ በጋራ መክፈል።




☐ **2.** ምግብ ከማዘዝ እና ሬስቶራንቶች ገብቶ ከመመገብ ይልቅ፣ ለምግብ የሚሆነውን በመግዛት ቤት ውስጥ ምግብ ማብሰል ይችላሉ።



☐ **3.** ቅናሽ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን መግዛት እና እነዚያ ምርቶች የሚገኙባቸው መሸጫዎች መሄድ፣ ለማነጻጸርም የተለያዩ መደብሮችን በራሪ ወረቀቶች መመልከት።



☐ **4.** ተንቀሳቃሽ ስልክ እንዲሁም የመስመር ስልክ ከመያዝ ይልቅ፣ የመገናኛ ወጪዎን ለመቀነስ አንዱን ብቻ መምረጥ ይቻላል። የረጅም ርቀት የስልክ ጥሪዎች በጣም ውድ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም ዓለማቀፍ የስልክ ጥሪ ከማድረግዎ አስቀድመው የክፍያውን መጠን በጥንቃቄ መመልከት አለብዎት። በተጨማሪም በቅናሽ ወጪ የረጅም ርቀት ጥሪዎችን ለማድረግ በይነ መረብ መጠቀም ወይም የመደወያ ካርዶችን መግዛት ይችላሉ።



☐ **5.** መኪና ከመግዛት ይልቅ የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ።




☐ **6.** በቤተመጻሕፍት እንዲሁም የሕዝብ መሰብሰቢያ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን ነጻ የበይነ መረብ አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ።



☐ **7.** ለተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ለቴሌቭዥን፣ ለበይነመረብ፣ ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ ወይም ለመኪና ስምምነት ወይም የክፍያ እቅድ ከመምረጥዎ አስቀድሞ ደንብ እና ሁኔታዎን በንጽጽር ይመልከቱ። ቅናሾች ያሉ ከሆነ ይፈልጉ።



☐ **8.** ሁሉም አገልግሎቶች የተጠቃለሉበት የቤት ኪራይ ክፍያ ያለው ቤት መፈለግ ይችላሉ። ይህ ቋሚ ወጪ በመሆኑ ገንዘብዎን ለመመደብ ያግዝዎታል። ካልሆነ እንደ ግል አጠቃቀምዎ ወጪዎም የተለያየ ይሆናል።




☐ **9.** ቅናሽ ዋጋ ያለው የልጆች እንክብካቤ መኖሩን ለጋሾችዎን ወይም በመንግስት የሚደጎም ድርጅቶችን መጠየቅ አልያም ከሌሎች ወላጆች ጋር ኃላፊነትን መጋራት ይችላሉ።

# 8.5 ከገንዘብ ድጋፍ ጋር በተገናኘ የሚጠበቁ ነገሮች



የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ መጠን ውስን ነው። መሠረታዊ ፍላጎቶችዎን ብቻ ሊሸፍኑ የሚችሉ ናቸው። በሚቀበሉት ገንዘብ ተጨባጭ እና ሊደርጓቸው የሚችሏቸውን ነገሮችን ማስቀመጥ በካናዳ የተረጋጋ ሕይወት ለመምራት ያግዝዎታል።

**መመሪያ:** ሁኔታዎቹን ይመልከቱ። በእያንዳንዱ ሁኔታ እና ለሁኔታው ተጨባጭ እንዲሆኑ በሚጠበቁ መካከል ያዛምዱ።




**1.** ከመንግስት እና/ወይም ከለጋሾችዎ የገንዘብ ድጋፍ እየተቀበሉ ነው።




**2.** ቤትዎ እና ሊሄዱበት የሚፈልጉት ቦታ ይራራቃሉ።



**3.** ለብቻዎ ይኖራሉ፣ ልጆች የለዎትም እንዲሁም የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ ነው የሚያገኙት።



**4.** በሌላ ሀገር ያሉ ቤተሰብዎችዎን ማናገር ይፈልጋሉ።




**ሀ)** ከሌላ ሰው ጋር ቤት በመጋራት የቤት ኪራይ ተካፍለው ይከፍላሉ።



**ለ)** በበይነመረብ አልያም የስልክ ጥሪ ካርዶችን በመግዛት ከቤተሰብዎ ጋር ይገናኛሉ።




**ሐ)** የሕዝብ ትራንስፖርት ጉዞ ለማድረግ ዝቅተኛ ዋጋ ያለው አማራጭ ነው። ወርሃዊ የይለፍ ትኬት በመግዛት ገንዘብ መቆጠብ ይችላሉ።




**መ)** ምን አልባት ወደ ሀገር ቤት ሊልኩ የሚችሉት በቂ ገንዘብ ላይኖርዎ ይችላል።

መልሶች፡ 1 (መ)፤ 2 (ሐ)፤ 3 (ለ)፤ 4 (ሀ)



5.

ከካናዳ ውጪ መጓዝ ይፈልጋሉ።



ሠ) ከወሩ መጨረሻ በፊት ያለዎትን ገንዘብ በሙሉ ተጠቅመው ከጨረሱ፣ ተጨማሪ አይሰጥዎትም። ወጪዎን እንዴት መቆጣጠር ይችላሉ የሚለውን በሚመለከት ከመንግስት የሚደጎሙ ድርጅቶች ወይም ሊጋሾችዎ ጋር ይነጋገሩ።



6.

ወጪዎ በየወር ከሚቀበሉት ገቢ ይበልጣል።




ረ) ጉዞ ማድረግ ውድ ነው፣ የሚቀበሉት የገንዘብ ድጋፍ መጠንም ይህን ለመክፈል በቂ አይደለም። ቀድመው ማቀድ እና መቆጠብ አለብዎት።



7.

የረጅም ጊዜ ግብዎ ድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትዎን መጨረስ፣ ቤት ወይም መኪና መግዛት ነው።



ሰ) አብዛኛው የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ የቤት ኪራይ ለመክፈል የሚውል ነው። ቤተሰቦች ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞች ሊያስፈልጋቸው ይችላል።



8.

በማኅበረሰብዎ ውስጥ መኖሪያ ቤት በጣም ውድ ነው።



ሸ) ገንዘብ መቆጠብ እና/ወይም መበደር ሊኖርብዎ ይችላል። ለእነዚህ ወጪዎች ክፍያ ለመፈጸም በየወሩ የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ብቻውን በቂ አይሆንም።

መልሶች፡ 5 (ረ)፤ 6 (ሠ)፤ 7 (ሸ)፤ 8 (ሰ)

# 8.6 ግብይት በካናዳ

ግብይት ለማካሄድ የትኛው ቦታ ነው ጥሩ የሚለውን ለመለየት ጊዜ ሊወስድ ይችላል።



***መመሪያ:*** በካናዳ ግብይት ሊፈጽሙ የሚችሉባቸውን የተለያዩ ቦታዎችን ይመልከቱ። በእያንዳንዱ ቦታ እና በቦታዎቹ ሊገዙ በሚችሏቸው ምርቶች መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**ሱፐርማርኬት (ትልቅ ዘመናዊ ገበያዎች)**

**1.**




**ሀ)** ልብስ፣ ጫማ፣ የቤት ውስጥ መገልገያ፣ ቁሳቁሶች እንዲሁም በጠቅላላ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የሚገኙበት ትልቅ መደብር ነው።



**የመድኃኒት መደብሮች**

**2.**



**ለ)** እነዚህ በጣም የተለመዱ የምግብ መሸጫዎች ናቸው። ብዙዎቹም የጽዳት እቃዎች፣ የውበት መጠበቂያ፣ መጽሔቶች እና የተለመዱ የሐኪም ትዕዛዝ የማይጠይቁ መድኃኒቶች ይሸጥባቸዋል።



**በተለያዩ ክፍሎች የተደራጁ ግዙፍ መደብሮች**

**3.**



**ሐ)** እነዚህ ቤት ለማደስ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች የሚሸጥባቸው፣ አንዳንዴም የቤት ዕቃ የሚሸጥባቸው ናቸው።




**የቤት ጥገና/ማሻሻያ ቁሳቁስ መሸጫ መደብሮች**

**4.**



**መ)** እነዚህ በአብዛኛው የመድኃኒት ቤት የያዙ መደብሮች ሲሆኑ፣ በሐኪም ትዕዛዝ የተፈቀዱ መድኃኒቶች የሚሸጥባቸው ናቸው። ብዙዎችም ያለ ሐኪም ትዕዛዝ መሸጥ የሚችሉ መድኃኒቶችን፣ የልጆች ዳይፐር፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ የውበት መጠበቂያዎች፣ መጽሔቶች እንዲሁም ምግብ ነክ ነገሮች ይገኙባቸዋል።


መልሶች፡ 1 (ለ)፣ 2 (መ)፣ 3 (ሀ)፣ 4 (ሐ)

5. 

ያገለገሉ እቃዎች መሸጫዎች



ሠ) እነዚህ መደብሮች ከተለያየ ሀገር እና ባህል በተውጣጡ፣ ከሀገራቸው ወደ ካናዳ ምርቶችን በሚያስገቡ ሰዎች ባለቤትነት የተያዙ ናቸው። በእነዚህ መደብሮች የመጡበትን ሀገር ምግብ ሊያገኙ ይችላሉ።

6. 


የባህል ምግብ መሸጫዎች



ረ) በይነ መረብን በመጠቀም የሚደረግ ግዢ ነው። ሻጮች ከእነዚህ መገበያያዎች በተጨማሪ ግለሰቦች በግላቸው የተገለገሉበት እቃዎችንም ይሸጣሉ። በካናዳ ላሉ ሰዎች የድረገጽ ላይ ግብይት የተለመደ ነው።

7. 

የጋራዥ እቃዎች ሽያጭ



ሰ) እነዚህ መደበኛ ያልሆኑ፣ ከቤት ውጪ የሚደረጉ ግብይቶች ሲሆኑ፣ ሰዎች በቤታቸው ያገለገሉ እቃዎችን በቅናሽ ዋጋ የሚሸጡበት ነው። የሽያጩ ቀን እና ቦታን በተመለከተም ብዙ ጊዜ ማስታወቂያዎች በዚያው አካባቢ ይገለጻሉ።

8. 

የቀጥታ የድረገጽ ላይ ግብይቶች



ሸ) እነዚህ መደብሮች እንደ ልብስ እና ሌሎች የቤት ውስጥ ያገለገሉ እቃዎችን በቅናሽ ዋጋ የሚሸጡ ናቸው። በካናዳ ያገለገሉ እቃዎችን መግዛት የተለመደ ነው።


**በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ሊጋሾችዎ ምግብ የት መግዛት እንደሚችሉ ሊያሳይዎት አልያም ጥሩ ዋጋ ያለበትን በሚመለከት ሐሳብ ሊሰጡዎት ይችላሉ። የቅናሽ ዋጋ ገበያዎች የት እንደሚገኙ፣ የቅናሽ ኩፖኖችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ፣ የገበያ ዋጋዎችን እንዲያነጻጽሩ እና የግል ሽያጮችንም በሚመለከት ሊነግርዎት ይችላሉ።**




መልሶች፡ 5 (ሠ)፤ 6 (ረ)፤ 7 (ሰ)፤ 8 (ሸ)

# 8.7 ምን ያስፈልግዎታል እና ምን ይፈልጋሉ?

**መመሪያ:** እያንዳንዱን ዕቃ/ቁሳቁስ ይመልከቱ እና የሚያስፈልግዎትን እና የሚፈልጉትን ይለዩ። የሚያስፈልግዎ ያለበት ሳጥን ላይ የ "○" ምልክት ያስቀምጡ፣ የሚፈልጉት ያለበት ሳጥን ላይ ደግሞ የ "△" ምልክትን በሳጥኑ ውስጥ ያስቀምጡ።



☐ **1.** መኪና



☐ **2.** ጤናማ ምግብ



☐ **3.** ትልቅ ቤት




☐ **4.** ልብስ



☐ **5.** ዘመናዊ/ ስማርት/ ስልክ




☐ **6.** የንጽህና መጠበቂያ ምርቶች



☐ **7.** የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ክበብ አባልነት



☐ **8.** መኖሪያ ቦታ




☐ **9.** በሬስቶራንት መመገብ



☐ **10.** ዝነኛ/ውድ ሥም/ ያላቸው ጫማዎች



**የሚያስፈልግዎትን እና የሚፈልጉትን መለየት አስፈላጊ ነው። አንዳንድ የሚፈልጓቸው ነገሮች ውድ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ስለዚህም ለመግዛት መጠበቅ ይኖርብዎታል።**



# 8.8 ባንክ በካናዳ



ካናዳ ከደረሱ ከአጭር ጊዜ በኋላ በመንግስት የሚደገመው ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ በካናዳ ባንክ የሂሳብ ቁጥር ለመክፈት ማመልከቻ እንዲሞሉ ይረዱዎታል።

የባንክ የሂሳብ ቁጥር  መክፈት ተከታዮቹን ለማድረግ ይረዳዎታል፤



1. ዘመናዊ የባንክ ማሽኖችን ለመጠቀም



2. በቀጥታ የገንዘብ ዝውውር ገንዘብ ለመቀበል



3. በበይነመረብም ሆነ መደብሮች ውስጥ ግብይት ሲደርጉ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርድ ለመጠቀም



4. የቀጥታ መስመር የባንክ አሠራርን በመጠቀም ወርሃዊ ወጪዎችን ለመክፈል



5. ቼክ ለመጻፍ

የተለያዩ የባንክ ሂሳብ መለያ ዓይነቶች አሉ። ተከታዩቹ በጣም የተለመዱት ናቸው፤



1. **የቼክ መለያዎች**
   እነዚህ ወጪዎችን ለመክፈል ያገለግላሉ። የቤት ኪራይን ጨምሮ የተለያዩ ወርሃዊ ወጪዎችን ለመሸፈን ቼክ ማዘዝ ይችላሉ። ገንዘቡን ከመለያዎ የዴቢት ካርድ ማውጣት አልያም በቀጥታ ማስተላለፍም ይችላሉ።



2. **የቁጠባ መለያ**
   እነዚህ የወደፊት ወጪ እና ግብን ለማሳካት እንዲቻል ገንዘብ ለመቆጠብ የሚያገለግሉ ናቸው። በሚያስቀምጡት ገንዘብ መጠን መሠረት ባንኮችም ለዚህ ወለድ ሊከፍልዎት ይችላሉ።




**በቼክ ክፍያ ሲፈጽሙ፣ በቼክ መለያዎ ካለው ተቀማጭ ገንዘብ በላይ እንዳይሆን ይጠንቀቁ። ይህ ከሆነ በሕግ ተጠያቂ ያደርግዎታል። ያሉትን የተለያዩ የባንክ መለያ ዓይነቶች በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ፤**



## 8.9 የብድር/ክሬዲት ካርዶች

ብዙ በካናዳ የሚኖሩ ሰዎች ለበርካታ ግብይታቸው እነዚህን ካርዶች ይጠቀማሉ፣ ይህም በየእለቱ በመደብሮች ከሚያደርጉት ግብይት አንስቶ በበይነ መረብ የሚገዙትን ጭምር ነው።






1. ክሬዲት ካርድ ሲጠቀሙ ገንዘብ እየተበደሩ ነው ማለት ነው። ካርዱን የሰጥዎ ባንክ ወይም ኩባንያ የወሰዱት ገንዘብ ላይ ወለድ ጨምሮ ነው የሚቀበልዎት። ይህን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ።



2. ክሬዲት ካርዶችን በጥንቃቄ ይጠቀሙ። ክሬዲት ካርድ መጠቀም በቀላሉ እዳ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ማንኛውንም ነገር በብድር ከመግዛትዎ አስቀድሞ፣ በባንክ መለያ ቀሪ ሂሳብዎ በቂ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጡ አልያም ከመደበኛ ወጪዎ ውጪ ያሉ ወርሃዊ ክፍያዎችን በጊዜ መክፈል መቻልዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

**የብድር/ክሬዲት ካርድ ክፍያዎችዎን ሳይፈጽሙ ከቀሩ፣ ባንኩ ወይም ያበደርዎ ኩባንያ የቅጣት ክፍያ ይጥልብዎታል።**



## 8.10 የብድር ታሪክዎ



1. ብድር ሲጠቀሙ፣ የአካፋፈል ሁኔታዎ በብድር ታሪክዎ ላይ ሰፍሮ ይቀመጣል። ወደፊት በሌላ ጊዜ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ሲያመለክቱ፣ ባንኮች ውሳኔ የሚሰጥዎት ያንን ታሪክዎን ተመልክተው ነው። ጥሩ የብድር ታሪክ እንዲኖርዎ ክፍያዎን በሙሉ እና በየወሩም ጊዜውን ጠብቀው መፈጸም አለብዎት።



2. በየወሩ የቤት ኪራይ እና ወርሃዊ ክፍያዎችን በሰዓቱ መክፈል አለብዎ። ክፍያዎን ለመፈጸም ቢያረፍድ፣ በብድር ታሪክዎ ላይ የሚጻፍ ሲሆን እንዲወጡ/እንዲሰረዙ ሊደረግም ይችላል።

**በካናዳ ጥሩ የብድር ታሪክ እንዲኖርዎ የሚያስችልዎ የመጀመሪያው እድል፣ በየወሩ የኢሚግሬሽን ብድር ክፍያን መፈጸም ነው።**



# 8.11 ግብር በካናዳ

የካናዳ የገቢዎች ኤጀንሲ በካናዳ ዋናው እና የግብር ሕግ የማውጣት ኃላፊነት ያለበት አካል ነው። ግብር በፌዴራል፣ በግዛት እንዲሁም በከተማዎች አስተዳደር መንግስት ይሰበሰባል።

የካናዳ የገቢዎች ኤጀንሲን በተመለከተ እንዲሁም በድህረ ገፅ የቀጥታ መለያን ለመክፈት ይህንን ያንብቡ፤

***መመሪያ:*** በካናዳ ሰዎች የሚከፍሏቸውን የተለያዩ የግብር ዓይነቶችን ይመልከቱ። በእያንዳንዱ ግብር እና በተቀመጠው ማብራሪያ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.** **የእቃ እና የአገልግሎት (ወይም የሽያጭ) ግብር**




**2.** **የንብረት ግብር**




**3.** **የገቢ ግብር**




**ሀ)** ይህን የግብር ዓይነት የሚከፍሉት ቤት፣ አፓርታማ ወይም መሬት ካለዎት ነው። በኪራይ የሚኖሩ ከሆነ ይህን ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ያለበት የቤቱ ባለቤት ነው።




**ለ)** እነዚህ የግብር ዓይነቶች በመንግስት የሚወሰዱ ሲሆን ሠርተው ከሚያገኟቸው ገቢዎች ወይም ጥቅሞች ላይ ይቀነሳሉ። እነዚህም ብዙ ጊዜ ክፍያው ለእርስዎ ሳይደርስ ተቀናሽ ይደረጋሉ።



**ሐ)** አንድን እቃ ሲገዙ ወይም አገልግሎት ሲያገኙ ከሚከፍሉት ክፍያ በተጨማሪ የሚከፍሉት ገንዘብ ነው። በካናዳ መሠረታዊ በሆነው ምግብ ላይ ግብር አይጣልም። እንደ ሲጋራ እና አልኮል መጠጥ ያሉ ሸቀጦች ላይ ደግሞ ተጨማሪ ግብር ይጣላል።

መልሶች: 1 (ሐ)፤ 2 (ሀ)፤ 3 (ለ)

በካናዳ ሁሉም ሰው ግብር ይከፍላል። በካናዳ የተሰበሰበ ግብር ለተከታዮቹ አገልግሎት ይውላል፤








**1.** መሠረታዊ ትምህርት




**2.** የጤና እንክብካቤ



**3.** የመንገድ እና አውራጎዳና ጥገና





**4.** እንደ እሳት አደጋ እና ፖሊስ ያሉ የድንገተኛ አገልግሎቶች



**5.** የማኅበረሰብ አገልግሎት



**6.** የሕዝብ መናፈሻ





**7.** የሕዝብ ትራንስፖርት እና መኪና ማቆሚያ




**8.** በመንገድ፣ አውራ ጎዳና እና የእግረኛ መንገድ ላይ ያለን በረዶ ለማስወገድ

## 8.12 የገቢ ግብርን ማሳወቅ

ካናዳ ከገቡ እና የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SIN/NAS) ካገኙ በኋላ፣ የገቢ ግብር ሪፖርት ማስገባት አለብዎት። ይህም ማንኛውም ዓይነት የተቀበሉትን የገንዘብ ድጋፍ ያካትታል። ይህም የሚደረገው በየዓመቱ ከፌብሯሪ እስከ ኤፕሪል ባለው ጊዜ ነው። በካናዳ የኖሩት ከፊል የዓመቱን ክፍል ቢሆን እንኳ ወይም በዓመቱ ምንም ዓይነት ገቢ ያልነበርዎ ቢሆን፣ የግድ ሪፖርት ማስገባት አለብዎት። የኑሮ ወይም የትዳር አጋር ቢኖርዎ እንኳን፣ ሁለታችሁም በየዓመቱ በተናጠል ሪፖርት ማስገባት አለባችሁ።






ይህን ሪፖርት ማስገባት አለመቻል እንደ የሕጻናት የግብር ተጠቃሚነት ያሉ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ሊያሳጣ የሚችል ነው።

የገቢ ግብር ሪፖርት ማስገባትን በተመለከተ የበለጠ ለማወቅ በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን ይጠይቁ፣ እንዲሁም ይህንን ያንብቡ፤

## 8.13 ተጨማሪ የገንዘብ ጥቅሞች

ወዲያውኑ የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን (SIN/NAS) ካገኙ በኋላ የሚገባዎትን ጥቅም ለማግኘት ማመልከቻ ያስገቡ። የገቢ ግብር ሪፖርት በጊዜ ማስገባትዎ ማግኘት የሚገባዎትን ጥቅም እንዲያገኙ ይረዳዎታል።





የካናዳ የሕጻናት የግብር ተጠቃሚነትን ጨምሮ የእቃ እና የአገልግሎት ግብር ተመላሽ እንዲሁም ሌሎች በየክልሉና በየግዛቱ ያሉ የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በመንግሥት የሚደጎም ድርጅትን ወይም ለጋሾችዎን ሊያገኙ የሚችሏቸውን ጥቅሞች በሚመለከት ይጠይቋቸው።



በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ለጋሾችዎ አስፈላጊውን ቅጾች እንዲሞሉ እና ተፈላጊ ሰነዶችን እንዲያያይዙ ሊረዱዎት ይችላሉ።

ለእርስዎ የቀረቡ ጥቅሞችን በሚመለከት የበለጠ ለማወቅ ይህንን ያንብቡ፤

# ምዕራፍ 9
# መጓጓዣ/ትራንስፖርት




# ምዕራፍ 9

# መጓጓዣ/ትራንስፖርት


## 9.1 መጓጓዣ/ትራንስፖርት በካናዳ

ካናዳ ብዙ ክልሎች ያሏት እና ሰፊ መልክዓ ምድር ያላት ትልቅ ሀገር ናት። ሰዎች በክልሎች መካከል እንዲሁም በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ በተለያየ መንገድ ይንቀሳቀሳሉ። በካናዳ ውስጥ ከቦታ ቦታ ጉዞ ለማድረግ የተለያዩ አማራጮች አሉ።





**መመሪያ፡** በካናዳ ያሉ መጓጓዣ/ትራንስፖርት ዓይነቶችን ያንብቡ። አዲስ የሆኑብዎት ካሉ በሳጥኑ ውስጥ የ “✓” ምልክት ያድርጉ።



☐ 1. **የሕዝብ ትራንስፖርት**

በካናዳ በሚገኙ በሁሉም ትልቅ እና መካከለኛ ከተማዎች ሰዎች  እነዚህን የትራንስፖርት አገልግሎቶች ይጠቀማሉ። በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ በፍጥነት ለመንቀሳቀስ አማራጮች ናቸው። አውቶቢስ፣ ከወለል በታች ያሉ ባቡሮች፣ ቀላል ባቡር እና መኪናዎች ለዚህ ምሳሌ ናቸው። እንደሚኖሩበት ቦታ ግን ሊለያይ ይችላል።



☐ 2. **ብስክሌት**

ይህ በከተማዎች አካባቢ ለመንቀሳቀስ ጤናማ እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ነው። በብዙ መንገዶች ላይ ብስክሌት ማሽከርከር የተፈቀደ ሲሆን፣ የራሱ የሆነ የተወሰነ የተሰጠው የመንገድ ላይ መስመርም አለ። የራስ መከላከያ ወይም ሄልሜት ማድረግ በጣም ይበረታታል።





☐ 3. **ታክሲ**

ሁሉም ትልቅ እና መካከለኛ ከተማዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ የታክሲ ኩባንያዎች አሏቸው። አሽከርካሪዎችም በከተማው እውቅና ያገኙበት ይፋዊ መታወቂያ አላቸው። ውድ ሲሆኑ፣ የጉዞዎን ክፍያ የሚፈጽሙት በኪሎሜትር ተሰልቶ ነው። ይህን የሚያሰሉ አውቶማቲክ ሜትር መለኪያ አሏቸው። የክፍያው መጠን የተመደበ ሲሆን መደራደርም ሆነ መከራከር አይቻልም።



☐ 4. **የጉዞ መጋሪያ መተግበሪያዎች**

ይህ ቴክኖሎጂ ተሳፋሪ እና አሽከርካሪዎች በሞባይል መተግበሪያ የሚገናኙበት ነው። ክፍያው በተወሰነ መጠን ከታክሲ ይቀንሳል፣ ነገር ግን እነዚህ አገልግሎቶች በመንግስት ስር አይደሉም። ይህን አገልግሎት ሲጠቀሙ ተጨማሪ ጥንቃቄዎችን ያድርጉ።




**5. ሞተር-ሳይክል**

እነዚህ የሚጠቀሙት የነዳጅ መጠን በጣም አነስተኛ ነው። ሆኖም ግን በክረምቱ የጸባይ ለውጥ ምክንያት መጠቀም የሚቻለው ለጥቂት ወራት ብቻ ነው። ሞተርሳይክል ለመንዳት ልዩ መንጃ ፈቃድ ያስፈልጋል።



**6. መኪናዎች**

በካናዳ የተለያዩ ዓይነት እና መጠን ያላቸው መኪናዎች አሉ። እርስዎም ከእነዚህ ውስጥ የኑሮ ዘይቤ፣ አቅም እና ፍላጎትዎን መሠረት በማድረግ ሊመርጡ ይችላሉ። መኪና ከመግዛት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ተጨማሪ ወጪዎች ሲኖሩ፣ ከእነዚህም ኢንሹራንስ፣ ነዳጅ እና ጥገና ይገኙበታል።



**7. ጀልባዎች**

በብሪቲሽ ኮሎምቢያ እና አትላንቲክ አካባቢ ባሉ የባህር ዳርቻ ቦታዎች፣ ጀልባዎች የተለመዱ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ናቸው። ብዙዎቹም ተሳፋሪዎችንም ሆነ ተሽከርካሪዎችን መጫን የሚችሉ ናቸው።




**8. አውሮፕላን**

በካናዳ ረጅም መንገዶችን በፍጥነት ለመጓዝ ያለው መንገድ አውሮፕላን ነው። ውድ ይሁን እንጂ በመጨረሻ የወጣው ወጪ ሲታይ መኪና ለማሽከርከር ወይም ባቡር ለመሳፈር ከሚወጣው ወጪ አንጻር ዝቅተኛ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ሁሉም በካናዳ የሚገኙ ዋና ከተማዎች አውሮፕላን ማረፊያዎች አሏቸው።



**9. ባቡር**

የባቡር መስመር በመላ አገሪቱ የተዘረጋ ነው። ሆኖም ግን ሁሉም ትልቅም ሆኑ መካከለኛ ከተማዎች በባቡር የተሳሰሩ አይደሉም። ለባቡር ትኬቶችን ቀድሞ መግዛት ብዙም ውድ አይደለም።



**10. ከተማ ዓቀፍ አውቶቢስ**

ይህም በከተማዎች መካከል ለመንቀሳቀስ ብዙም ውድ ያልሆነ መንገድ ነው። ከመንገዱ ርቀት የተነሳ ጉዞው ረጅም ሊሆን ይችላል። መኪና ከሌለዎት በተለይ ወደ መካከለኛ ከተማዎች ለመሄድ ብቸኛው መንገድ ነው።



**በካናዳ ስላለው መጓጓዣ/ትራንስፖርት ብዙ ማወቅ ይቻላል። ካናዳ ሲደርሱ በመንግሥት የሚደጎም ድርጅት ወይም ለጋሾችዎን በአካባቢዎ ስላለው መጓጓዣ/ትራንስፖርት እንዲነግርዎት ይጠይቋቸው።**



## 9.2 የመጓጓዣ/ትራንስፖርት ወጪ

**መመሪያ:** በካናዳ ያሉ የመጓጓዣ/የትራንስፖርት ዓይነቶችን ይመልከቱ። ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡት ላይ የ "$$$" ምልክት፣ መካከለኛ ወጪ ላላቸው "$$" እንዲሁም ዝቅተኛ ወጪ ለሚያስወጡ የ "$" ምልክት ጋር ያድርጉ።


**1.** የረጅም ርቀት ጉዞ






$$$


ሀ) አውሮፕላን



ለ) ባቡር




ሐ) ከተማ ዓቀፍ አውቶቢሶች



መ) ጀልባዎች




የሕዝብ ትራንስፖርትን፣ ካርታ እና ትኬቶችን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት በአካባቢዎ ያለ የአውቶቢስ ወይም የባቡር ጣቢያ የመረጃ መስኮት ጋር በመደወል አልያም በአካል በመሄድ መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን በቀጥታ ከድረገጽ መፈለግም ይችላሉ።



መልሶች፡ (ሀ) $$$፤ (ለ) $$-$$$፤ (ሐ) $፤ (መ) $$

## 2. የአጭር ርቀት ጉዞ






ሀ) ታክሲ





ለ) የጉዞ መጋሪያ መተግበሪያዎች




ሐ) የሕዝብ ትራንስፖርት

## 3. የግል ተሽከርካሪን በመጠቀም መጓዝ






ሀ) ሞተርሳይክል



ለ) ብስክሌት




ሐ) መኪናዎች

መልሶች: 2 (ሀ) $$$; (ለ) $$; (ሐ) $; 3 (ሀ) $$; (ለ) $; (ሐ) $$$


# 9.3 በካናዳ የሕዝብ መጓጓዣ/ትራንስፖርት መጠቀም

***መመሪያ:*** በካናዳ የሕዝብ ትራንስፖርት ስለመጠቀም የተጻፈውን መግለጫ ያንብቡ። አዲስ የሆነብዎት ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ “ ✔ ” ምልክት ያስቀምጡ።






☐ **1.** የሕዝብ መጓጓዣ/ትራንስፖርት ለመጠቀም ወደ ተሽከርከሪው ሲገቡ መክፈል፣ አስቀድሞ መሳፈሪያ ትኬት መግዛት ወይም የይለፍ ካርድ መያዝ ግዴታ ነው።




☐ **2.** ብዙ ከተማዎች እና አካባቢዎች ተደራሽ የሆነ የሕዝብ መጓጓዣ/ትራንስፖርት አላቸው። ከእነዚህም በተለይ እንደልብ ለመንቀሳቀስ ለሚቸገሩ የሚሆኑ የተሟሉ አውቶብሶች ይገኙበታል።



☐ **3.** ለተማሪዎች እንዲሁም እድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ ለሆኑ ሰዎች ቅናሽ አለ።



☐ **4.** የሚወርዱበት ቦታ በደረሱ ሰዓት፣ በተሳፈሩት አውቶቢስም ሆነ መኪና መጥሪያ በመንካት አልያም መጥሪያውን በመደወል ለመውረድ እንደፈለጉ ለአሽከርካሪው ያሳውቁ። የሚወርዱበትን ቦታ ለመለየት እርዳታ ካስፈለግዎ፣ አሽርካሪውን ይጠይቁ እና ፊት ለፊት በሚገኙ ወንበሮች አካባቢ ይቀመጡ።



☐ **5.** በእድሜ ከእርስዎ ከፍ ላሉ፣ አካል ጉዳት ላለባቸው፣ ለነፍሰ ጡር ሴቶች ወይም ሕጻን ልጅ ለያዙ አዋቂዎች ወንበር እንዲለቁ ይጠበቅብዎታል።



6. ብዙ ጊዜ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አሽከርካሪዎች በጥሬ ገንዘብ ክፍያን ስለማይቀበሉ እና መልስ ለመስጠት ስለሚቸገሩ በሚሳፈሩበት ጊዜ መልስ የሚያስፈልገውን ትክክለኛውን የክፍያ መጠን ይዘው እንዲገቡ ይመረጣል።



7. ወደ የሕዝብ ትራንስፖርት ሲገቡ፣ አስቀድመው የተሳፋሩ እስኪወርዱ ጠብቀው ይሳፈሩ።



8. በጉዞዎ ሁሉ መክፈልዎን የሚያረጋግጠውን ደረሰኝ ይያዙ።




9. በሕዝብ ትራንስፖርቶች ላይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው የድንገተኛ አደጋ መጠቆሚያዎች አሉ።




10. የሕዝብ ትራንስፖርት በሚጠብቁበት ጊዜ እርስዎም ሆነ ሌሎች መንገደኞች በአግበቡ መሰለፍ አለባችሁ።




11. የትምህርት ቤት አውቶቢሶች በትምህርት ቤቱ በተወሰነ ርቀት ላይ ለሚገኙ ልጆች ሁሉ የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። የተቀሩት እና በርቀት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የሕዝብ ትራንስፖርት ሊጠቀሙ ይችላሉ።

**በብዙ ከተማዎች በእግር እርምጃ መሄድ እና ብስክሌትን መጠቀም ይቻላል። የሕዝብ ትራንስፖርት ከመጠቀምም ሆነ መኪናን ከማሽከርከር ጋር ሲነጻጸር ጤናማ አማራጮች አሉት። ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ቤት በእግር ወይም በብስክሌት ሊሄዱ ይችላሉ።**




# 9.4 በካናዳ መኪና ማሽከርከር

በካናዳ ለመጀመሪያ ጊዜ የመኪና መንጃ ፈቃድ ለማግኘት ያለው ሂደት እንደሚኖሩበት ክልል ወይም ግዛት የተለያየ ነው። በአብዛኞቹ ክልሎችና ግዛቶች ማንኛውም ጸታ ለሆኑ ሰዎች የመንጃ ፈቃድ ትምህርት ለመማር ቢያንስ 16 ዓመት ሊሆናቸው ይገባል።

***መመሪያ፡*** በካናዳ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ሊያልፉበት የሚገባውን ሂደት ያንብቡ። ከመጀመሪያ ወደ መጨረሻ ከ**1** እስከ **6** ድረስ ቁጥር በመስጠት በቅደም ተከተል ያስቀምጧቸው።



☐ ሀ) የለማጅ ፈቃድ መያዝ።



**1** ለ) ማመልከቻ መሙላት።




☐ ሐ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ማግኘት።



☐ መ) የአሽርካሪዎች የጽሑፍ ፈተና ማለፍ።




☐ ሠ) መንገድ ላይ የማሽከርከር ፈተናን ማለፍ።




☐ ረ) ለማሽከርከር ፈተና መዘጋጀት፤ የማሽከርከር ትምህርት/ኮርስ መውሰድና ቶሎ የማሽከርከር ሙሉ ፍቃድን ማግኘት።

**በሌላ ሀገር የያዙት ህጋዊ የመንጃ ፈቃድ ካለዎት፤ በአካባቢዎ የአሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ ሊያስቀይሩ ወይም ካናዳ ከገቡ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በመንግስት የሚደጎም ድርጅት ወይም ሊጋሮችዎ በሚኖሩበት ግዛት ወይም አካባቢ ስላሉ ደንቦች እንዲነግርዎ ይጠይቁ።**



መልሶች፡ (ሀ) 3፤ (ለ) 1፤ (ሐ) 6፤ (መ) 2፤ (ሠ) 5፤ (ረ) 4

# 9.5 መኪና መግዛት

**መመሪያ:** በካናዳ መኪና የገዛውን የዚህን ሰው ተሞክሮ ይመልከቱ።

1. 

2. 

3. 

4. 



5. 


6. 


**ይህ ሰው ከዚህ የተለየ ሊያደርግ የሚችለው ምን ነበር?**

# 9.6 ከማሽከርከር ጋር የተገናኙ ሕጎች



በካናዳ የተሽከርከሪ ሕጎች በአግባቡ ተግባራዊ ይደረጋሉ። እነዚህን ሕጎች ጥሶ መገኘትም ብዙ ወጪ የሚያስወጣ ሲሆን ከክፍያ ጀምሮ ከፍተኛ የመድኅን ወጪ አልፎም እገዳ እና የመንጃ ፈቃድ መቀማት ድረስ የሚዘልቅ ቅጣት ያስቀጣል።

**መመሪያ:** በካናዳ ስላሉት የተሽከርካሪ ሕጎችን ይመልከቱ። አዲስ የሆነብዎ ሕግ ላይ በሳጥኑ ውስጥ የ "✓" ምልክት ያድርጉ።




☐ **1.** በካናዳ ያሉ አሽከርካሪዎች የመንጃ ፈቃድ እና የመኪና መድኅን የገቡበት ማረጋገጫ ያስፈልጋል። ያለእነዚህ መኪና ማሽከርከር ሕጋዊ አይደለም፣ አሽርካሪዎችም በሚያሽከረክሩበት ሰዓት ሁሉ እነዚህን ሊይዙ ይገባል።



☐ **2.** አሽከርካሪዎች በተለያየ ነገሮች ተጽእኖ ስር ሆነው እንዲያሽከረክሩ አይፈቀድላቸውም። (አደንዛዥ እጾች፣ አልኮል ወይም መድኃኒት)





☐ **3.** ቀይ መብራት ሲበራና የአቁም ምልክትን ሲያሳይ ሁሉም አሽከርካሪዎች ከተማሪ አውቶብሶች በተወሰነ ርቀት ጠብቀው መቆም አለባቸው።



☐ **4.** ተሽርካሪዎች የሚነዱት በግራ በኩል ነው። አሽርካሪዎች መብራታቸውን እያበሩ እና ሳይረን እያስጮኹ ለሚሄዱ ለድንገተኛ የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።



☐ **5.** ማንኛውም ሰው ተሳፋሪም ሆኖ ይሁን አሽከርካሪ መኪና ሲሳፈር የመኪና ወንበር ቀበቶ ማሰር ግዴታ ነው።



☐ **6.** በአብዛኛው የካናዳ አካባቢዎች ለማሽከርከር ፈታኝ ከሆኑ ኩነቶች ውስጥ በረዶ ዋነኛው ነው። በአንዳንድ ግዛቶች እና ክልሎች የክረምት ጎማ መጠቀም ግዴታ ነው።



☐ **7.** ትንሽ ልጆች እና ሕጻናት መቀመጥ ያለባቸው ከመኪና የኋላ ወንበር፣ ለእነርሱ ተለይቶ በተዘጋጀ ደኅንነታቸውን በሚጠብቅ መቀመጫ ላይ ነው። የወንበር ምርጫው በልጆች የእድሜ እና ክብደት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። የልጆችን መቀመጫ ወንበር በሚመለከት ይህን ይህንን ያንብቡ፤

# 9.7 በካናዳ የተለመዱ የመንገድ ላይ ምልክቶች

አነዚህ የመንገድ ምልክቶች አንዳንድ ቦታዎች ላይ በተወሰነ መንገድ ለየት ያሉ ይምሰሉ እንጂ በመላው ካናዳ ሊታዩ ይችላሉ።


**መመሪያ:** የመንገድ ምልክቶችን ይመልከቱ። በየአንዳንዱ ምልክት እና በዝርዝሩ መካከል በማስመር ያዛምዱ።



**1.**



**2.**



**3.**



**4.**



**5.**

**ሀ) የሚያንሸራትት መንገድ**


**ለ) እንስሳት የሚያቋርጡበት**

**ሐ) የትምህርት ቤት መሻገሪያ መንገድ**


**መ) ተራመድ**

**ሠ) ለብስክሌት ብቻ**


**መንገድ ሲሻገሩ በዙሪያዎ ያለውን የትራፊክ ምልክቶችን ልብ ይበሉ።**



**ቀይ ማለት "ቁም"**




**ቢጫ ማለት "ፍጥነት ቀንስ"**



**አረንጓዴ ማለት "ሂድ"**

መልሶች: 1 (ለ)፣ 2 (ሀ)፣ 3 (ሠ)፣ 4 (ሐ)፣ 5 (መ)

| | | |
|---|---|---|
|  | 6. | ረ) ወደ ቀኝ መታጠፍ አይቻልም |
|  | 7. | ሰ) የእግረኛ መሻገሪያ |
|  | 8. | ሸ) ቁም |
|  | 9. | ቀ) አውቶቢስ ብቻ |
|  | 10. | በ) አትራመድ |
|  | 11. | ተ) የፍጥነት ገደብ በኪሎሜትር በሰዓት |
|  | 12. | ቸ) ማሳለፍ (መንገድ መልቀቅ) |



በመንገድ ላይ ከሌላ መኪና ጋር ግጭት ቢፈጥሩ ወይም እግረኛ ቢገጩ ፣ የአደጋ ቦታውን ትቶ መሄድ ከባድ ወንጀል ነው። ፖሊስ እንዲሁም አምቡላንስ ለመጥራት የድንገተኛ አደጋ ቁጥር 911 ላይ ይደውሉ።




መልሶች፦ 6 (ቀ)፤ 7 (ሸ)፤ 8 (ረ)፤ 9 (ሰ)፤ 10 (ቸ)፤ 11 (በ)፤ 12 (ተ)


# መልካም እድል በካናዳ!



# ማስታወሻዎች




በካናዳ ሁሉም የሰፈራ ፕሮግራሞች በነጻ የሚሰጡ ናቸው። እያንዳንዱ የሰፈራ ሁኔታ የራሱ መልክ ያለው እና የተለየ ነው። ከላይ የተጠቀሱት የሂደት ዝርዝሮች ቅደም ተከተላቸው ሊለያይ ይችላል።





IOM
UN MIGRATION

AMHARIC